# አዲስ ዘመን

ኢፕድ

ረቡዕ

82ኛ ዓመት ቁጥር 291 ሰኔ 21 ቀን 2015 ዓ.ም ዋጋ 10.00

ብዕራችን ለኢትዮጵያ ህዳሴ ይተጋል!


## “ኢትዮጵያ ከምንም ነገር በላይ ዛሬ የምትፈልገው፣ መከባበርን እና መፋቀርን ነው”

- ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶክተር)



በጋዜጣው ሪፖርተር

አዲስ አበባ፡- ሙስሊሞች የዒድ አል አድሃን በአንድነትና በፍቅር እንደሚያከብሩት ሁሉ ኢትዮጵያ ከምንም ነገር በላይ ዛሬ የምትፈልገው፣ መከባበርን እና መፋቀርን ነው ሲሉ ጠቅላይ ሚኒስትር ዶክተር ዐቢይ አሕመድ ገለጹ፡፡ ጠቅላይ ሚኒስትሩ ለ1444ኛው የዒድ አል አድሃ የእንኳን አደረሳችሁ መልዕክት አስተላልፈዋል፡፡

ጠቅላይ ሚኒስትር ዶክተር ዐቢይ አሕመድ ለሙስሊም ዕምነት ተከታዮች ለ1444ኛው የዒድ አል አድሃ በዓል በማስመልከት ትናንት ባስተላለፉት መልዕክት እንዳሉት፤ የአረፋ ኮረብታ ከመላው ዓለም የተሰባሰቡ ሙስሊሞች የዒድ አል አድሃን በአንድነት ያከብራሉ፡፡ ዜግነታቸውና ማንነታቸው የተለያየ ቢሆንም፣ ሁሉም የሚያስቡት ሙስሊም መሆናቸውን ብቻ ነው፡፡ የተለያዩበትን ረስተው የተገናኙበትን፣ የተሣሠሩበትን እያሰቡ፣ አንድ ይሆናሉ፡፡

እኛም ለምንለያይበት ሳይሆን ለምንገናኝበት፣ ለምንገፋፋበት ሳይሆን ለምንሳሳብበት፣ ለምንሻኮትበት ሳይሆን ለምንተባበርበት ቅድሚያ ሰጥተን፣ አንድ ትልቅ ሕዝብ እንሁን፡፡ ከልዩ ልዩ ቦታ ብንመጣም፣ ልዩ

"ኢትዮየጵያ ከምንም .. ወደ ገጽ 4 ዞሯል

## “የሚያጋጥሙንን ተግዳሮቶች በትብብርና በአጋርነት መንፈስ ለመፍታት ጊዜው አሁን ነው”

- አቶ ደመቀ መኮንን -
ምክትል ጠቅላይ ሚኒስትር እና የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር

ቃልኪዳን አሳዬ

አዲስ አበባ፡- የሚያጋጥሙንን ተግዳሮቶች በትብብርና በአጋርነት መንፈስ ለመፍታት ጊዜው አሁን ነው ሲሉ ምክትል ጠቅላይ ሚኒስትር እና የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር አቶ ደመቀ መኮንን በዓለም አቀፉ የትምህርት ትብብር ድርጅት (አኢሲ) ጉባዔው ላይ ተናገሩ፡፡

የዓለም አቀፉ የትምህርት ትብብር ድርጅት (አኢሲ) የመጀመሪያ ልዩ ጉባኤውን በትናንትናው ዕለት በአዲስ አበባ ማካሄድ ጀምሯል።

ምክትል ጠቅላይ ሚኒስትር እና የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር አቶ ደመቀ መኮንን ለተሳታፊዎቹ የእንኳን ደህና መጣችሁ መልዕክት ባስተላለፉበት ወቅት የሚያጋጥሙንን ተግዳሮቶች በትብብርና በአጋርነት መንፈስ ለመፍታት ጊዜው አሁን ነው ብለዋል፡፡

ኢትዮጵያ እንደ ሀገር የተጣለባትን ሃላፊነት ለመወጣት ቁርጠኝነቷን አጠናክራ እንደምትቀጥል ገልጸው፤ በተለይም ለዓለም አቀፉ የትምህርት ትብብር ድርጅት (አኢሲ) ውጥን መሳካት ሁሉን አቀፍ ድጋፍ እንደምታደርግ አረጋግጠዋል።

"የሚያጋጥሙንን ተግዳሮቶች .. ወደ ገጽ 11 ዞሯል





## “የሀገርን ሉዓላዊነት የሚያስከብር ጠንካራ ሠራዊት በመገንባት ለቀጣዩ ትውልድ እናስረክባለን”

- ፊልድ ማርሻል ብርሃኑ ጁላ
የጦር ኃይሎች ኢታማዦር ሹም

ሞገስ ተስፋ


ቢሾፍቱ፡- ከመቼውም ጊዜ በበለጠ የህዝብን ደህንነትና የሀገርን ሉዓላዊነት የሚያስከብር ጠንካራ ሠራዊት በመገንባት ለቀጣዩ ትውልድ እናስረክባለን ሲሉ የጦር ኃይሎች ኢታማዦር ሹም ፊልድ ማርሻል ብርሃኑ ጁላ ገለጹ። የኢትዮጵያ ባህር ኃይል በተለያዩ የሙያ መስኮች ያሠለጠናቸውን ባህረተኞች

"የሀገርን ሉዓላዊነት .. ወደ ገጽ 11 ዞሯል












## ሕዝበ ሙስሊሙ በዓሉን ኃይማኖታዊ እሴቱን በጠበቀ መልኩ ሊያከብረው ይገባል

ገጽ 4







# በህዝበ ውሳኔው ስድስት ዞኖችና አምስት ልዩ ወረዳዎች ክልል ለመመስረት የሚያስችላቸውን ድምጽ አገኙ

**ሳሙኤል ወንደሰን**

<u>አዲስ አበባ፡-</u> የስድስት ዞኖች እና የአምሥት ልዩ ወረዳዎች ባካሄዱት ህዝበ ውሳኔ ከ752 ሺህ በላይ መራጮች በአንድ ክልል እንደራጅ የሚል ድምጽ መስጠታቸውን የኢትዮጵያ ምርጫ ቦርድ አስታወቀ። ቦርዱ በትናንትናው ዕለት የመጨረሻውንና የተረጋገጠውን የሕዝበ ውሣኔው ውጤት ይፋ አድርጓል።

ህዝበ ውሳኔው በኮንሶ፣ በወላይታ፣ በደቡብ ኦሞ፣ በጋሞ፣ በጌዴኦ፣ በጎፋ ዞኖችን እና በቡርጂ፣ በባስኬቶ፣ በአሌ፣ በአማሮ፣ በደራሼ ልዩ ወረዳዎችን ያካተተ ነው። በተካሄደው ሕዝበ ውሳኔም አብዛኛው ድምጽ ሰጪ በአንድ ክልል መደራጀትን መምረጡ ይፋ ተደርጓል።

ለድምጽ አሰጣጡ ከተመዘገቡት 840 ሺህ 226 መራጮች ከ752 ሺህ በላይ የሚሆኑ መራጮች በአንድ ክልል እንደራጅ የሚል ድምፅ መስጠታቸውን በውጤቱ ተገልጿል።

በመግለጫው እንደተገለጸው፤ አንበሁምቦ ማዕከል በቦ/ገዋ ሀ 2 ምርጫ ጣቢያ እና በቦዲቲ ማዕከል በሻብሼ ሸኔ ሀ ምርጫ ጣቢያ በመሳሰሉ አንዳንድ ጣቢያዎች ድምጽ መስጫ ሳጥን ውስጥ የተገኘው የድምጽ መስጫ ወረቀት ብዛት በዕለቱ ድምጽ ለመስጠት ከፈረሙት መራጮች በላይ በሆኑ ከውጤት መዳመር ውጪ ሆኗል።

በኦፋ ማዕከል ገሱባ ምርጫ ጣቢያ 05 ላይ መራጮች ይዘው የመጡት መታወቂያ በወጣበት ቀን ላይ ስርዝ ድልዝ በማድረግ ለመቀየር ሙከራ የተደረገባቸው መታወቂያዎች ተገኝተዋል።

በቦዲቲ ማዕከል ሰፈራ ሰላም 5 እና ሻሻ ጋሌ 2 እንዲሁም ዳሞት ሞኮኒስ 1 በመሳሰሉ ጣቢያዎች ዕድሜያቸው ለመምረጥ ያልደረሱ መሆናቸው በግለጽ የሚያስታውቅ ህጻናት ሰልፍ ላይ መገኘታቸው በቦርዱ ተከታታዮች ተረጋግጧል።

በበሌ ማዕከል አይዲ ጫማ ብድራቴ ምርጫ ጣቢያ ላይ የቀበሌ አመራሮች ምርጫ ጣቢያ ላይ ተገኝተው ያለምስክር አስመርጡ በማለት ተፅዕኖ ማድረጋቸው በቦርዱ ተከታታዮች ተረጋግጧል።

ዳሞት ፑላሳ ማዕከል ጋሌ ቡጌ ምርጫ ጣቢያ ላይ የሲቪክ ማህበራት ታዛቢ ከአስፈጻሚዎች ጋር በምርጫ ጣቢያ ውስጥ ውጤት ሲቆጥር በክትትል ቡድኑ ተገኝቷል።

ሶዶ ከተማ ማዕከል ገበያ አዳራሽ 11 ምርጫ ጣቢያ ላይ የቀበሌ አመራሮች በምርጫ ጣቢያው ውስጥ ተገኝተው ተፅዕኖ ሲያደርጉ እንደነበር በቦርድ አመራር አባላት ታይቷል።

አንዳንድ ችግር የታየባቸው ጣቢያዎች ከውጤት እንዲወጡ ከመደረጉ በተጨማሪ በውጤት ማረጋገጥ ሂደት ላይ በመራጮች መዝገብ ላይ የሰፈሩ ፊርማዎች አጠቃላይ ብዛት ላይ የድምር ስህተት በመገኘቱ በአረጋጋጭ ቡድኑ የድምር ማስተካከያ ተደርጓል። በዚህም ምክንያት የመረጡ መራጮች ድምር ከ849,896 ወደ 840,226 ተስተካክሏል።

በሌላ በኩል የኢትዮጵያ ምርጫ ቦርድ ዋና ሰብሳቢ ብርቱካን ሚደቅሳ በሕመም ምክንያት ከኃላፊነታቸው ለመልቀቅ ለህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጥያቄ ማቅረባቸውን ገልጸዋል።

ይህንንም ጥያቄያቸውን ሰኔ 5 ቀን 2015 ዓ.ም ለሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ማቅረባቸውን የገለጹ ሲሆን ኃላፊዋ እስከ ፊታችን ነሀሴ 1 ቀን 2015 ዓ.ም ድረስ በህዝብ የተጣለባቸውን ኃላፊነት እንደሚወጡም ታውቋል።

# “ሕፃናት በአካልና በአዕምሮ ጎልብተው የሚያድጉባት ከተማን ለመገንባት በትኩረት እንሰራለን”

- አዳነች አቤቤ - የአዲስ አበባ ከተማ ከንቲባ

**ሄለን ወንድምነው**



ከንቲባ አዳነች አቤቤ

<u>አዲስ አበባ</u>፡- ሕፃናት በአካልና አዕምሮ ጎልብተው የሚያድጉባት በአፍሪካ ተመራጭ የሆነች ከተማን ለመገንባት በትኩረት እንሰራለን ሲሉ የአዲስ አበባ ከተማ ከንቲባ አዳነች አቤቤ ተናገሩ፡፡

“ሕፃናት የነገ ተስፋ ለአዲስ አበባ” በሚል መሪ ቃል ለተጀመረው የቀዳማይ ልጅነት ልማት ፕሮግራም በሚቀጥሉት ሶስት ዓመታትና 90 ቀናት በሚሰሩ ሥራዎች ከባለድርሻ የከተማ አስተዳደሩ ተቋማት፣ ከክፍለ ከተሞች እና ወረዳ አመራሮች ጋር በትናንትናው ዕለት ውይይት ተካሂዷል፡፡

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ከንቲባ አዳነች አቤቤ በውይይቱ ላይ ባደረጉት ንግግር፤ በአዲስ አበባ ከተማ ለሶስት ዓመታት ተግባራዊ በሚደረገው የቀዳማይ ልጅነት ልማት ፕሮግራም ሕፃናት በአካልና አዕምሮ ጎልብተው የሚያድጉባት በአፍሪካ ተመራጭ የሆነች ከተማን ለመገንባት በትኩረት እንደሚሰራ ገልጸዋል፡፡

የቀዳማይ ልጅነት ልማት ፕሮግራም “አዲስ አበባ ሕፃናትን ለማሳደግ ምርጥ የአፍሪካ ከተማ ለማድረግ“ የሚል ራዕይ የተሰነቀበትና ለወላጆች፣ ለአሳዳጊዎች እና ለሕፃናት ሁለንተናዊ አገልግሎት ለመስጠት ያለመ ነው ብለዋል፡፡

የቀዳማይ ልጅነት ልማት ፕሮግራም ከጽንስ እስከ ስድስት ዓመት ዕድሜ ባላቸው ሕፃናት እና በቅድመ አንደኛ ደረጃ ትምህርት አሰጣጥ ላይ ትኩረት በማድረግ ለሶስት ዓመታት ተግባራዊ የሚደረግ መሆኑን አስታውቀዋል፡፡

በፕሮግራሙ የሚከናወኑት ተግባራት በስድስት ስትራቴጂካዊ ዕቅዶች ላይ ያተኮረ መሆኑን ጠቁመው፤ የወላጆች ምክር እና ሁለንተናዊ አገልግሎት ድጋፍ ሥርዓት መዘርጋት አንዱ መሆኑን ገልጸዋል።

በሶስት ዓመታት በዝቅተኛ የኑሮ ደረጃ ለሚገኙ 330 ሺህ የማህበረሰብ ክፍሎች የምክር አገልግሎት ይሰጣል ያሉት ከንቲባዋ፤ በቀጣይ ጊዜያት ሁሉንም ህብረተሰብ ተደራሽ ለማድረግ በትኩረት ይሰራል ብለዋል፡፡

12 ሺህ የሕፃናት መጫወቻ ስፍራዎችን መገንባት፣ አንድ ሺህ የህጻናት መዋያዎችን ማልማት፣ አንድ ሺህ 95 የቅድመ አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶችን ትራንስፎርም ማድረግ በቀዳማይ ልጅነት ልማት ፕሮግረሙ የሚከናወኑ ተግባራት መሆናቸውን አስረድተዋል፡፡

እንደ ከንቲባዋ ገለጻ፣ 101 ጤና ጣቢያዎችን ለቀዳማይ ልጅነት ልማት አገልግሎት ምቹ ማድረግ፣ ለወላጆችና አሳዳጊዎች የምክር አገልግሎት የሚሰጡ አምስት ሺህ ሰራተኞችን አሰልጥኖ ማሰማራት እና የሀገሪቱን ብሎም የአፍሪካን የቀዳማይ ልጅነት ሥራዎች በምርምር እና ስርፀት የሚደግፍ የልህቀት ማዕከል መገንባት በፕሮግራሙ ለማከናወን ከተያዙት ዕቅዶች መካከል ናቸው ብለዋል፡፡

ከጽንስ ጀምሮ እስከ ስድስት ዓመት ባሉ ሕፃናት ላይ ትኩረት አድርጎ ለመስራት በተቋቋመው እና በሀገሪቱ የመጀመሪያ በሆነው የቀዳማይ ልጅነት ፕሮግራም በትውልድ መካከል እያጋጠመ ያለውን ስብራት ከምንጩ ለመፈወስ በዚህ የዕድሜ ክልል ላይ ለመሥራት ምክንያት መሆኑን ገልጸዋል፡፡

የቀዳማይ ልጅነት ልማት ፕሮግራም የነገ ሀገር ተረካቢ ህፃናት ላይ የሚሰራ በመሆኑ ለሀገሪቱ የሚያስገኘው ጠቀሜታ ጉልህ ነው ያሉት ከንቲባዋ፤ በአዲስ አበባ የተጀመረውን የቀዳማይ ልጅነት ልማት ፕሮግራም እንደማሳያ በመጠቀም በሌሎች የሀገሪቱ አካባቢዎች ተግባራዊ ሊደረግ እንደሚገባ አመላክተዋል።

# “የሙስና የስር መሠረት የሆነውን የሥነ ምግባር ዝቅጠት በጋራ ልናስወግደው ይገባል”

- አሰፋ ቶላ
የአዲስ አበባ የሥነ ምግባር እና የጸረ ሙስና ኮሚሽን ምክትል ኮሚሽነር

**ዳግማዊት አበበ**



<u>አዲስ አበባ</u>፡- የሙስና የስር መሠረት የሆነውን የሥነ ምግባር ዝቅጠት በጋራ ልንሠራና ልናስወግደው ይገባል ሲሉ የአዲስ አበባ የሥነ ምግባር እና የጸረ ሙስና ኮሚሽን ምክትል ኮሚሽነር አሰፋ ቶላ ገለጹ፡፡

ኮሚሽኑ በአዲስ መልክ መልሶ በተቋቋመው የሰራተኞች አደረጃጀት እና አሰራር መመሪያ ዙሪያ ከከተማ አስተዳደር ሁሉም ሴክተሮች፣ ከክፍለ ከተማ የቡድን መሪዎችና ባለሙያዎች እንዲሁም ከ121 የወረዳ ቡድን መሪዎች ጋር በትናንትናው ዕለት ውይይት አድርጓል፡፡

በውይይቱ ላይ ንግግር ያደረጉት በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የሥነ ምግባርና ጸረ ሙስና ኮሚሽን ምክትል ኮሚሽነር አሰፋ ቶላ እንደገለጹት፤ የጸረ-ሙስና ስራ የአንድ ተቋም ብቻ ስራ አይደለም። የብዙ አካላት ቅንጅትን ይጠይቃል፡፡ የሙስና የስር መሠረቱ የሥነ ምግባር ዝቅጠት ነው፡፡ የሥነ ምግባር ዝቅጠት እንዳይኖር ደግሞ ብዙ ባለድርሻ አካላት በጋራ ሊሰሩ ይገባል፡፡

የሙስና የስር መሠረት የሆነውን የሥነ ምግባር ዝቅጠት በጋራ ልንሠራና ልናስወግደው ይገባል ብለዋል፡፡

ከባለድርሻ አካላቱ መካከል የሃይማኖት፣ የትምህርት እና የሚዲያ ተቋማት ትልቁን ድርሻ ሊወስዱ ይገባል ያሉት ምክትል ኮሚሽነሩ፤ ያለበለዚያ የጸረ ሙስና ትግሉን ማሳካት አንችልም ሲሉ ገልጸዋል።

በዚህም ሥነ ምግባር ላይ የሚሰሩ ሥራዎች ውጤታማ እንዲሆኑ በዚህ ዓመት ከሃይማኖት ተቋማትና ከሚዲያ አካላት ጋር አብሮ ለመስራት ተፈራርመናል ብለዋል፡፡

እንደ ምክትል ኮሚሽነር አሰፋ ገለጻ፤ መንግሥት ለጸረ ሙስና ትግሉ ትኩረት ሰጥቶ እየሰራ ነው፡፡ ለዚህም ጠቅላይ ሚኒስትሩ እንደ ሀገር ያቋቋሙት የጸረ ሙስና ኮሚቴ አንዱ ማሳያ ነው፡፡ በዚህም ኮሚሽኑ በከተማ አስተዳደር ደረጃ ይህን ኮሚቴ በማዋቀር ሙስናን የልማት እና የዴሞክራሲ ስጋት የማይሆንበት ደረጃ ላይ ለማድረስ እየተሰራ ነው፡፡ በዚህ መሠረትም ጥቆማዎች በመቀበል የተጠያቂነት ሥራዎች በአግባቡ እየተሰሩ ይገኛሉ፡፡

ምክትል ኮሚሽነሩ አክለውም፤ ኮሚሽኑ በ2015 በጀት ዓመት እንደ አዲስ ከመቋቋሙ ጋር ተያይዞ በዚህ ዓመት ተቋም የማደራጀት ሥራ ነው እየሰራ ያለው፡፡ በዚህም ቀደም ሲል በፌዴራል ስር የነበሩ መኮንኖችን በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ስር በማድረግ እንደ አዲስ እንዲዋቀር መደረጉን ተናግረዋል፡፡

ሙስናን ለመከላከል በሚደረገው እንቅስቃሴ ሁሉም ዜጋ የጸረ ሙስና ትግሉ አካል ሊሆን እንደሚገባ ጥሪ አቅርበዋል፡፡

# የአረፋ በዓል መገለጫ የሆነው መረዳዳት እንዲጎለብት የሃይማኖት አባቶች ሃላፊነታቸውን ሊወጡ ይገባል"

**- ረዳት ፐሮፌሰር አደም ካሚል-**
**የታሪክ ተመራማሪ**

**ሞገስ ተስፋ**

አዲስ አበባ:- የአረፋ በዓል መገለጫ የሆነው መደጋገፍና መረዳዳት እንዲጎለብት የሃይማኖት አባቶች ሃላፊነታቸውን ሊወጡ ይገባል ሲሉ የታሪክ ተመራማሪው ረዳት ፕሮፌሰር አደም ካሚል ገለጹ።

ረዳት ፕሮፌሰር አደም ካሚል ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፣ በእስልምና እምነት ተከታዮች ዘንድ የሚከበረው የአረፋ በዓል ትልቁ የሀጅ በዓል የሚከበርበት ቦታ ነው፡፡

አረፋ አደምና ሀዋ የተገናኙበት ነው ያሉት ረዳት ፕሮፌሰር አደም፣ የአረፋ በዓል በአንድ ቦታ በአንድ አለባበስ ከሁለት ሚሊዮን በላይ የእምነቱ ተከታዮች ቋንቋ ሳይገድባቸው፣ ጥቁሩ፣ ነጩ፣ ሁሉም ስፍራና ማንነት ሳያጥረው በአንድነት በመሰባሰብ ጥያቄያቸውን ለፈጣሪ የሚያቀርቡበት ነው ብለዋል፡፡ ፈጣሪም ምህረቴን ሰጥቻችኋለው ብሎ የሚያውጅበት ፣ በሀጅ ያልተጋበዙና ዕድሉን ያላገኙ በየሀገራቱ የሚኖሩ በጾም ጊዜውን የሚያሳልፉበት እንደሆነም ጠቁመዋል፡፡

እንደ ተመራማሪው ገለጻ፣ በዓሉ የሰው ልጆችን እኩልነት፣ የመተዛዘን፣ የመከባበር፣ ሥርዓትን የሚያስታውስ ነው፡፡



"ለኢትዮጵያውያን የሀጅ ጉዞ ታሪካችን የምናውቅበት መድረክ ነው። "ወደ አካባቢው ስንጓዝ እስላማዊ ስደቱ ወደ ኢትዮጵያ የተንቀሳቀሰው መቼ፣ የት እንደሆነ ነብዩ ሙሃመድ ለምን የአበሻን ምድር እንደመረጡ፣ እነ ቢላል ማን ናቸው፣ ለምንድነው መሥዋእትነት የከፈሉት፣ በእስልምና የነነጃሽ ተሳትፎ ምን ይመስል ነበር የሚለውን በተገቢው ሁኔታ የምንገነዘብበት ነው" ብለዋል፡፡

በሃጅ መድረክ ልክ እንደኮንፈረንስ ሆኖ ኢትዮጵያን የምናስተዋውቅበት ነው ያሉት ረዳት ፕሮፌሰር አደም፣ ነገር ግን እንደ ሀገር ለሀጅ ጉዞ የተሻሉ ምሁራን እንዲሄዱና የኢትዮጵያን ታሪክ በአግባቡ እንዲያስተዋውቁ ከማድረግ አንጻር ውስንነቶቻችንን በመቅረፍ ትኩረት ሊሰጠው ይገባል ብለዋል።

የአረፋ በዓል የእምነቱ ተከታዮች ጥፋት ካለባቸው ለጥፋቱ ይቅርታ ጠይቀው ወደ ትክክለኛ መንገድ የሚመጡበት ነው ያሉት ረዳት ፕሮፌሰሩ፣ እርስ በእርሱ በመተዛዘን ለችግሮች መፍትሄ የሚሰጥበት ትልቅ ሃይማኖታዊ መድረክ እንደሆነም ጠቁመዋል፤ የሃጅ ጉዞ ተንኮልን በመጸየፍ የመተዛዘን፣ የመደጋገፍ ትምህርት የሚቀሰምበት ሃይማኖታዊ ጉዞ እንደሆነም አብራርተዋል፡፡

የታሪክ ተመራማሪው፣ የአረፋ በአል መገለጫ የሆነው የመደጋገፍና የመረዳዳት ባህል እንዲጎለብት የሃይማኖት አባቶች ሃላፊነታቸውን ሊወጡ ይገባል ብለዋል። በኢትዮጵያ በህዝበ ሙስሊሙም ሆነ በክርስትና እምነት ተከታዮች ዘንድ ያለው ክፍተት ተከታዩ ወደ ቤተ እምነቶች ሲመጣ ብቻ ነው ትምህርት የሚያገኘው። ይህ በቂ ስላልሆነ የሃይማኖት መሪዎች ወደ ታች ወርደው ሊታስተምሩ ይገባል። ሰበካው በቤተ ክህነት እና በመስጊድ መቆጠብ የለበትም። የንግዱም ማህበረሰብም ሆነ በተለያዩ የሙያ መስኮች ያለው የእምነቱ ተከታይ ሀቀኛ መሆን አለበት። ለዚህም ሃይማኖታዊ ሥርዓቱን ጠንቅቆ እንዲያውቅ ማድረግ አስፈላጊ ነው ብለዋል።

የአረፋ በዓል እርድ አርዶ ለጎረቤት፣ ለዘመድ፣ ለችግረኞች፣ በሰፊው የምናካፍልበት በዓል መሆን እንዳለበት የጠቀሱት ረዳት ፕሮፌሰር አደም፣ ይህ በነቢዩ ኢብራሂም የተሰጠው ትምህርት አንድ ሰው አንድ እርድ አድርጎ አንድ ሶስተኛውን ለራሱ፣ አንድ ሶስተኛውን ለችግረኞች፣ አንድ ሶስተኛውን ለጎረቤት ይሰጣል። ይህም አብሮ መብላትና መካፈልን ያመጣል። ስለዚህ ትምህርቱን በሚገባ ለእምነቱ ተከታዮች ማስተላለፉ ያስፈልጋል ብለዋል።

መረዳዳት በዓል ሲመጣ ብቻ ሳይሆን ሁልጊዜም ባህል ልናደርገው ያስፈልጋል። ሰላም፣ መረጋጋትና ልማት እንዲመጣ የሃይማኖት ሊቃውንቶች ትልቅ ሚና አላቸው ብለዋል ረዳት ፕሮፌሰር አደም ካሚል፡፡

ረዳት ፕሮፌሰር አደም ካሚል ለመላው የእስልምና እምነት ተከታዮች መልካም የአረፋ በዓል እንዲሆን ተመኝተዋል።

# አረንጓዴ ዐሻራው በሀገሪቱ ለሚያጋጥሙ ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ችግሮች ዘላቂ መፍትሄ የሚሰጥ ነው

- **በመዲናዋ ሁለተኛው ምዕራፍ የአረንጓዴ ዐሻራ ማስጀመርያ መርሃግብር በተለያዩ ክፍለከተሞች ተካሂዷል**

**በጋዜጣው ሪፖርተሮች**

አዲስ አበባ:- የአረንጓዴ ዐሻራ መርሀ ግብሩ በሀገሪቱ ለሚያጋጥሙ ማበራዊና ኢኮኖሚያዊ ችግሮች ዘላቂ መፍትሄ የሚያመጣ መሆኑን የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ምክትል ከንቲባ ተናገሩ፡፡ በከተማዋ የተለያዩ ክፍለከተሞች ሁለተኛው ምዕራፍ የመጀመርያ ዓመት የአረንጓዴ ዐሻራ መርሃግብር በትናንትናው እለት ተጀምሯል፡፡

የአቃቂ ቃሊቲ ክፍለከተማ የ2015 የሁለተኛ ምእራፍ የአረንጓዴ ዐሻራ መርሀ ግብር ንቅናቄን በቂሊንጦ ኢንዱስትሪያል ፓርክ በይፋ ያስጀመሩት የአዲስ አበባ ከተማ ምክትል ከንቲባ አቶ ዣንጥራር አባይ እንደገለጹት በአዲስ አበባ ከተማ ሊተከል ከታቀደው 17 ሚሊዮን ችግኝ 2 ነጥብ 6 በዚህ ክፍለ ከተማ ይተከላል።

አቶ ዣንጥራር የአረንጓዴ ዐሻራ መርሀ ግብር አሁን በሀገሪቱ እያጋጠሙ ያሉ የድርቅና የጎርፍ አደጋዎችን ለመከላከል የሚረዳ በመሆኑ ሁሉም የከተማዋ ነዋሪ አስተዋጽኦውን ሊያበረክት ይገባል ብለዋል።

ምክትል ከንቲባው ባለፉት ዓመታት የተካሄዱ የችግኝ ተከላ መርሀግብሮች በሀገሪቱ የደን ሽፋን ላይ ከፍተኛ አስተዋጽኦ ያበረከቱ በመሆኑ ይህንን አጠናክሮ መቀጠል እንደሚገባ ጠቁመዋል። በተለይም በክፍለ ከተማው ብዙ ኢንዱስትሪዎች የሚገኙ በመሆኑ በትኩረት ሊሰራ እንደሚገባ አሳስበዋል።

እንደ አቶ ዣንጥራር ገለጻ በከተማዋ አጠቃላይ የደን ሽፋን 30 በመቶ ለማድረስ የታቀደ ሲሆን በአሁኑ ጊዜም የከተማዋ አጠቃላይ የደን ሽፋን ከሁለት ነጥብ ስድስት በመቶ ወደ 15 በመቶ ማድረስ መቻሉን ገልጸዋል።

የክፍለከተማው ዋና ሥራ አስፈጻሚ ዶክተር አበራ ብሩ በበኩላቸው በመርሀግብሩ ሁሉም የክፍለከተማው ነዋሪ እንደሚሳተፍ ገልጸው፤ በተለየ መልኩ የፋብሪካ ባለቤቶች፣ የእምነት ተቋማትና ትምህርት ቤቶች ላቅ ያለ ሚና ይጫወታሉ ብለዋል፡፡

ዶ/ር አበራ ህዝቡ ለአረንጓዴ አሻራ የሚያሳየው መነሳሳት ኢትዮጵያን በአረንጓዴ ዐሻራ መርሀ ግብር በዓለም አቀፍ ደረጃ ስሟን ለማስመዝገብ የሚደረገውን ጥረት እውን የሚያደርግ ነው ብለዋል፡፡

በተያያዘም ሁለተኛው ምዕራፍ አንደኛ ዙር የአረንጓዴ ዐሻራ ማስጀመሪያ መርሃ-ግበር በአዲስ ከተማ ክፍለ ከተማ ተካሂዷል፡፡

በማስጀመሪያ መርሃ-ግብሩ ላይ ተገኝተው ንግግር ያደረጉት የአዲስ አበባ ከተማ ምክር ቤት ዋና አፈጉባዔ ወይዘሮ ቡዜና አብዱልቃድር፤ ችግኝ ከመትከል ጎን ለጎን የሀገር አንድነትና ሰላም በሚያጸኑ ዐቢይ ጉዳዮች ላይ በተትጋት መሥራት ያስፈልጋል ብለዋል፡፡

እንደ ወይዘሮ ቡዜና ገለጻ፤ ባለፉት ዓመታት በአረንጓዴ ዐሻራ የተገኙ ለውጦች በአንድነትና በአብሮነት መስራት ምን ያህል የጎላ ፋይዳ እንዳለው ማሳያ ነው፡፡

የሚተከሉት ችግኞች ኢኮኖሚውን የሚደግፉ በመሆናቸው የዘንድሮ የአረንጓዴ ዐሻራ መርሃ ግብር ለየት ያደርገዋል ያሉት ዋና አፈጉባዔዋ፤ የተተከሉት ችግኞች እንዲጸድቁም ሁሉም የበኩሉን እንዲወጣ ጥሪ አድርገዋል፡፡

የአዲስ ከተማ ክፍለ ከተማ ዋና ሥራ አስፈጻሚ ወይዘሮ ሽታዬ መሐመድ በበኩላቸው ባለፉት ዓመታት አመርቂ ለውጥ ከታዩባቸውና የህዝቦች አንድነት ከተስተዋለባቸው ዐቢይ ጉዳዮች መካከል አንዱ የአረንጓዴ ዐሻራ ነው ብለዋል፡፡

ዋና ሥራ አስፈጻሚዋ አክለውም ከመትከል ባሻገር መንከባከብና ለፍሬ ማብቃት ያስፈልጋል ብለዋል፡፡

በክፍለ ከተማው የተተከሉት ችግኞች ጸድቀው ለፍሬ የሚበቁበትን የቅድመ ዝግጅት ሥራዎች በጥራት ሲሰራ ቆይቷል ያሉት ዋና ሥራ አስፈጻሚዋ፤ በክፍለ ከተማው ከ650 ሺህ በላይ ችግኞች እንደሚተከሉ ተናግረዋል፡፡



በተመሳሳይ "የወል እውነታችንን ለማረጋገጥ የአረንጓዴ ዐሻራችንን በአንድነት እናኖራለን" በሚል መሪ ሃሳብ የየካ ክላስተር 2ኛ ዙር የብልጽግና ፓርቲ ሠልጣኝ አመራሮች ፈረንሳይ በሚገኘው በአቦ ቤተክርስቲያን አቅራቢያ የችግኝ ተከላ መርሀ ግብር አከናውነዋል።

በመርሀ ግብሩ ላይ ንግግር ያደረጉት የየካ ክፍለ ከተማ ዋና ሥራ አስፈፃሚ አቶ ሞገስ አባተ እንደጠቆሙት፤ የጋራ አስተሳሰብ በመያዝ ወንድማማችነትንና እህትማማችነትን አጠናክረን በአንድነት ከተማችንን በመቀየር ብልፅግናዋን ለማረጋገጥ ከፍተኛ መነሳሳት ያስፈልጋል ብለዋል።

ባለፉት ቀናት በአመራሩ መካከል በርካታ ውይይቶች ሲካሄዱ መቆየታቸውን አስታውሰው የችግኝ ተከላ መርሃ ግብሩ የህብረተሰቡን መሠረታዊ ችግሮች ለመፍታት በተነቃቃንበት ወቅት የተካሄደ በመሆኑ ልዩ እንደሚያደርገው ገልጸዋል።

ነገን ዛሬ እንትከል በሚል መርሀ ቃል በከተማ ደረጃ ችግኝ መተከል ከተጀመረ ሳምንት ሆኖታል ያሉት አቶ ሞገስ ይህም የአየር ንብረት ለውጥ ተጽእኖን ለመግታት ወሳኝ ሚና ያለው ተግባር በመሆኑ ተጠናክሮ መቀጠል አለበት ብለዋል።

የየካ ክፍለ ከተማ የብልጽግና ፓርቲ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት ኃላፊ አቶ ታረቀኝ ገመቹ በበኩላቸው እንደተናገሩት፤ የችግኝ ተከላ መርሃ ግብሩን ለየት የሚያደርገው ለአራት ቀናት ሲካሄድ የቆየው የክፍለ ከተማው አመራሮች ሥልጠናውን በማጠናቀቅ በፈጠራና በፍጥነት የወል እውነቶችን በማጽናት ሁለንተናዊ ብልጽግናን ለማረጋገጥ የሚያስችል ሥልጠና በመውሰድ ብዙ ግንዛቤ በተገኘበት ማግስት በመሆኑ ነው።

በተያዘው እቅድ መሠረት በየካ በክፍለ ከተማ 1 ነጥብ 5 ሚሊዮን ችግኝ ለመትከል ታስቦ የመትከያ ጉድጓድ ዝግጅት ሲደረግ መቆየቱን ገልጸው ከተማይቱን ውብና አረንጓዴ ለማድረግ አመራሮች አሻራቸውን ማስቀመጣቸውን ጠቁመዋል።

ኃላፊው አክለውም ነጠላ እውነቶችን ወደ ጎን በመተው የወል እውነቶችን በማጽናት ሁለንተናዊ ብልጽግናን ለማረጋገጥ ሁሉም በየድርሻው በመትጋት ስኬታማ ሥራዎችን መስራት ይገባል ብለዋል።

# ሕዝበ ሙስሊሙ በዓሉን ኃይማኖታዊ እሴቱን በጠበቀ መልኩ ሊያከብረው ይገባል

**አማን ረሺድ**

አዲስ አበባ፡- ህዝበ ሙስሊሙ አቅመ ደካሞችንና የተቸገሩትን በመርዳት የበዓሉን ኃይማኖታዊ እሴት በጠበቀ መልኩ ሊያከብረው እንደሚገባ የአዲስ አበባ ከተማ እስልምና ጉዳዮች ከፍተኛ ምክር ቤት ገለጸ፡፡

ምክር ቤቱ በትናትናው ዕለት የ1444ኛው የኢድ አል አድሃ (አረፋ) በዓልን በማስመልከት በከተማውና በመላው ዓለም ለሚገኙ የእስልምና እምነት ተከታዮች የእንኳን አደረሳችሁ መልዕክት አስተላልፏል፡፡

የአዲስ አበባ ከተማ እስልምና ጉዳዮች ከፍተኛ ምክር ቤት ፕሬዚዳንት ሼክ ሱልጣን አማን ባስተላለፉት መልዕክት፤ በእድሳት ምክንያት ያለፉትን የኢድ ሰላቶች ሳያስተናግድ የቆየው የአዲስ አበባ ስቴዲየም የዘንድሮውን የ1444ኛው የኢድ –አል አደሃ (አረፋ) ሰላት እንደሚያስተናግድ ገልጸዋል፡፡

እስልምና ሰላም መሆኑን አንስተው፤ ሙስሊሙ ኅብረተሰብ የሀገርን ሰላም ለማረጋገጥ የበኩሉን ሚና መወጣት አለበት ብለዋል።

የአዲስ አበባ ከተማ እስልምና ጉዳዮች ከፍተኛ ምክር ቤት ዋና ጸሃፊ ሼህ ሁሴን በሽር በበኩላቸው እንደገለጹት፤ ሕዝበ ሙስሊሙ በዓሉን ሲያከብር የእስልምና እምነት እሴት በሚያዘው መሠረት በፍቅር፣ በመከባበርና በመቻቻል መሆን እንዳለበት አሳስበዋል።

ኢትዮጵያ ባለችበት አስቸጋሪ ሁኔታ ሙስሊሙ ማህበረሰብ የእምነቱ መገለጫ የሆነውን ሰላም በማስቀደም ኃይማኖታዊ እሴቱን በመከተል ዜጋዊ ግዴታውን በመወጣት ለሰላሟና ለዕድገቷ መስራት እንደሚገባው ሼህ



ሼክ ሱልጣን አማን

ሁሴን አስረድተዋል፡፡

ከሶላት በኋላ የሚታረድ ዕርድ (ኡዱሁያ) ከጎረቤቱ ጋር በመሆን ለወላጅ አልባ ሕጻናት፣ ለአዛውንቶችና ለተቸገሩ ዜጎች ያላቸውን በማካፈል እንዲያከብሩ አደራ ብለዋል።

በዓሉም ያለው ለሌለው በማካፈል የሚከበር መሆኑን የገለጹት ሼህ ሁሴን፤ ሁሉም ሕዝበ ሙስሊም የእምነቱ እሴት በሚያዘው መሠረት ያለውን በማካፈል በሠላምና በመቻቻል በዓሉን እንዲያሳልፉ ጥሪ አቅርበዋል።

ኢማሞችና ኡስታዞች ባሉበት ሁሉ ስለ ሠላም መምከር እንዳለባቸውም አሳስበው፤ የ1444ኛው የኢድ አል አድሃ (አረፋ) በዓል የሰላምና የደስታ እንዲሆን ተመኝተዋል፡፡

# “ኢትዮጵያ ከምንም ነገር...

ከ1ኛው ገጽ የዞረ

ልዩ ማንነት ቢኖረንም፣ የተለያየ ቋንቋ ብንናገርም፣ የተለያየ ሃይማኖት ብንከተልም፣ ኢትዮጵያ ሲባል አንድ እንሁን ብለዋል፡፡

ይህ መንደር ይህ ሠፈር የእኔ ነው ማለትን ትተን፣ ኢትዮጵያ የእኛ ናት የምንል ዜጎች እንድንሆን አደራ እላለሁ ያሉት ጠቅላይ ሚኒስትሩ፤ ሁሉንም አካባቢ ለሁላችንም እንዲበቃ አድርገን ልናለማው፣ ልናበለጽገው እንችላለን፡፡ ከነካነው ያልነካነው ሀብታችን ይበልጣል፤ ከሠራነው ያልሠራነው ይበዛል ብለዋል፡፡

ልጆቿ ተደማምጠው እና ተከባብረው፣ በሰላም እና በፍቅር የሚኖሩባትን ሀገር፣ በጋራ እንድንገነባ ሙስሊሞችን ብቻ ሳይሆን፣ የሁሉንም እምነት ተከታዮች በአክብሮት የሚጠይቁ መሆኑን አመልክተው፤ ኢትዮጵያ ከምንም ነገር በላይ ዛሬ የምትፈልገው፣ መከባበርን እና መፋቀርን መሆኑን አስገንዝበዋል፡፡

ከዘመናት በፊት ነቢዩ ኢብራሂም ስለ እምነታቸው እንደተፈተኑት ሁሉ፣ እኛም ዛሬ ስለ ሀገራችን ስንል በፈተና ላይ ነን፡፡ ያሉት ጠቅላይ ሚኒስትር ዶክተር ዐቢይ፤ ሰላምን ለማረጋገጥ፣ ከድህነት ለመውጣት፣ ኢኮኖሚያችንን ለማሳደግ፣ ሕዝባችንን ለማበልጸግ ትግል ላይ ነን፡፡ ተጋጭተን ሳይሆን ተነጋግረን፤ ተሻምተን ሳይሆን ተካፍለን፤ ተገፋፍተን ሳይሆን ተጋግዘን፤ ለሀገራችን ከሠራን፣ ፈተናችንን ያለምንም ጥርጥር በድል እንወጣዋለን ነው ያሉት፡፡

እንደ ጠቅላይ ሚኒስትሩ ገለጻ፤ ሀገራችን፣ በተለያዩ ጊዜዎች የተለያዩ ችግሮች ገጥመዋት ያውቃሉ። የሚታለፉ የማይመስሉ ፈተናዎች በየወቅቱ ቢደቀኑባትም፣ ችግሮቹንና ፈተናዎቹን ተራ በተራ አልፋ፣ ወደ ፊት በመጓዝ ላይ ነች፡፡ መከራው በበዛ ጊዜም፣ ዜጎቿ የመጨረሻውን መሥዋዕትነት ለመክፈል ወደ ኋላ አላሉም፡፡ ንብረታቸውን ብቻ ሳይሆን፣ ሕይወታቸውን ለመስጠት አላቅማሙም። ኢትዮጵያን እዚህ ያደረሷት፣ ልጆቻቸውን ጭምር የከፈሉ ልጆቿ መሆናቸውን ሁሌም ሲዘከር የሚኖር ደማቅ ታሪካችን ነው፡፡ ኢትዮጵያውያን ራሳቸውንም መሥዋዕት ያደርጋሉ፡፡ የሚወዱትንም ነገር ለሀገራቸው ሲሉ ይሠዋሉ፡፡ ዛሬ፣ በታላቁ የመሥዋዕትነት በዓል ላይ ቆመን፣ ሁለቱንም በክብር እናስታውሳለን፡፡

ሀገር ሀገር የምትሆነው ጊዜያቸውን፣ ጉልበታቸውን፣ ዕውቀታቸውንና ከፍም ሲል ሕይወታቸውን ለመሥዋዕትነት የሚያቀርቡ ብዙ ልጆች ማፍራት ስትችል መሆኑን ገልጻው፤ አንዱ ለሌላው መሞት፤ አንዱ ለሌላው መስጠት፤ አንዱ ለሌላው ማካፈል፤ አንዱ ለሌላው ሲል መሥዋዕትነትን መክፈል ነው የዓለምን ሥልጣኔ በጽኑ መሠረት ላይ ያቆመው ነው ያሉት፡፡

ጥላቻ፣ ግጭት፣ መከፋፈልና መገፋፋት መሥዋዕትነት ባለበት ቦታ አይኖሩም ያሉት ጠቅላይ ሚኒስትሩ፤ እነዚህ የስግብግብነት ውጤቶች ናቸው፡፡ እንዲህ ዓይነቱ ታላቅ በመሥዋዕትነት የተሞላ ፍቅር በሚከበርበት በዓል፣ የትም ይሁን የት፣ ጥላቻን መስበክ ሐራም ነው፡፡ መለያየትንና መገፋፋትን መስበክ ነውር ነው፡፡ ኢትዮጵያ ከምንም ነገር በላይ አሁን የምትፈልገው ፍቅርን እና የሕዝቦቿን አንድነት መሆኑን በመልዕክታቸው አስፍረዋል፡፡

# ርዕሰ አንቀፅ

## የኢድ አልአድሃ (አረፋ) በዓልን የተቸገሩ ወገኖችን በማሰብ እናክብር!

የአረፋ በዓል በሂጅራ ዘመን አቆጣጠር በ12ኛው ወር በ10ኛው ቀን የሚከበር በዓል ነው፡፡ የአረፋ በዓል ሁለት ምክንያቶችን ከግምት ውስጥ በማስገባት ተከብሮ ይውላል፡፡ አንደኛው ነብዩ ኢብራሂም (ዐ.ሰ) አንድያ ልጃቸውን እስማኤልን እንዲሰዉ ከፈጣሪያቸው የወረደላቸውን ትዕዛዝ ለመፈጸም ያሳዩትን ቁርጠኝነት ለመዘከር የሚታሰብ ሲሆን በሌላ መልኩ ደግሞ የእስልምና እምነት እንደሚያስተምረው ዐረፋ የሚለው ቃል በዐረብኛ «አወቀ» እንደማለት ነው፡፡ ይህም የራሱ የሆነ ታሪክ አለው፡፡

አዳምና ሔዋን ወይንም አደምና ሃዋ ከጀነት ወደ ምድር ከወረዱ በኋላ ለብዙ ዘመናት ተጠፋፍተው ነበር፡፡ ለረጅም ጊዜ ሲፈላለጉ ከቆዩ በኋላ በዚህ ዕለት በሳዑዲ ዐረቢያ ባለው የአረፋ ተራራ ላይ ተገናኙ፡፡ እዚያም «ዐረፍቱከ...ዐረፍቱኪ» ተባባሉ፡፡«አወቅኩህ! አወቅኩሽ» ማለታቸው ነው፡፡ ይህንን ታሪክ ለመዘከር ሲባል ነው የአረፋን በዓል ማክበር የተጀመረው፤ ይህ በዙልሂጃ ዘጠነኛው ቀን የሚከበር በዓል ነው።

አረፋ የመረዳዳረት በዓል ነው፡፡ ማንኛውም አቅሙ የቻለ አማኝ ከሚያርደው እንስሳ 1/3ኛውን ለድሃ የማከፋፈል ግዴታ ያለበትና ሁሉም በዓሉን በእኩልነት የሚያሳልፍበት በዓል ነው፡፡ ሙስሊም ዕለቱን አቅሙ በፈቀደ ሁኔታ እንስሳት በማረድ ከቤተሰብና ዘመድ አዝማድ ጋር ያሳልፈዋል። ለኢድ አል አድሃ(አረፋ) አንድ ሰው ከሚያርደው ከብት ሲሶውን ብቻ ለራሱ እንዲጠቀም ነው ኃይማኖታዊ ግዴታው የሚያዘው። ከተቀረው ሲሶው ለዘመድ አዝማድ፣ሲሶው ደግሞ አቅም ለሌለው ደሃ እንዲከፋፈል እስልምና ያዛል።

ከዚህ የተነሳም የአረፋ በዓል በእስልምና ኃይማኖት ተከታዮች ዘንድ ታላቅ በዓል ነው። በዓሉን ከኃይማኖታዊ ትሩፋቱ ባለፈ የቤተሰባዊ እሴት ማጠናከሪያ እና መሰባሰቢያ በዓል አድርገው ስለሚያዩት በተለያየ ምክንያት ተለያይተው የሚኖሩ ቤተሰቦች ይሰባሰቡበታል፡፡ ሕፃናት በበዓል አልባሳት ደምቀው ስጦታ ለጎረቤቶቻቸው በማበርከት ያሳልፋሉ፡፡ እናቶች መኖሪያ ቤቶቻቸውን ያሳምራሉ፤ተወዳጅ እና ጣፋጭ ምግቦች በተለየ ሁኔታ ለቤተሰቡ ያዘጋጃሉ፡፡

በኢትዮጵያ የእስልምና ኃይማኖት ተከታዮች ዘንድም አማኞች በጠዋት ተነስተው፣ በኃይማኖታዊ ንፁህ አልባሳት ደምቀው እና አምረው ወደ መስገጃ አደባባይ እና ወደ መስጂዶች በረድፍ ሲያመሩ ሲታዩ የጎላ ውበት፣ አስደማሚ አንድነት ይንፀባረቃል። ሶላታቸውን በጋራ ሰግደው እና በአንድ ዓይነት መንፈሳዊ ቋንቋ ፈጣሪያቸውን አመስግነው፣እርስ በእርሳቸው የመልካም ምኞት መግለጫ ተለዋውጠው፣ ከልብ የመነጨ ፈገግታ ተመጋግበው፣ «አብረን ወደ ቤት እንግባ፣ አብረን እንዋል እያሉ» ሲገባበዙ፣ በአክብሮት ሲጠራሩ ማየትና ማዳመጥ የተለመደ ነው።

በተለይም ኢትዮጵያን ለየት የሚያደርጋት እስላምና ክርስቲያኑ በመጠራራት በዓሉን በጋራ የሚያከብሩባት ድንቅ ሀገር መሆኗ ነው፡፡ ኢትዮጵያ ለእስልምና ኃይማኖት መስፋፋት ከፍተኛ አስተዋጽኦ ያበረከተችና በእንግዳ ተቀባይነቷም ዝንተዓለም ስሟ የሚነሳ ሀገር ናት፡፡ ይህን መነሻ በማድረግም ሃበሾችን መሠረት ያደረጉ ከ23 በላይ የቁርአን አንቀጾች፣ በሃበሾች ቋንቋም ከ30 በላይ የቁርአን አንቀጾች እንዲወርዱ፤በተጨማሪም በነብዩ መሐመድ /ሰዐወ/ ስለ ሃበሾች ክብር ከ27 ያላነሱ ነብያዊ ሃዲሶች እንዲነገሩ ምክንያት እንደሆኑ ይነገራል።

በአጠቃላይ ኢድአልአደሃ (አረፋ) የአብሮነት እና የመረዳዳት በዓል ነው፡፤ በተለይም በኢትዮጵያ የኢድ አልአድሃ (አረፋ) አከባበር ለየት የሚልባቸው እሴቶች አሉ፡፡ ኢትዮጵያ ከጥንት ጀምሮ የተለያዩ እምነቶችን በጸጋ የተቀበለችና የተለያዩ እምነት ተከታዮችም ተከባብረው የሚኖሩባት የተለየች ሀገር ነች፡፡ አረፋን በመሳሰሉ የበዓል ወቅቶች ደግሞ ሙስሊሙ ማኅበረሰብ የክርስትና እምነት ተከታዮች የሆኑ ጎረቤቶችን በመጥራት በዓሉን በጋራ ማሳለፍ የተለመደ ነው፡፡ ይህ አንዱ ኢትዮጵያዊ ዕሴት ሲሆን ለዘመናትም ሲወርድ ሲዋረድ ዛሬ ላይ የደረሰ ድንቅ መገለጫችን ነው፡፡

ከአረፋ በዓል ዕሴቶች አንዱና ዋነኛው የተቸገሩ ወገኖችን መርዳት ነው፡፡ የእስልምና እምነት በአረፋ ወቅት ድሆችን ከሚያስብበትና በዓሉንም በደስታ እንዲያሳልፉ በአማኞች ላይ ግዴታ ከጣለባቸው ትዕዛዞች አንዱ ከሚታረዱ እንስሳት 1/3ኛውን ላጡና ለተቸገሩ ወጎኖች የሚሰጥ መሆኑ ነው፡፡ ይህ ደግሞ በችግር ውስጥ የሚገኙ ወገኖች በዓሉን በደስታ እንዲያሳልፉ የሚያስችልና የመረዳዳት እሴትንም የሚጨምር ነው፡፡

በተለይም በአሁኑ ወቅት በሰውሰራሽና ተፈጥሯዊ ምክንያቶች የተፈናቀሉ በርካታ ወገኖች በሀገራችን የተለያዩ አካባቢዎች ይገኛሉ፡፡ ስለዚህም እነዚህን ወገኖችን አስቦ መዋል በአረፋ ወቅት የሚከወን ተግባር ሊሆን ይገባል!


# አዲስ ዘመን

ግንቦት 30 ቀን 1933 ዓ.ም ተቋቋመ

**የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ዋና ስራ አስፈጻሚ**
ስልክ ቁጥር - 011-126-42-22
ኢሜል ፡- epa@press.et

**ዋና አዘጋጅ**
አንተነህ ኃ/ብርሃን ወ/መድህን

**አድራሻ**
ንፋስ ስልክ ላፍቶ ክ/ከ
ወረዳ 06
የቤት ቁጥር 319
ኢሜይል - anteneh.hailebirhan@press.et
ስልክ ቁጥር - 011-1-26-42-40

**የገበያ ልማትና ፕሮሞሽን ዘርፍ**
ኢሜይል - etpresspromotion@gmail.com
ስልክ - 011-126-43-41
ፋክስ - 011-811-13-15
የዝግጅት ክፍል ፋክስ - 251-011-1-56-98-62

**የአዲስ ዘመን ማኔጂንግ ኤዲተር**
ወንድወሰን ሽመልስ ታደሰ
ስልክ፡- 011 126 4200
Email:- wendweson.shimelis@press.et
wendwesonshimelis@gmail.com

**የአዲስ ዘመን ምክትል ዋና አዘጋጆች**
• ወርቁ ማሩ
• ኃይሉ ሣህለድንግል
• እስማኤል አረቦ
• ቦጋለ አበበ

**የማስታወቂያ መቀበያ ክፍል**
ስልክ ቁጥር - 011-156-98-73
ፋክስ - 011-126-58-12
ቴሌግራም - 097- 608-47-07 - Press

**የማስታወቂያ ሽያጭ ማስተባበሪያ**
ስልክ - 011-1-26-43-39

**ማከፋፈያ** ፡- ስልክ ቁጥር - 011-157-02-70


## «ዓለም የተራመደችበት የዕድገት ደረጃ ሁሉ የመሥዋዕትነት ውጤት ነው»

\- ጠቅላይ ሚኒስትር ዶክተር ዐቢይ አሕመድ

**(የኢፌዴሪ ጠቅላይ ሚኒስትር ዶክተር ዐቢይ አሕመድ የ1444ኛው የዒድ አል አድሃ በዓልን ምክንያት በማድረግ ያስተላለፉት መልዕክት ሙሉቃል)**

ውድ ኢትዮጵያውያን ሙስሊም ወገኖቼ!

እንኳን ለታላቁ የዒድ አል አድሃ በዓል አደረሳችሁ!

ዒድ አል አድሃ፣ አረፋ ሙስሊሞች በታላቅ ክብር እና ፍቅር የሚያከብሩት፣ መሥዋዕትነትን የሚዘክር በዓል ነው። በዓሉ ከአምስቱ የእስልምና መሠረቶች መካከል አንዱ የሆነውና ማንኛውም ሙስሊም የገንዘብና የጉልበት ዐቅሙ እስከፈቀደ ድረስ በሕይወት ዘመኑ ቢያንስ አንዴ ወደ መካ በመጓዝ እንዲያከናውነው የሚጠበቅበት የሐጅ ሥርዓት የሚካሄድበትና የሚጠቃለልበት ታላቅ ምዕራፍ ነው።

አረፋ፣ የሰው ልጅ ለፈጣሪው እና ለእምነቱ ሲል፣ መከራ ለመቀበል፣ ካስፈለገም ለመሠዋት ያለውን ፈቃደኛነት የምናስታውስበት፣ የምናከብርበት፣ የምንዘክርበት ልዩ ቀን ነው። አላህ (ሱብሀነሁ ወተአላ)፣ ነቢዩ ኢብራሂምን፣ ልጅህን መሥዋዕት አድርግልኝ ብሎ ሲያዛቸው፣ ነቢዩ ኢብራሂም፣ የአባት ኀዘን አላሸነፋቸውም፤ የልጅ ፍቅር አላጓጓቸውም፣ የቤታቸው መፍረስ አላሳሰባቸውም፤ የትኛውም ጉዳይ ከፈጣሪ ትእዛዝ አይበልጥምና፣ አንድዬ ልጃቸውን እስማኤልን መሥዋዕት ለማድረግ ተነሡ። ልጃቸው እስማኤልም ለመሠዋት ዝግጁ ነበር። ዒድ አል አድሃ የመሥዋዕት በዓል ነው የሚባለውም ለዚያ ነው።

ኢትዮጵያውያን፣ ከዚህ ጥንታዊ ኢስላማዊ ታሪክ ሁለት ታላላቅ ቁም ነገሮችን ተምረናል። ወርቅ በእሳት እንደሚፈተነው ሁሉ፣ ሰዎችም በአስቸጋሪ ጊዜዎች ይፈተናሉ። እንደ እስማኤል ያለውን ነገር ሁሉ ሰጥቶ ለመሠዋት የቆረጠ ፈተናውን አልፎ፣ ትልቅ ታሪክ ጽፎ፣ እንደ ዒድ አል አድሃ ያለውን መታሰቢያ አትርፎ፣ ከዘመን ዘመን እየታወሰ ይኖራል። መሥዋዕትነትን ያልደፈረ፣ ከክብር ርቆ፣ ከታሪክ ተፍቆ እንደ አቧራ ይበናል።

ሁለተኛው ትምህርት፣ ታላቅ ግብ ላይ የሚደረሰው የሚወዱትን እንኳን ሳይቀር አሳልፎ በመስጠት መሆኑን ነው። ነቢዩ ኢብራሂም ለእስማኤል የማይለካ ፍቅር ነበራቸው። ትልቁ ግባቸው ግን የፈጣሪያቸውን የአላህን ፈቃድ መፈጸም ነው። ይሄንን ግባቸውን ለማሳካት ሲሉ በምድር ላይ ትልቁ ሀብታቸው አድርገው የሚቆጥሩትን እስማኤልን ለመሠዋት ቆረጡ።

የመሥዋዕትነት በዓል በሚከበርበት በዚህ ልዩ ቀን፣ ኢትዮጵያውያን ‹እንኳን አደረሳችሁ› እንዲባባሉ ብቻ ሳይሆን፣ ሁለቱንም ቁም ነገሮች ልብ እንዲሉ አደራ እላለሁ። ለትልቅ ጉዳይ መፈተን፣ ለብርቱ ጉዳይ መሥዋዕት ለመሆን መዘጋጀት ታላላቅ ሰዎች የሚፈጽሙትና ታሪክ የሠሩበት ዕሴት ነው። ለታላቅ ግብ ሲባል የሚወዱትን ሳይቀር ለመሠዋት መቁረጥም ዓለምን የሚለውጥ ታሪክ የሚሠሩ ሁሉ የሚፈጽሙት ነው።

ሀገራችን፣ በተለያዩ ጊዜዎች የተለያዩ ችግሮች ገጥመዋት ያውቃሉ። የሚታለፉ የማይመስሉ ፈተናዎች በየወቅቱ ቢደቀኑባትም፣ ችግሮቹንና ፈተናዎቹን ተራ በተራ አልፋ፣ ወደ ፊት በመጓዝ ላይ ነች። መከራው በበዛ ጊዜም፣ ዜጎቿ የመጨረሻውን መሥዋዕትነት ለመክፈል ወደ ኋላ አላሉም። ንብረታቸውን ብቻ ሳይሆን፣ ሕይወታቸውን ለመስጠት አላቅማሙም። ኢትዮጵያን እዚህ ያደረሷት፣ ልጆቻቸውን ጭምር የከፈሉ ልጆቿ መሆናቸውን ሁሌም ሲዘከር የሚኖር ደማቅ ታሪካችን ነው። ኢትዮጵያውያን ራሳቸውንም መሥዋዕት ያደርጋሉ። የሚወዱትንም ነገር ለሀገራቸው ሲሉ ይሠዋሉ።

ዛሬ፣ በታላቁ የመሥዋዕትነት በዓል ላይ ቆመን፣ ሁለቱንም በክብር እናስታውሳለን።

በድጋሚ፣ እንኳን ለዒድ አል አድሃ/ አረፋ በዓል አደረሳችሁ!

ያለ መሥዋዕትነት የጸና ሀገር፣ የበለጸገ ሕዝብ በዓለም ላይ የለም። ዓለም የተራመደችበት የዕድገት ደረጃ ሁሉ የመሥዋዕትነት ውጤት ነው። አሁን የደረስንበት ደረጃ ላይ እንድንደርስ ብዙ ወገኖች ራሳቸውንም የሚወዱትንም ነገር መሥዋዕት አድርገዋል። ከመኖር ለሚበልጥ ግብ ሲሉ ሕይወትን ያህል ውድ ነገር ከፍለዋል። ሀገር ሀገር የምትሆነው ጊዜያቸውን፣ ጉልበታቸውን፣ ዕውቀታቸውንና ከፍም ሲል ሕይወታቸውን ለመሥዋዕትነት የሚያቀርቡ ብዙ ልጆች ማፍራት ስትችል ነው። አንዱ ለሌላው መሞት፤ አንዱ ለሌላው መስጠት፤ አንዱ ለሌላው ማካፈል፤ አንዱ ለሌላው ሲል መሥዋዕትነትን መክፈል ነው የዓለምን ሥልጣኔ በጽኑ መሠረት ላይ ያቆመው።

ጥላቻ፣ ግጭት፣ መከፋፈልና መገፋፋት መሥዋዕትነት ባለበት ቦታ አይኖሩም። እነዚህ የስግብግብነት ውጤቶች ናቸው። እንዲህ ዓይነቱ ታላቅ በመሥዋዕትነት የተሞላ ፍቅር በሚከበርበት በዓል፣ የትም ይሁን የት፣ ጥላቻን መስበክ ሐራም ነው። መለያየትንና መገፋፋትን መስበክ ነውር ነው። ኢትዮጵያ ከምንም ነገር በላይ አሁን የምትፈልገው ፍቅርን እና የሕዝቦቿን አንድነት ነው።

አደምና ሐዋ ከገነት ከተባረሩ በኋላ በተገናኙበት የአረፋ ኮረብታ ከመላው ዓለም የተሰባሰቡ ሙስሊሞች የዒድ አል አድሃን በዓል በአንድነት ያከብራሉ። ምንጫቸው የተለያየ፣ ቀለማቸው የተለያየ፣ ዜግነታቸው የተለያየ፣ ማንነታቸው የተለያየ ቢሆንም፣ ሁሉም የሚያስቡት ሙስሊም መሆናቸውን ብቻ ነው። የተለያዩበትን ረስተው የተገናኙበትን፣ የተሣሠሩበትን እያሰቡ፣ አንድ ይሆናሉ። እኛም ለምንለያይበት ሳይሆን ለምንገናኝበት፣ ለምንገፋፋበት ሳይሆን ለምንሳሳብበት፣ ለምንሻኮትበት ሳይሆን ለምንተባበርበት ቅድሚያ ሰጥተን፣ አንድ ትልቅ ሕዝብ እንሁን። ከልዩ ልዩ ቦታ ብንመጣም፣ ልዩ ልዩ ማንነት ቢኖረንም፣ የተለያየ ቋንቋ ብንናገርም፣ የተለያየ ሃይማኖት ብንከተልም፣ ኢትዮጵያ ሲባል አንድ እንሁን።

ይህ መንደር ይህ ሠፈር የእኔ ነው ማለትን ትተው፣ ኢትዮጵያ የእኛ ናት የምንል ዜጎች እንድንሆን አደራ እላለሁ። ሁሉንም አካባቢ ለሁላችንም እንዲበቃ አድርገን ልናለማው፣ ልናበለጽገው እንችላለን። ከነካነው ያልነካነው ሀብታችን ይበልጣል፤ ከሠራነው ያልሠራነው ይበዛል።

ልጆቿ ተደማምጠው እና ተከባብረው፣ በሰላም እና በፍቅር የሚኖሩባትን ሀገር፣ በጋራ እንድንገነባ ሙስሊሞችን ብቻ ሳይሆን፣ የሁሉንም እምነት ተከታዮች በአክብሮት እጠይቃለሁ። ኢትዮጵያ ከምንም ነገር በላይ ዛሬ የምትፈልገው፣ መከባበርን እና መፋቀርን ነው። አንዳችን ሌላችንን እንድንሠዋ ሳይሆን፣ አንዳችን ለሌላችን ብለን እንድንሠዋ ነው። አንዳችን የሌላውን ሞት እንድንሞት ነው። ከዘመናት በፊት ነቢዩ ኢብራሂም ስለ እምነታቸው እንደተፈተኑት ሁሉ፣ እኛም ዛሬ ስለ ሀገራችን ስንል በፈተና ላይ ነን። ሰላምን ለማረጋገጥ፣ ከድህነት ለመውጣት፣ ኢኮኖሚያችንን ለማሳደግ፣ ሕዝባችንን ለማበልጸግ ትግል ላይ ነን። ተጋጭተን ሳይሆን ተነጋግረን፤ ተሻምተን ሳይሆን ተካፍለን፤ ተገፋፍተን ሳይሆን ተጋግዘን፤ ለሀገራችን ከሠራን፣ ፈተናችንን ያለምንም ጥርጥር በድል እንወጣዋለን። እኛ ተሠዉተን ኢትዮጵያን እናጸናለን። የነቢዩ ኢብራሂም ታሪክ ለትውልድ ሁሉ ተርፎ ሚሊዮኖችን ከመላው ዓለም ወደ አረፋ ተራራ እንደሚስበው ሁሉ፣ የእኛም ታሪክ ለትውልድ ተርፎ ሚሊዮኖችን ከመላው ዓለም ወደ ኢትዮጵያ እንደሚስባቸው አምናለሁ።

ዒድ ሙባረክ!

መልካም የዒድ አል አድሃ በዓል!

ኢትዮጵያ በልጆቿ ጥረት ታፍራና ተከብራ ለዘለዓለም ትኑር

ፈጣሪ ኢትዮጵያንና ሕዝቦቿን ይባርክ!

ሰኔ 20 ቀን 2015 ዓ.ም

## ተጠየቅ

# ‹‹ የከተማ ቦታ ኪራይ እና የከተማ ቤት ግብር ከ1937 ዓ.ም ጀምሮ የነበረ የግብር ዓይነት ነው ››



**- የአዲስ አበባ ገቢዎች ቢሮ የታክስ ጉዳዮች ዘርፍ ምክትል የቢሮ ኃላፊ- አቶ ዘገየ በላይነህ**

ምህረት ሞገስ

**በቅርቡ ማሻሻያ ተደርጎ የቤት ባለይዞታዎች እንዲከፍሉ የተደረገውን ግብር የማኅበረሰቡን ኑሮ ያላማከለ፤ ኅብረተሰቡ እንዲወያይ ሳይደረግ በአቅጣጫ በግዳጅ እየተፈፀመ ያለ፤ በተለይ የጋራ መኖሪያ ቤቶች ቆጥበው ያገኙት ቤት ላይ እንዲከፍሉ መደረጉ፤ ድሃውን የሚጎዳ ነው የሚሉ ሰፋ ያሉ ወቀሳዎች እየተሰነዘሩ ይገኛሉ። አሠራሩ ከክፍለ ከተማ ክፍለ ከተማ የተለያየ ነው የሚሉ እና ሌሎችም ተያያዥ ሃሳቦች እየተሰነዘሩ ናቸው። እነዚህ እና ሌሎችም ተያያዥ ጥያቄዎችን በመያዝ የከተማ ቦታ ኪራይ እና የከተማ ቤት ግብር የአዲስ አበባ ገቢዎች ቢሮ የታክስ ጉዳዮች ዘርፍ ምክትል የቢሮ ኃላፊ አቶ ዘገየ በላይነህን አነጋግረን እንደሚከተለው አቅርበነዋል።**

**አዲስ ዘመን፡-የንብረት ግብር ይከፈል መባሉ በችኮላ የተወሰነ፣ ኅብረተሰቡ ያልተወያየበት እና የኅብረተሰቡን አቅም ያላገናዘበ ነው የሚሉ እና ሌሎችም ቅሬታዎች በመሰማት ላይ ናቸው። እርሶ ምን ይላሉ?**

**አቶ ዘገየ፡-** በቅድሚያ ይህ ግብር አዲስ እንዳልሆነ እና ከ1937 ዓ.ም ከንጉሡ ዘመነ መንግሥት ጀምሮ የነበረ ነው ። በደርግ ጊዜም በ1968 ዓ.ም በአዋጅ ተሻሽሎ አዋጅ ቁጥር 80/1968 በሚል አዋጅ እስከ ዛሬ እየተተገበረ ነው። ወቅታዊ ከማድረግ በስተቀር አዲስ አይደለም።

ከስያሜ አንፃርም መስተካከል ያለበትነገር አለ። አሁን እየተተገበረ ያለው የንብረት ግብር ሳይሆን፤ የከተማ ቦታ ኪራይ እና የከተማ ቤት ግብር ነው። ይህ አዋጅ ደንብም አለው። አዋጁን ለማስተግበር ደንብ ቁጥር 36/1968 በዚያው ጊዜ የወጣ ነው። ስለዚህ በጣም የቆየ እንጂ እንደአዲስ የታወጀ አዋጅ አይደለም።

በችኮላ በአቅጣጫ በግዳጅ እንዲፈፀም የተወሰነ ነው በሚል ነገሮችን አጠቃሎ ማስቀመጡ ተገቢ አይደለም። ይህ በጥናት ላይ የተመረኮዘ፤ ግብሩም ወቅታዊ የከተማ ቦታ ኪራይ እና የከተማ ቤት ዋጋን መሠረት ያደረገ ነው።

በካሬ ስንት እንደሆነ ጥናት ላይ በመመሥረት የተዘጋጀ ነው። ቀድሞ ግን እንደገለፅኩት አዋጁ በ1968 የተዘጋጀ እና የቆየ ነው ፤ አከፋፈሉ ላይ ግን ትልቅ ችግር ነበር። ለምሳሌ የ2014 ዓ.ምን አከፋፈል ማየት ይቻላል።

በ2014 ዓ.ም 182 ሺህ ሰዎች ይህን ግብር የከፈሉ ነበር፤ ይህን ግብር ከከፈሉ ሰዎች መካከል 2ሺህ 578 ሰዎች የሚከፍሉት አንድ ብር አካባቢ ብቻ ነበር። 23 ሺ ሰው ከ10 ብር ያነሰ የሚከፍል ነው፤ ወደ 84ሺህ ሰው ከ11 ብር እስከ 100 ብር ከፍሏል።

በአዋጁ በግልፅ እንደተመላከተው በየጊዜው ወቅታዊ ማድረግ ያስፈልግ ነበር። ነገር ግን በአንድም ሆነ በሌላ ወቅታዊ ሳይደረግ ቆይቷል። አሁን ግን የከተማ አስተዳደሩ እያቀረበ ካለው የመሠረተ ልማት እና በከተማ ውስጥ ቤቶች በካሬ የሚከራዩበትን ግምት ውስጥ በማስገባት ጥናት ተደርጎ ወደ ሥራ ተገብቷል።

‹‹ኅብረተሰቡን ማወያየት ያስፈልግ ነበር›› ለሚለው በየመገናኛ ብዙኃኑ ኅብረተሰቡ ግራ ለሚጋባባቸው ጉዳዮች እና ከሕዝቡ ለሚነሱ ጥያቄዎች ምላሽ እየተሰጠ ነው። ይህ ብቻ አይደለም። በገቢ ቢሮ በኩል መዋቅራችን እስከ ወረዳ ድረስ አለ። ሥራው የመሬት ቢሮን፣ የግንባታ ፈቃድ እና ቁጥጥር ባለሥልጣንንም ይጨምራል። እነዚህ ሁሉ ተቋማት የየራሳቸው ድርሻ አላቸው፤ በእነዚህ ሁሉ ተቋማት በኩል ለኅብረተሰቡ ግንዛቤ እየተሰጠ ነው።

የሌሎች ሀገሮችን የአፍሪካ አገሮችን ልምድ እንኳ ወስደን ስናይ ለምሳሌ የዛምቢያ ዋና ከተማ ሉሳካ 74 ነጥብ 6 በመቶ የከተማው ገቢ ከዚህ ዓይነት ግብር የሚሰበሰብ ነው። ይህ የ2021 መረጃ ነው። የጎረቤታችን ኬንያ የዋና ከተማ የናይሮቢ ገቢ 20 በመቶ የሚሰበሰበው ከእንደዚህ ዓይነት ግብር ነው።

የእኛ አገር ደግሞ የ2014 ዓ.ም ከላይ እንደጠቀስኩት የተሰበሰበው የከተማዋን በጀት ከአንድ በመቶ ያነሰ እንዲያውም ወደ ዜሮ ነጥብ ዜሮ ስምንት አካባቢ የተጠጋ ነው። ስለዚህ ይህንን በምናይበት ጊዜ ወቅታዊ ማድረጉ የግድ ነው። እስከ አሁን ሳይፈፀም ወደ ኋላ መቅረቱ እንጂ፤ በጊዜ ወቅታዊ እየተደረገ ቢሆን ኖሮ መንግሥት የተሻለ መሠረተ ልማትም እንዲገነባ የሚያስችል ነበር። ስለዚህ ግብሩ ይህንን ታሳቢ ያደረገ ነው። በግብታዊነት የተወሰነ አዲስ አዋጅ አይደለም።

የአከፋፈል ሁኔታውን በተመለከተ አሁን እየተከፈለ ነው። ቅርንጫፎች እና ንዑስ ቅርንጫፎች ወይም በወረዳ ደረጃ ያሉ የታክስ ማዕከላት ትንሽ የሰው መብዛት እና መጨናነቆች ቢኖርም እየተሠራ ነው። ስለዚህ ያንን ለማቃለል ሠራተኞቻችን ማልደው በመግባት እና ማታም አምሽቶ በመሥራት አገልግሎት እንዲሰጡ እያደረግን ነው።

ከሌሎች የሥራ ክፍሎችም ሰዎችን አንቀሳቅሰን የሰው ኃይል በማብዛት አገልግሎቱ እንዲሰጥ ጥረት እያደረግን ነው። በአጭር ጊዜ ውስጥ ሙሉ ሰነድ እንኳን ብንጠቀም እስከ አሁን ያልከፈሉ ሰዎች ከፍለው ወደ ሚቀጥለው አመት እንሸጋገራለን። በዚህ ዓመት የሚከፈለው መኖሪያ ቤት ከሆነ 50 በመቶ ብቻ ነው። ድርጅት ከሆነ ደግሞ 75 በመቶ ብቻ ነው። ይህ ከሆነ በአንድ ጊዜ ግብር ከፋዩ ላይ ጫና እንዳይመጣ መንግሥት አስቦ ያደረገው ነው። ይህ ጫናውን ለማቅለል የተወሰደ ከፍተኛ እርምጃ ነው። ስለዚህ ክፍያው በዚህ መልክ እየተሰበሰበ ነው።

**አዲስ ዘመን፡- ግብሩ አዲስ ባይሆንም ተመኑ ሲወጣ ካለው የኑሮ ውድነት አኳያ ምን ያህል ወቅቱን ያገናዘበ ነው? ከጋራ መኖሪያ ቤቶች ጋር አያይዘው ቢነግሩን?**

**አቶ ዘገየ፡-** የጋራ መኖሪያ ቤቶች እስከ አሁን ሳይከፍሉ የቆዩት አዋጁ ላይ እንደተመላከተው የአከፋፈሉ ሁኔታ በየጊዜው ወቅታዊ ባለመደረጉ ነው። በተጨማሪም ኅብረተሰቡ ላይ ሊፈጠር የሚችለውን ጫና ታሳቢ በማድረግ ነው። በሌላ በኩል ግን የጋራ መኖሪያ ቤቶች በብዛት አንድ ቦታ የተገነቡ ቢሆንም አንዳንዱ ዕጣ ደርሶት፣ አንዳንዱ ገዝቶ ሌላው ደግሞ ድርጅት ገዝቶለት የሚኖር ነው። ቤቶቹ ካርታ አላቸው የሚጠቀምባቸውም ግለሰብ አለ። ስለዚህ ከተማ ውስጥ ያሉ ቤቶችን ግብር የመሰብሰብ ሥልጣን የከተማ አስተዳደሩ ስለሆነ እስከ ዛሬ አልከፈልንምና ነፃ መሆን አለብን የሚለው አያስኬድም።

ነገር ግን መንግሥታችን አሁን ያለውን የኑሮ ውድነት እና የኢኮኖሚ ጫና እንዲሁም ያሉትን ነገሮች ይረዳል። በዚህ የተነሳ በዚህ ዓመት እስከ የካቲት 30 ግብር መክፈል ነበረበት። ነገር ግን የአሁኑ ግብር ተግባራዊ የሚደረገው ባልከፈሉት ላይ ብቻ ነው። እስከ አሁን ያልከፈሉትም ቢሆኑ የግብሩን 50 በመቶ ብቻ እንዲከፍሉ ተደርጓል። በመንግሥት ይህ የተደረገው የሕዝብን ጫና ለመቀነስ ነው።

የአዲስ አበባ ከተማ ገቢዎች ቢሮ የግለሰብ ግብር ከፋዮች መክፈል ያለባቸውን ግብር ይሰበስባል። ቤቱ የግለሰብ ቤት ነው። እንደምሳሌ የጋራ መኖሪያ ቤትን እንጥቀስ ከተባለ፤ የጋራ መኖሪያ ቤት በግል የሚከፈል ሲሆን፤ በልዩ ሁኔታ የተቸገረ ከሆነ እና ቤቱን የሆነ ድርጅት ገዝቶ የሠጠው እንዲሁም ምንም ዓይነት ገቢ ከሌለው ምንም ማድረግ የማይችል ሰው ቅሬታ የሚሰማባቸው ማዕከላት አሉ።

በከተማ ደረጃ የተዋቀረ ቅሬታ ሰሚ አለ። የእኛም የታክስ ማዕከል ላይ ቅሬታ የሚሰበስቡ ባለሞያዎች አሉ። በግሉ የተቸገረ ሰው ችግሩን ተናግሮ ከችግር የመውጫ መንገዶቹን በተመለከተ በተቋም ደረጃ እኛም ስላለን በዚያ መገልገል ይችላል። ነገር ግን እስከ ዛሬ ስላልከፈልን አሁንም መቀጠል አለብን የሚለው አያስኬድም።

ግለሰብ ግብር የሚከፈለው ለራሱ ነው። መንግሥት ወኪል ነው፤ ግብር ሰብስቦ በተገቢው ቦታ ላይ የሚያውል አካል ነው። ከዚህ ውጪ ግብር በመከፈሉ ተጠቃሚው መንግሥት ብቻ አይደለም። ራሱ ግብር ከፋዩም ተጠቃሚ ነው። በተከፈለው ግብር ተጠቃሚ የሚሆነው ራሱ ነው የሚባለው መሠረተ ልማት በየደጃችን እንዲስፋፋ ስለሚያስችል ነው።

የመሠረተ ልማት መስፋፋት የንብረቶቻችንን ዋጋ ይጨምረዋል። ለምሳሌ ሽያጭም ሆነ ኪራይ መሠረተ ልማት ሲስፋፋ መጨመሩ አይቀርም። እንደመሠረተ ልማት ተደራሽነት እና እንደቦታው የከተማ ቅርበት የቤት የሽያጭ ዋጋም ሆነ ኪራይ ከፍ ይላል። ስለዚህ መሠረተ ልማት በተስፋፋ ቁጥር በአንድም ሆነ በሌላ መልኩ ግለሰብ ተጠቃሚ ይሆናል። ስለዚህ ግብር መክፈል ጥቅም ያስገኛል።

በግል አሁን ከምንነጋገረው ውጪ ይሔ ችግር አለብኝ የሚል ሰው ከመጣ ልናዳምጠው ዝግጁ ነን። የጋራ መኖሪያ ቤት ላይ የልኬት ችግር አይኖርም። ነገር ግን ሌሎችም ከልኬትም ሆነ ከአከፋፈል ጋር በምንም መልኩ በአገልግሎት አሰጣጥ ላይም ቅሬታ ያላቸው ሰዎች በክፍለከተማም ሆነ በገቢዎች ቢሮ በኩል ቅሬታ ማቅረብ ይችላሉ።

**አዲስ ዘመን፡- በአብዛኛው ቅሬታዎች ተመኑ የወቅቱን የኑሮ ውድነት ያገናዘበ አይደለም የሚል ናቸው። ችግሩ ተከራዮችንም የሚነካ በመሆኑ ፍትሃዊ ነው ብለው ያምናሉ?**

**አቶ ዘገየ፡-** ከመሬት በመነሳት የተሰጠ ውሳኔ አይደለም። በተቻለ አቅም ጥናት ላይ ለመመስረት ጥረት ተደርጓል። በከተማ ደረጃ ተጠሪነቱ ለፋይናንስ ቢሮ የሆነ ፕሮጀክት ጽሕፈት ቤት የተቋቋመ ሲሆን፤ የንብረት ታክስ ማስተግበሪያ ጽሕፈት ቤት ነው። እርሱ የንብረት ግብርን ወደፊት ሥራ ላይ ስናውል የዓለም አቀፍ ሕግና ተሞክሮ ምን ይመስላል? የሀገራችን ሕጎችስ ምን ይመስላሉ? የሚለውን እያየ ይህንንም በታሳቢነት ማሻሻል ይገባል የሚለውን ያጠናው ይህ የሥራ ክፍል ነው።

በደንብ በባለሞያዎች የተደራጀ እኔን ጨምሮ በከፍተኛ አመራሮች የሚመራ እና የምናስተባብረው ነው። አሁን ተገቢ ነው የሚለው በጥናት የተመለሰ ጥያቄ በመሆኑ እዚህ ላይ ምንም ብዥታ የለም። ሕግ ቢወጣም ተግባር ላይ ሲውል አፈፃፀም ላይ ችግር ሊኖር ይችላል። ችግሮች ሲኖሩ በጋራ እየተወያየን በአስተዳደር የሚፈቱ ደግሞ አስተዳደራዊ መፍትሔዎችን እየሠጠን እንሔዳለን። በዚህ ወቅት መጠናቱ እና መተግበሩ ተገቢ ነው። ምክንያቱም ይህንን ከከተማ አስተዳደሩ ልማቶችን ከመሥራቱ አንፃር መታየት አለበት።

ወደ ኋላ ዞር ብለን ብንመለከት ባለፉት አራት ዓመታት እንኳ ኅብረተሰቡን ተጠቃሚ ያደረጉ እና የኅብረተሰቡን ኑሮ የሚያሻሽሉ ትልልቅ ፕሮጀክቶች ተሠርተዋል። የካፒታል ፕሮጀክቶችን ብናይ፣ የምገባ ማዕከላት፣ የተማሪ ምገባ፣ ድሃ ተኮር ፕሮጀክቶች ሁሉ በብዛት ከግብር ከፋዩ በሚሰበሰብ ገንዘብ የሚሠሩ ናቸው። ግብር ስንከፍል ተጠቃሚ የምንሆነው እኛው ነን። ለጊዜው ጫና ሊኖር ይችላል። ነገር ግን በመጨረሻ በጊዜ ሒደት ተጠቃሚ ኅብረተሰቡ ነው።

አፈፃፀም ላይ ወይም በጥናት ላይ ያልታየ ነገር ካለ የባለሞያን ምክር እየወሰድን እየተሻሻለ ይሔዳል። ከላይ አውሮፓን ሳናነሳ የአፍሪካ አገሮችን ጠቅሰን ምሳሌዎችን አንስተናል። ሌሎች አገሮች የገቢያቸውን ሃምሳ በመቶ እና ከዚያ በላይ ከተመሳሳይ የገበያ ርስት እየሰበሰቡ እኛ ከአንድ በመቶ በታች እየሰበሰብን ነው። ይህንን አልሰበሰብንም ማለት ዕድገት ተጓተተ ማለት ነው። መሠረተ ልማት በአግባቡ አይስፋፋም ማለት ነው። ያ ሲሆን ደግሞ በተዘዋዋሪ በወቅቱ የምንፈልገው አገልግሎት እንዳናገኝ፤ መሠረተ ልማት እንዳይስፋፋ ዞሮም ደግሞ በመሠረተ ልማት ተደራሽነት ሊጨምር የሚችለውን የንብረታችንን ዋጋ የሚቀንስ ስለሆነ ግብር በዚህ ልክ መሰብሰቡ ብዥታ መፍጠር የለበትም።

ይሔን ብቻ ሳይሆን ሌላም ሕግ ሲወጣ መሬት ላይ ወርዶ እንዳይፈፀም የሚያደርግ፤ የሚያስከትለው ችግር ካለ ወይም በጥናት ጊዜ ግንዛቤ ውስጥ ያልገቡ ነገሮች ካሉ በሥራ ሒደት እየተሻሻሉ ይሔዳሉ።

ወደ ገጽ 7 ዞሯል

## ተጠየቅ

# ‹‹ የከተማ ቦታ ኪራይ እና ...



ከገጽ 6 የዞረ

**አዲስ ዘመን፡- የጋራ መኖሪያ ቤት የካሬው ልኬት እየታወቀ በድጋሚ መሐንዲስ ይለካል መባሉ በተጨማሪ የመሐንዲስ የአገልግሎት ክፍያ መጠየቁን ተገቢ ነው ?**

**አቶ ዘገየ፡-** በልኬት በኩል ያለውን ዋጋ በመሬት ቢሮ በኩል ስለሆነ ያንን ማለት አልችልም። እኔ በምክትል ቢሮ ኃላፊነት የምመራው የገቢዎችን ቢሮን ነው። ስለዚህ የመሬትን ጉዳይ የመሬት ቢሮ ቢመልስ ይሻላል። አጠቃላይ ልኬትን በተመለከተ ለምሳሌ አንድ ሰው የኔ ቤት ስፋት ይህንን አያክልም ሊል ይችላል። የዚያን ጊዜ ግብሩ ታሳቢ ያደረገው ቤቱ የተሠራበትን ቁሳቁስ የአፈር ወይም የብሎኬት ሊሆን ይችላል። ወይም ስፋቱ እና የቤቱ አገልግሎት ማለትም ቤቱ ለንግድ ነው ወይስ ለመኖሪያ የሚለው እነዚህን ሁሉ ግብሩ ግምት ውስጥ ያስገባል።

ቤቱ ወይም ሕንፃው የሚገኝበት የቦታ ደረጃ እንደሚታወቀው አንደኛ ደረጃ፣ ሁለተኛ ደረጃ እና ሦስተኛ ደረጃ የሚባል ቦታ አለ። ስለዚህ ግብሩም ይህንን ታሳቢ ያደረገ ነው። ለምሳሌ ከእነዚህ በአንዱ ላይ ግብር ከፋዩ የእኔ ቤት ስፋት ይህን አያክልም ቢል፤ ወይም ይህን አገልግሎት እየሠጠ አይደለም ብሎ መጠየቅ እና ምላሽ ማግኘት ይችላል። በሌላ በኩል ሊለካለትም ይችላል።

አሁን ባለኝ ግንዛቤ ከዚያ ቢሮ ጋር ባለኝ ግንኙነት በሁሉም የጋራ መኖሪያ ቤት ልኬት የሚያስፈልግበት ሁኔታ ያለ አይመስለኝም። ነገር ግን ለአንዱ ቤት የተሟላ መረጃ ተይዞ በሌላ በኩል መረጃ የሌለው የጋራ መኖሪያ ቤት ሊኖር ይችላል። ለምሳሌ ተመሳሳይ ሕንፃ ላይ ሆኖ የተጓደለ መረጃ ካለ የአንደኛው ተለይቶ ሊለካ ይችላል። ስለዚህ በዚህ መልኩ ልኬት የግድ የሚሆንበት ጊዜ አለ። የማያስፈልግበት ሁኔታም አለ። አከፋፈል ላይም ተጨማሪ ክፍያ የሚያስፈልገው አለ። ለዚህ የመሬት ቢሮ ቢጠየቅ ይሻላል።

**አዲስ ዘመን፡- ከግብር አከፋፈሉ ጋር በተያያዘ ምን ያህል ግንዛቤ ተፈጥሯል? በአስቸኳይ እንድንከፍል መደረጉ ተገቢ አይደለም ከሚለው አስተያየት አንፃር ምን ይላሉ?**

**አቶ ዘገየ፡-** የግንዛቤ ጉዳይ ሲነሳ ከተማው ሰፊ እና ብዙ ሕዝብ የሚኖርበት በመሆኑ ሁሉም ጋር ግንዛቤው ተፈጥሯል ለማለት አልችልም። ነገር ግን በጥናቱ ጊዜም ጉዳዩ የሚመለከታቸው ባለሞያዎች፣ የሥራ ኃላፊዎች እና የተለያዩ ሠራተኞች እንዲሁም በአንድም በሌላ መልኩ የግብር ከፋዩ ተወካዮች ተሳትፈዋል። የጥናቱን ግኝት ወደ ሥራ ይዘነው ስንመጣ እነዚህ አካላት በደንብ ያውቁታል። ዋናው ነገር ከላይ እንደገለፅኩት ግብሩ አሁን የተፈጠረ ርዕስ አይደለም።

የተሠራው የግብሩን ተመን ወቅታዊ ከማድረግ በስተቀር ምጣኔ እንኳን አልተሻሻለም። በጥናት የተሻሻለው ያውም አሁን ከተማዋ ባለችበት ሁኔታ ስንት ሕዝብ እየተከራየ ነው? ኪራይ ደግሞ መንግሥትም ሆነ ሌሎች የፋይናንስ ተቋማት ይከራያሉ። እነዚህ ሁሉ የጥናት ግብዓት ሆነዋል። ቃለመጠይቅ ተደርጎ በብዙ ሒደት ውስጥ አልፎ በጥናት የተገኘ ስለሆነ ሁሉም ሰው ጋር በአንድ ጊዜ ግንዛቤው ተፈጥሯል ባይባልም፤ በብዛት ግን የሚመለከታቸው አካላት እንዲሳተፉበት ተደርጓል። ከላይ እንደገለፅኩት እስከ ታች ድረስ መዋቅር ስላለ ግብሩን የመሰብሰብ እና የማሳወቅም ሥራ ይሠራል። ከከተማው ስፋት እና ከግብር ከፋዩ መጠን አንፃር ካየን ግን ሁሉም ሰው ጋር በተመሳሳይ መልኩ መልዕክት ደርሷል የሚል ድምዳሜ የለኝም።

**አዲስ ዘመን፡- የተሰጠው የግብር መክፈያ ጊዜ አጭር ነው መባሉስ ?**

**አቶ ዘገየ፡-** ግብር የመክፈያ ጊዜው እንደሚታወቀው እየተጠናቀቀ ነው። እስከ ሰኔ 30 እንዲከፈል ብለናል። እንዲያውም መከፈል የነበረበት እስከ የካቲት 30 ነበር። የካቲት 30 ባይከፈልም እስከ ሰኔ 30 እንዲከፈል ብለናል። ሰኔን አልፎ ወደሚቀጥለው ዓመት ከሔደ ስለሚደረብ ተጨማሪ ጫና ይፈጥራል። ስለዚህ እስከ ሰኔ 30 እንዲከፈል እናበረታታለን። በእኛ በኩልም ተገቢውን አገልግሎት ለመስጠት ዝግጁ ነን። ስለዚህ ጊዜው ያጠረው በበጀት ዓመቱ ውስጥ መሰብሰብ ስላለበት ነው።

**አዲስ ዘመን፡- አሁን ደግሞ ክፍያ ለመፈፀም መጨናነቆች እየተፈጠሩ ናቸው። ግብር ከፋዮች በአንድ መስኮት አገልግሎት መሰጠት እያስባቸው የተለያየ ቦታ ላይ እንዲሄዱ እየተገደዱ ስለመሆኑ እየገለፁ ናቸው። ለምሳሌ ልኬትን በተመለከተ ከወረዳ ወደ ክፍለ ከተማ፤ እንዲሁም ወደ ንግድ ባንክ እየተላኩ በወረፋ እየተንገላቱ ስለመሆኑ እየገለፁ ነው። ይህንን በተመለከተ ምን ይላሉ?**

**አዲስ ዘመን፡-** እንግዲህ ሌሎች ግብሮች፤ ለምሳሌ የ2014 ዓ.ም የግብር መክፈያ ጊዜ ከሐምሌ 1 2014 እስከ ጥቅምት 30 ቀን 2015 የነበረውን የቴክኖሎጂ ሲስተማችንን በማሻሻል ከተለያዩ ተቋማት ጋር በመሥራት ግብር ከፋዩ እንዳይንገላታ አድርገናል። ለምሳሌ ግብር ከፋዩ ወደ እኛ ሳይመጣ በእጅ ስልኩ መልዕክት እንዲደርሰው በማድረግ በቴሌ ብር ግብር እንዲከፍል አድርገናል። በተለይ ደረጃ ‹‹ሐ›› የሚባለው መክፈል የሚገባው ግብር በቴሌ ብር ወይም በባንክ ሔዶ እንዲከፍል ብዙ ሁኔታዎችን አመቻችተናል። ይህ ግን ሳይከፍሉ የዘገዩ ናቸው።

ልኬት የሚመጣው ከመሬት ቢሮ ነው፤ እኛ ቢሮ ተጀምሮ እኛ ቢሮ ላይ የሚጠናቀቅ አይደለም። ስለዚህ ድካም ሊኖረው ይችላል። እኛ ግን በፍፁም የግብር ከፋዩን ድካም ለመቀነስ በአነስተኛ ጊዜ ግዴታውን ተወጥቶ መብቱን አግኝቶ መሔድ እንዳለበት በመንግሥት ታምኖበት እየተሠራ ነው።

በአንዳንድ ቅርንጫፎች በተለይም ለሚ ኩራ ክፍለ ከተማ አካባቢ ሰው በዝቶ እየተቸገሩ መሆኑን አይተናል። የሰው ኃይል ከሌላ ክፍል በማንቀሳቀስ እንግልቱን ለመቀነስ እንሠራለን፤ ምናልባት ሰኔ ሙሉውን መክፈል ስለሚቻል። ሁሉም ይህቺኑ ጊዜ ተጠቅሞ አጠናቆ ቢሔድ ጥሩ ነው።

ነገር ግን አሁንም ግብር ከፋዮቻችን በዚህ ጊዜ ብቻ ሳይሆን መቼም ቢሆን ግብር ከፋዮች የሚሔዱት በመጨረሻዎቹ ቀኖች አካባቢ ነው። ከቀን 26 በኋላ ወደ ቅርንጫፎቻችን ሲኬድ በጣም ብዙ ሰው ተሰልፎ ይታያል። ከ10 እስከ 15 ደግሞ ማንም ላይኖር ይችላል፤ ስለዚህ ጫና እያመጣ ያለው የግብር ከፋዩም የሚከፍልበት ጊዜ ነው።

ነገር ግን በምንም ሁኔታ ተጨማሪ የሰው ኃይል በማምጣት እና ተጨማሪ ጊዜ በመስጠት አሁን ያሉትን ጫናዎች ለመቋቋም ጥረት እናደርጋለን። በሚቀጥለው ዓመት ደግሞ እንደሌሎች ግብሮች ከሌሎች የፋይናንስ ተቋማት ጋር በመቀናጀት በቀነሰ ድካም እና እንግልት ግብር ከፋዮች ግዴታቸውን ተወጥተው መብታቸውን እንዲያገኙ እንሠራለን።

**አዲስ ዘመን፡- የተመኑ ሁኔታ እና አከፋፈሉ ከክፍለ ከተማ ክፍለ ከተማ ሰፊ ልዩነት ያለው መሆኑን በሚመለከት ቅሬታዎች በመቅረብ ላይ ናቸው። ይህንን በተመለከተ ያለው ነገር ምንድን ነው ?**

**የጋራ መኖሪያ ቤቶች እስከ አሁን ሳይከፍሉ የቆዩት አዋጁ ላይ እንደተመላከተው የአከፋፈሉ ሁኔታ በየጊዜው ወቅታዊ ባለመደረጉ ነው። በተጨማሪም ኅብረተሰቡ ላይ ሲፈጠር የሚችለውን ጫና ታሳቢ በማድረግ ነው**

**አቶ ዘገየ፡-** ከላይ እንደገለፅኩት ነው። ደረጃ አንድ፣ ደረጃ ሁለት እና ደረጃ ሦስት የሚባሉ ቦታዎች አሉ። ካሬው ተመሳሳይ ቢሆንም ደረጃው የተለያየ ሊሆን ይችላል።

**አዲስ ዘመን፡- እርሱ ትክክል ነው። ነገር ግን አከፋፈሉ ላይ በአንድ ይዞታ ላይ የቤቱ ግንባታ የተለያየ ሲሆን ፤ ማለትም አንድ ሰው 50 ካሬ ሜትር ላይ ያረፈ የጭቃ ቤት እና 100 ካሬ ሜትር ላይ ያረፈ የድንጋይ ቤት ቢኖረው ሙሉ ለሙሉ የድንጋይ ቤት እንደሆነ ተቆጥሮ፤ በድንጋይ ቤት ተሰልቶ ይከፈላል።**

**አቶ ዘገየ፡-** የድንጋዩ ቤት ከበዛ መመሪያው እንደሚለው እንደ ድንጋይ ወይም 150ውም እንደብሎኬት ቤት ይወሰዳል።

**አዲስ ዘመን፡- ይሔ ሁሉም ክፍለ ከተማ ላይ አሠራሩ አንድ ነው ?**

**አቶ ዘገየ፡-** ከክፍለ ከተማ ክፍለከተማ የተለያየ አሠራር አይኖርም። አንድ ግለሰብ የአሠራር ልዩነት አለ የሚል ከሆነ ቅሬታ ማቅረብ ይችላል። ልኬትም ላይ ችግር ሊኖር ይችላል። 150 ካሬ ሜትር ቤት 250 ነው ከተባለ ግለሰቡ ቅሬታ አስገብቶ እንደገና እንዲገመትለት ማድረግ ይቻላል። የእያንዳንዱን ግለሰብ ጉዳይ እያነሳን አጋነን ማቅረብ የለብንም።

**አዲስ ዘመን፡- አንደኛው አሠራሩ ከክፍለ ከተማ ክፍለ ከተማ የተለያየ ነው የሚባለው አንዳንዱ ቦታውን ለክቶ ሲያስከፍል፤ አንዳንዱ ደግሞ ካርታን መሠረት አድርጎ ብቻ ያስከፍላል የሚል ነው?**

**አቶ ዘገየ፡-** ልኬት የሚኖረው የተደራጀ መረጃ ሳይኖር ሲቀር ነው። እንዲያውም እኛ መለካት አንፈልግም። ነገር ግን መረጃ ከሌለ ሊለካ ይችላል። ነገር ግን እንደአቅጣጫ ልኬት አይኑር ብለናል። ይሔ ከብዙ ሰው ውስጥ የአንድ ሰው ፋይል ላይኖር ይችላል። ይህ ከብዙ አንድ ቢያጋጥም ነው። ድርጅት ወይም የግለሰብ ቤት፤ ወይም ፎቅ ሊሆን ይችላል። መረጃ ባይኖርም ግብሩ መከፈል ስላለበት በራሱ በግብር ከፋዩም ጥያቄ ሊለካ ይችላል። በቂ መረጃ ከሌለ ሰውየው ላይ ጫና እንዳይፈጠር ወይም የመንግሥትም ጥቅም እንዳይጎድል ልኬት ሊከናወን ይችላል።

**አዲስ ዘመን፡- ኅብረተሰቡ ለሚያቀርበው ቅሬታ ምላሽ መሰጠት እና ግልፅነት መፍጠር አለበት?**

**አቶ ዘገየ፡-** ግልፅ ሊሆን የሚገባው ልኬቱ መሠረት የሚያደርገው ቤቱ የተሠራበት ግብአት እና ቤቱ የሚሰጠው አገልግሎት ነው። መኖሪያ ነው ወይስ የንግድ፤ የቤቱ ስፋት እንዲሁም ቤቱ የሚገኝበት የከተማ ደረጃ ነው። እንዲያውም በመሬት ማኔጅመንት እስከ ደረጃ 18 ነው። እኛ ግን ከሦስት በኋላ ያሉት ስለሚቀራረቡ ደረጃ ሦስት ብለን ይዘናል። ይሔ መመሪያው ላይ በትክክል ስለተቀመጠ ችግር የለውም። አፈፃፀሙ ላይ ችግር የገጠመው ሰው ማለትም በቦታው ስፋት መጠኑ ከተለያየ፤ ቤቱ መኖሪያ ሆኖ የንግድ ከተባለበት ወይም ደረጃ አንድ ሆኖ ደረጃ ሦስት ከሆነ ይህ ሰው ቅሬታ ማቅረብ ይችላል።

እስከ አሁን ስንሠራም በአፈፃፀም ላይ በቸልተኝነት ወይም በተለያየ ምክንያት ስህተት ሊፈጠር ይችላል። ስህተት ሲሠራ ደግሞ ይህ ሊፈጠር እንደሚችል በመገመት መንግሥት ማረሚያ መንገድ አለው። የታክስ ሕጉ ላይ ራሱ ቅሬታ የሚሠማበት አሠራር አለ። ከቅርንጫፍ እስከ ፍርድ ቤት ድረስ ቅሬታ ማቅረብ ይቻላል። ስለዚህ ይህም ተመሳሳይ ነው። ቅሬታ ማቅረብ ይቻላል።

**አዲስ ዘመን፡- በዚህ ግብር ላይ ከተፈጠረው ብዥታ መካከል አንዱ ግብሩ የንብረት ነው ወይም ፕሮፐርቲ ታክስ ነው ይባላል። እርሶም ሆኑ ሌሉች የሥራ ኃላፊዎች እንደሚሉት ይህ የንብረት ግብር አይደለም እያላችሁ ነው። ወደፊት የንብረት ግብር አለ ማለት ነው?**

**አቶ ዘገየ፡-** አዎ የንብረት ግብር ገና ሕግ አልወጣለትም። ረቂቁ እየተዘጋጀ ሃሳብ እየተሰጠበት ነው። ስለዚህ ስለሱ ማውራት የሚቻለው ገና ሕጉ ሲወጣ ነው። ምን ምን ነገሮች ታሳቢ ይደረጋሉ፤ ምን ተጨማሪ ነገሮችን ያመጣል የሚለውን ማውራት የሚቻለው ወደ ፊት ነው። የአሁኑ አዋጅ 80 1968 ነው። ደንቡም 30 1968 ነው። የከተማ ቦታ ኪራይ እና የከተማ ቤት ግብር ነው። አሁን ቦታው ላይ ትኩረት ስላላደረግን ከአዋጁ ጋር እንዲጣጣም የቤት ግብር ብለን ወስደነዋል።

**አዲስ ዘመን፡-ሌላ መናገር የሚፈልጉት ነገር ካለ?**

**አቶ ዘገየ፡-** በአንዳንድ መገናኛ ብዙኃን እንደተነገረው አዲስ ነገር አልመጣም። ወሬው ትክክል አይደለም፤ ከላይ እንደገለፅኩት ነባር የግብር ዓይነት እየተሰበሰበ ነው። ኪራዩን ወቅታዊ ማድረግ በጣም ያስፈልጋል። ይህ ብቻ ሳይሆን ሌላ ለከተማ አስተዳደሩ ገቢ ሊያመነጩ እና መልሰው ኅብረተሰቡን ሊጠቅሙ የሚችሉ የአገልግሎት ተመኖችን ወይም የገቢ ሁኔታዎችንም በተጨማሪነት ማየት ሊያስፈልገን ይችላል።

ኅብረተሰቡ ዞሮ ዞሮ ከራስ ለራስ የሚከፍል ስለሆነ ለራሱ መሠረተ ልማት ተደራሽ ለማድረግ የሚሰበሰብ በመሆኑ፤ ቀደም ሲል ከአንድ ብር ጀምሮ ሲከፈል ነበር። አሁን ግን እንኳን በአንድ ብር በአስር ብርም የሚገዛ ምርትም ሆነ የሚገኝ አገልግሎት የለም።

አሁን ከአንድ ብር ጋር በማነፃፀር ዛሬ ከቁጥር አንፃር ሦስት እና አራት ሺህ ብር ክፈል ሲባል፤ ተገቢ አይደለም ሊል ይችላል። ነገር ግን እኛ እንደመንግሥት በየጊዜው እያሻሻልን ማስከፈል ሲኖርብን አለማስከፈላችን እንጂ፤ አሁን ክፈሉ የተባለው ተገቢ ክፍያ ነው። ስለዚህ በዚሁ መሠረት ሕዝቡ ግብሩን እየከፈለ መብቱን እንዲጠይቅ ጥሪዬን አስተላልፋለሁ። ከአገልግሎት ጋር ተያይዞ የሚነሳ ጥያቄ ካለ ግን በማንኛውም መልኩ ለማስተካከል ዝግጁ ነን።

**አዲስ ዘመን፡- ስቀረቡት ጥያቄዎች ምላሽ በመስጠትዎ በዝግጅት ክፍሉ ስም አመሰግናለሁ።**

**አቶ ዘገየ፡-** እኔም አመሰግናለሁ።

ፖለቲካ እና ልዩ ልዩ

# ነፃ ሃሳብ

# ኢድ አል አደሃ/ዐረፋ/፤እስልምናና ኢትዮጵያ!!

የአሰሳው ኃይረዲን ከድር/ከአዲስ አበባ/

በመላው ዓለም ዙሪያ በሚገኙ የእስልምና ሃይማኖት ተከታዮች ዘንድ በድምቀት ከሚከበሩ በዓላት መካከል አንዱ የሆነው የኢድ አል-አደሃ በዓል መከበር ምክንያቱና ታሪካዊ ዳራው ምን ይመስላል? «የዒድ አል-አድሃ ታሪካዊ ዳራ ነቢዩ ኢብራሂም/ዐሰ/ልጃቸውን ለአላህ ለመሰዋት ያደረጉት ቁርጠኝነት የተመላበት ውሳኔ እና ለመስዋዕትነት የቀረበው ልጅ ያሳየው የተለየ ጽናት ነው። ነቢዩ ኢብራሂም/ዐሰ/የአላህ ደግ ሰው ከ120 ዓመታት የመካንነት ሕይወት በኋላ የበኩር ልጃቸው የሆነውን ኢስማዔልን በእርጅና ዘመናቸው አላህ በፍቃዱ ቸራቸው።

ታላቅ ሚስታቸው ሳራ ለፍሬ ባለመብቃቷ። «ያ አላህ ያለ ዘር አታስቀረኝ፤ እኔን የሚተካ ሷሊህ የሆነ ልጅ ስጠኝ» በማለት ዱዓ አደረጉ፤ በዚሁ መሠረት በሳራ ፈቃደኝነት ሐጀራ የምትባለውን የቤት ሠራተኛቸውን አገቡ። ሐጀራም ዒስማኢል የተባለ ልጃቸውን ወለደችላቸው። ይህ ልጅ በአላህ ፈቃድ በመካ ከተማ እንዲያድግ የተወሰነ ስለነበረ ኢብራሂም ሐጀራን እና ዒስማኢልን ወደ ዐረቢያ ከተማ ወሰዷቸው። ዒስማኢል ካደገ በኋላ ደግሞ አላህ «ልጅህን እንድትሰዋ ታዘሃል» የሚል ትዕይንት በህልማቸው አሳያቸው። የነቢያት ህልም ደግሞ ከራዕይ የሚቆጠር ነው። ስለዚህ ኢብራሂም በህልማቸው ያዩትን ትዕዛዝ በዝምታ አላለፉትም። በወቅቱ የሆነውን ቅዱስ ቁርአን እንዲህ ይተርካል።

«ከርሱ ጋር ለሥራ በደረሰ ጊዜም» ልጄ ሆይ! እኔ በህልሜ የማርድህ ሆኜ አይቻለሁ፤ (እስቲ አንተም ነገሩን) ተመልከት። «ምን ይታይሃል»?አሉት፡ ፡(ልጁም) አባቴ ሆይ! የታዘዝከውን ፈጽም፤ አላህ ቢሻ ከታጋሾቹ ሆኜ ታገኘኛለህ አለ» (ሱረቱ-ሷፍፋት፤102)። አባትና ልጅ በዚህ መንገድ ከአላህ የተላለፈውን ትዕዛዝ ሊፈጽሙ ተነሱ፤ ነቢዩ ኢብራሂም/ዐሰ/ ልጃቸውን እንዲሰዉ የታዘዙት ከዐረፋት መሬት ብዙም ባልራቀ ቦታ ላይ ስለነበረ ወደዚያው ጉዞ ጀመሩ። በመንገዳቸው ግን ኢብሊስ (ሰይጣን) በሰው ተመስሎ በጣም ተፈታተናቸው፤ ሦስት ጊዜ ያህል እየወጣ «ከስንት ዓመት በኋላ ያገኘኸውን አንድዬ ልጅህን ስትሰዋ ምንም አይጸጽትህም?...እንዴት ጅል ትሆናለህ»? እያለ ሞገታቸው።

ከአላህ ትዕዛዝ ፍንክች የማይሉት ነብዩ ኢብራሂም ግን ድንጋይ ከመሬት በማንሳት «አዑዙቢላሂ ሚነ-ሸይጣኒ ረጂም» እያሉ ኢብሊስን ወገሩት። ነብዩ ኢብራሂም ብቸኛ ልጃቸውን ዒስማኢልን ሊያርዱት አጋደሙት። ልጁም ምንም ሳያንገራግር ከመሬቱ ላይ ተኛ። ነብዩ ኢብራሂም ልጁን ሊያርዱት ሲሞክሩ ግን ቢላዋው አላርድ አላቸው። ኢብራሂም እንደገና ቢላዋውን ገዘገዙት/ሣሉት/፤ነገር ግን ፈጽሞ ዶለዶመ። ታዛዡ ልጅ የሆነው ነገር አልገባውም። አባቱ ቶሎ ስላላረዱት ተገረመና «አባዬ!፣ምናልባት የአባትነት ፍቅር ይዞህ ይሆናል በቶሎ ያላረድከኝ፤እስቲ ዐይኔን በጨርቅ ሸፍነውና እርዱን ሞክር» የሚል አስተያየት ሰጠ።

በዚህን ጊዜ ግን ከወደ ሰማይ ጥሪ መጣ። የአላህ መልዓክ «ኢብራሂም ታላቅነትህን አስመስክረሃልና እርዱን አቆየው»በማለት አወጀ። በምትኩም መልዓኩ ከገነት ያመጣውን በግ እንዲያርዱና ልጁን ወደ ቤት እንዲመልሱት ነገራቸው። በዚህም መሠረት በጉ ታረደ። ኢብራሂምና ዒስማኢልም ወደ መካ ከተማ ተመለሱ። ሁለቱ ሰዎች ለፈጣሪ መታዘዝን በግልጽ ያሳዩባት ያቺ ዕለት የዒድ አል-አድሓ በዓል ሆና እንድትከበርም ተወሰነ። ዒስማኢል ለመስዋዕትነት የቀረበበት ድርጊት ደግሞ በዚሁ ዕለት የሚታረደው ከብት ወይም ግመል «ኡድሂያ» መነሻ ሆነ። ይህን ታሪክ መነሻ በማድረግ ኢድ አል-አደሃ ይከበራል።

በዓሉ የመስዋዕት፣ የእርድ በዓል ነው። በተለይም የሐጅ ጸሎት የሚፈጽም ሰው በዚህ ቀን ከብት የማረድ ግዴታ አለበት። የተቀረውም ሙስሊም ዕለቱን አቅሙ በፈቀደ ሁኔታ ከብት በማረድ ከቤተሰብና ዘመድ አዝማድ ጋር ያሳልፈዋል። ለኢድ አል አድሃ አንድ ሰው ከሚያርደው ከብት ሲሶውን ብቻ እንዲወስድ ነው ደንቡ። የተቀረው ሲሶው ለዘመድ አዝማድ፣ ሲሶው ደግሞ አቅም ለሌለው ደሃ እንዲከፋፈል እስልምና ያዛል። ከዚህ የተነሳም የአረፋ በዓል በእስልምና ኃይማኖት ተከታዮች ዘንድ ታላቅ በዓል ነው።

**በዓሉ የመስዋዕት፣ የእርድ በዓል ነው። በተለይም የሐጅ ጸሎት የሚፈጽም ሰው በዚህ ቀን ከብት የማረድ ግዴታ አለበት። የተቀረውም ሙስሊም ዕለቱን አቅሙ በፈቀደ ሁኔታ ከብት በማረድ ከቤተሰብና ዘመድ አዝማድ ጋር ያሳልፈዋል። ለኢድ አል አድሃ አንድ ሰው ከሚያርደው ከብት ሲሶውን ብቻ እንዲወስድ ነው ደንቡ። የተቀረው ሲሶው ለዘመድ አዝማድ፣ ሲሶው ደግሞ አቅም ለሌለው ደሃ እንዲከፋፈል እስልምና ያዛል።**

የእስልምና እምነት እንደሚያስተምረው ዐረፋ የሚለው ቃል በዐረብኛ «አወቀ» እንደማለት ነው። ይህም ታሪክ አለው። አዳምና ሔዋን ወይንም አደምና ሃዋ ከጀነት ወደ ምድር ከወረዱ በኋላ ለብዙ ዘመናት ተጠፋፍተው ነበር። ለረጅም ጊዜ ሲፈላለጉ ከቆዩ በኋላ በዚህ ዕለት በሳውዲ ዐረቢያ ባለው የአረፋ ተራራ ላይ ተገናኙ። እዚያም«ዐረፍቱክ...ዐረፍቱኪ»ተባባሉ።«አወቅኩህ! አወቅኩሽ»ማለታቸው ነው።ይህንን ታሪክ ለመዘከር ሲባል ነው የዐረፋን በዓል ማክበር የተጀመረው። ይህ በዙልሂጃ ዘጠነኛው ቀን የሚከበር በዓል ነው።

ሀገራችን ኢትዮጵያ ከቀደምት የእስልምና ሃይማኖት ተቀባዮች አንዷ ናት። የእስልምና ታሪክ ሲነሳ የኢትዮጵያም ስም አብሮ ይነሳል። የነብዩ መሐመድን (ሰዐወ)የቅርብ ቤተሰቦችና ተከታዮችን ተቀብላ ያስተናገደች ሀገር ናት። ኢትዮጵያ፣ የመጀመሪያው ሙዕዓዝን(አዛን አድራጊ)ወይም የሰላት ጥሪ አቅራቢ ቢላል ኢብን ረባህም ኢትዮጵያዊ ነው። የነብዩ መሐመድን (ሰዐወ) እንግዶች ተቀብሎ ያስተናገደው ንጉሥ ነጃሺ በእስልምና እምነት ተከታዮች ዘንድ ትልቅ ቦታ የሚሰጠው ነው። መሐመድ ዓሊ የተባሉ ምሁር(ፒ.ኤች.ዲ)አንድ ወቅት እንደገለጹት፣ «በንጉሥ ነጃሺ፣ በአጠቃላይም በሃበሻ አማካኝነት ሃበሾችን መሠረት ያደረጉ ከ23 በላይ የቁረአን አንቀጾች፣ በሃበሾች ቋንቋም ከ30 በላይ የቁረአን አንቀጾች እንዲወርዱ፤ በተጨማሪም በነብዩ መሐመድ/ሰዐወ/ሰበብ ስለ ሃበሾች ክብር ከ27 ያላነሱ ነብያዊ ሃዲሶች እንዲነገሩ ምክንያት እንደሆኑ ይነገራል። ከነዚህ የቁረአን አንቀጾችና ነብያዊ ሃዲሶች ለማሳያ ያህል አንድ ሦስቱን እሴቶች ባጭሩ እናውሳቸው።

ሀ) ሶላተል ገይብ፡-(አስከሬን በሌለበት የሩቅ ስግደት)። ነብዩ መሐመድ/ሰዐወ/የነጃሺ ሞት መርዶ በጅብሪል አማካኝነት ደረሳቸውና ምዕመኖቻቸውን አስከትለው ሶላተል ገይብ(አስከሬን/ጀናዛ/በሌለበት ስግደት)አሰገዱ። ከዚያን ጊዜ ጀምሮ ይህ የሶላተል ገይብ የሙስሊሞች ባህል ሆኖ ቀጠለ።

ለ) የውክልና ጋብቻ፡-ወደ ሃበሻ ከተሰደዱ ሴቶች መካከል ረምላ ቢንት አቡ ሱፊያን ነበረች። ረምላ ከባሏ ጋር በሃበሻ ስትኖር ባለቤቷ ኡቤይደላ ቢን ጃህሽ ከዚህ ዓለም በሞት ይለያታል። ረምላ፣ ቢባ ከምትባል ሕፃን ልጅዋ ጋር በብቸኝነት ስትኖር በአላህ ፈቃድ በንጉሥ ነጃሺ ውክልና ነብዩ መሐመድን/ሰዐወ/ለማግባት በቃች። የረምላም ወኪል የቅርብ ዘመዷ የነበረው ኻሊድ ቢንሰኢድ ነበር። በአጠቃላይ የጋብቻ ሥርዓቱ በውክልና ጋብቻ የተፈጸመበት፣ ራምላ ከማግባቷ በፊት አራት ወር ከአስር ቀን እንደሞላት የተረጋገጠበት፣ ጥሎሽ የተሰጠበት፣ የሰርግ ግብዣ የተደረገበት፣ ጋብቻው በምስክሮች ፊት የተፈጸመበት፣ ስለአፈጻጸሙም በቃዲ ትምህርት የተሰጠበት ወ.ዘ.ተ ነበር።

ከዚያ ጊዜ ጀምሮ ይህ በነብዩና በራምላ የተፈጸመ የጋብቻ ዓይነት የእስላማዊ ጋብቻ መሠረትና መመሪያ ሆኖ ይገኛል።

ሐ) የውርስ ሕግ፡-በእስልምና ታሪክ የውርስ ሕግ አጀማመር ከሃበሻ ጋር ግንኙነት እንዳለው ይታመናል። ለዚህም ወደ ሃበሻ ከተሰደዱ ሰዎች መካከል አዲይ ቢን ነዲላ የሚባል ይገኝበት ነበር። ይህ ሰው በስደት ሃበሻ እንዳለ በመሞቱ ነብዩ መሐመድ ንብረቱን ቤተሰቦቹ እንዲወርሱ በማዘዛቸውና ልጁ አማን በመውረሱ፣ ከዚህ ጊዜ ጀምሮ እስላማዊ የውርስ ሥርዓት እንደተጀመረ ይታመናል።

መ) ዘንግ፡-ነጃሺ ለነብዩ መሐመድ/ሰዐወ/ሦስት ዘንጎችን ልከውላቸው ነበር ይባላል። እሳቸውም አንዱን ለአቡበከር፣ ሁለተኛውን ለዓሊና ሦስተኛውን ለቢላል ሰጥተው በተለያዩ የበዓል ጊዜያት ዘንጉን ይዞ ሶላቱን ይመራበት ነበር፤ በአሁኑ ወቅትም በየመስጊዱ የጁምዓ ኹጥባ(ድስኩር)ኢማሞች የሚይዙት ዘንግ ከዚህ ተያይዞ እንደመጣ ይነገራል።

## የዓለም ሀገራት የኢድ አል - አድሃ/አረፋ/ በዓልን እንዴት ያከብሩታል?

በዓለም ዙሪያ የእስልምና ሃይማኖት ተከታዮች ዘንድ በድምቀት ከሚከበሩ በዓላት መካከል አንዱ ነው። የኢድ አል አድሃ(አረፋ)በዓሉ የእርድ ወይም የመስዋእትነት በዓል በመባል ይታወቃል። የአላህ/ሱወ/ ደግ ሰው ነብዩ ኢብራሂም/ዐሰ/ከ120 ዓመታት የመካንነት ሕይወት በኋላ በአላህ ፈቃድ ወንድ ልጅ ተቸራቸው። ልጃቸው ኢስማኤል ለአባቱ ታዛዥ እንደነበርም ይነገራል።

ነብዩ ኢብራሂም በደስታቸው ማግስት የእምነታቸው ጽናት የሚፈተንበት ወቅት ተፈጠረ። የሰባት ዓመት አንድያ ልጃቸውን መስዋእት ያደርጉ ዘንድ ከፈጣሪ ታዘዙ። የልጃቸው ፍቅር ቢያስጨንቃቸውም ትዕዛዙ የአላህ ነውና ሊፈጽሙ ከመካ ወደ አረፋ ተራራ ወጡ። ነብዩ ኢብራሂም ልጃቸውን ሊሰው ሲዘጋጁ ከሰማይ በኢስማኤል ምትክ መስዋእት የሚሆን በግ ወረደላቸው። በዓሉም ኢድ አል አድሃ(አረፋ)እየተባለ በየዓመቱ ለመከበሩ ምክንያት ሆነ።

## በዓለም ሀገራት የአረፋ በዓል አከባበርን ለአብነት ያህል

### በሕንድ

ሕንዳውያን በሂጅራ የዘመን ቀመር በ12ኛው ወር በ10ኛው ቀን የሚያከብሩትን የኢድ አል አድሃ በዓል «ታላቁ ኢድ» ሲሉ ይጠሩታል። ኢድ ኩርባን ወይም ኩርባን ባያራሚ ሲሉ እንደሚጠሩትም መረጃዎች ያመላክታሉ። የነብዩ ኢስማኤልን ለመስዋእትነት መመረጥ እና መታዘዝ ታሳቢ በማድረግም ጠቦት፣ ጥጃ፣ ግመል ወይም ሌሎች ለእርድ የተፈቀዱ እንስሳት በቀኑ ይታረዳሉ። የታረደው ስጋም ለቤተሰብ፣ ለጓደኛ እና ማረድ ለማይችሉ ወገኖች ለሦስት እኩል ይከፋፈላል።

ሕንዳውያን በዓሉን ከሃይማኖታዊ ትሩፋቱ ባለፈ የቤተሰባዊ እሴት ማጠናከሪያ እና መሰባሰቢያ በዓል አድርገው ስለሚያዩት በተለያየ ምክንያት ተለያይተው የሚኖሩ ቤተሰቦች ይሰባሰቡበታል። በዓለም ዙሪያ የሚገኙ ሀገራት እና ሙስሊሞች በዓሉን የሚያከብሩበት ሂደት ከባሕል እና ከእሴት ልዩነት ጋር በተያያዘ የሚያከብሩበት አውድ ከቦታ ቦታም ይለያያል። ኢድ አል_አድሃ(አረፋ) ከኢድ አልፈጥር በተለየ መልኩ በዓሉ የሚከበርበት ቀን የጨረቃን መታየት መሠረት አያደርግም።

### የተባበሩት አረብ ኤምሬትስ

የተባበሩት አረብ ኤምሬትስ ደግሞ ኢድ አል አድሃ (አረፋ)ን ለማክበር ሦስት ተከታታይ ቀናትን ይጠቀማሉ። ከኢድ አል አድሃ በዓል ቀድማ ያለችዋን ቀን በልዩ ትኩረት ሲያከብሯት ስያሜዋንም «አረፋ» ይሏታል። ከዋዜማው ቀን ጀምረው «ኢድ ሙባረክ» በመባባል የደስታ መልዕክት ይለዋወጣሉ።

ሕፃናት በበዓል አልባሳት ደምቀው የኢድ ስጦታ ለጎረቤቶቻቸው በማበርከት ያሳልፋሉ። እናቶች መኖሪያ ቤቶቻቸውን በኢድ አርማ ያሳምራሉ፤ ተወዳጅ እና ጣፋጭ ምግቦች በተለየ ሁኔታ ለቤተሰቡ ይዘጋጃሉ።

### በቱርክ

በቱርክ በመጀመሪያው የኢድ አል አድሃ ቀን ወንዶች ለተለየ ሃይማኖታዊ ሥርዓት ወደ መስጂድ በጠዋት ይሄዳሉ። ከቅርብ ጊዜ ወዲህ በቱርክ ለመስዋዕት የሚቀርበውን ገንዘብ እና እንስሳ ለበጎ አድራጎት ተቋማት ይሰጣል። ቱርካውያን በኢድ አል አድሃ ወቅት ለበዓሉ በሚመጥን አልባሳት ደምቀው ቤተ ዘመድ ይጎበኛሉ፤ ጥሪ አድርገው በቤታቸው ይጋብዛሉ፤ እንዲሁም የሀብት አቅም ለሌላቸው ወገኖች ድጋፍ ያደርጋሉ። ወጣቶች በጎረቤቶቻቸው ቤት በጠዋት እየሄዱ እንኳን አደረሳችሁ!!በማለት እጆቻቸውን በመሳም ይዘይራሉ። አንዳንድ ቱርካውያን ዓመታዊ እረፍታቸውንም በኢድ አል አድሃ አካባቢ ያደርጋሉ።

በሞሮኮ፣ ቱኒዚያ፣ ግብጽ፣ ኢትዮጵያ፣ ሱዳን እና በሌሎችም በርካታ የአፍሪካ እና የዓለም ሀገራት ኢድ አል አድሃ(አረፋ)በእስልምና ሃይማኖት ተከታዮች ዘንድ በተለያዩ ዓለም አቀፋዊ ድባቦች፣ በሰፊ ውብ ዝግጅቶች፣ በከፍተኛ ድምቀት ይከበራል።

ሁሉም የኢትዮጵያ ሕዝብ በቅርበት እንደሚያውቀው በኢትዮጵያ የእስልምና ሃይማኖት ተከታዮች በጠዋት ተነስተው፣ በሃይማኖታዊ ንፁህ አልባሳት ደምቀው እና አምረው ወደ መስገጃ አደባባይ እና ወደ መስጂዶች በረድፍ ሲያመሩ ሲታዩ የጎላ ውበት፣ አስደማሚ አንድነት ይንፀባረቃል። ሶላታቸውን በጋራ ሰግደው እና በአንድ ዓይነት መንፈሳዊ ቋንቋ አላህን አመስግነው፣ እርስ በእርሳቸው የመልካም ምኞት መግለጫ ተለዋውጠው፣ ከልብ የመነጨ ፈገግታ ተመጋግበው፣ አብረን ወደ ቤት እንግባ፣ አብረን እንዋል እያሉ ሲገባበዙ፣ በአክብሮት ሲጠራሩ ማዳመጥ፣ በተግባር መመልከት የተለመደ ነው።

ሲለያዩም በታላቅ ትህትና፣ በልዩ መተናነስ ታጅበው በመጡበት አኳኋን ወይም መንገድ ቀይረው ለፈጣሪ ምስጋና እያቀረቡ ወደ ቤታቸው ይመለሳሉ። ይሄ በኢትዮጵያዊ ጨዋነት የተሞላው መርሃ ግብር በሌላ እምነት ተከታይ ጓደኞች፣ የሥራ ባልደረቦች፣ ጎረቤቶች ዘንድ የማይረሳ የወዳጅነት ትዕይንት፣ የማይዘነጋ የአብሮነት እውነት እንደመሆኑ ከአደባባይ ሶላት በኋላ ደግሞ የእርድ ሥርዓት በየቤታቸው/በየሰፈራቸው/ ይኖራል። ቤተሰብ ተሰብስቦ በጋራ ያከብራል፤ ያለው ለሌለው ያካፍላል፤ እንዲሁም ከጎረቤቶቻቸው ጋር በመጠራራት ይገባበዛሉ።

ለጥንቃቄ ሲባል ከእርድ ሥርዓት ቀደም ተብሎ የሌላ ሃይማኖት ተከታይ ወዳጆች፣ ጎረቤቶች ተጠርተው እና ተጋብዘው፣ በጥልቅ የፍቅር ነፃ መንፈስ ተጫውተው«ኢድ ሙባረክ»እየተባባሉ፣ በሰላም፣ በጤና ዘልቀው ቀጣዩን ዓመት ሳይለያዩ በደስታ፣ በጋራ እንዲያከብሩ መልካም ምኞታቸውን እየተገላለፁ፣ ከልብ እየተመራረቁ በፍፁም ኢትዮጵያዊ ለዛ ይገባሉ፣ ይወጣሉ።

መቼም ኢትዮጵያዊነት ይለያል አይደል?

እኛም ለመላው የእስልምና ሃይማኖት ተከታዮች «ኢድ ሙባረክ» ብለናል!!

# የኤሌክትሮኒክ ግዢ ስርዓት - የመንግሥትን ሀብት ለታለመለት ዓላማ የማዋያ መንገድ

**ፍሬሕይወት አወቀ**

ከመንግሥት ዓመታዊ በጀት ከ60 እስከ 70 በመቶ የሚሆነው ሃብት ለግዥ እንደሚውል መረጃዎች ያመለክታሉ። የግዢ ስርዓቱ በሰዎች የሚፈጸምና በቴክኖሎጂ የተደገፋ ካለመሆኑ ጋር ተያይዞ ይህ ከፍተኛ መጠን ያለው የመንግሥት በጀት ለምዝበራና ለብልሹ አሰራር እየተጋለጠ ለታለመለት ዓላማ ሳይውል እንደሚቀር መረጃዎች ያመለክታሉ። ይሁንና የመንግሥት ግዢና ንብረት ባለስልጣን ይህን ችግር ለመፍታት ያስችል ዘንድ በተለይም የመንግሥት የግዢ ስርዓትን በማዘመን ከሰዎች እጅ ንክኪ ነጻ በሆነ በኤሌክትሮኒክ መንገድ መፈጸም የሚቻልበትን ሁኔታ አመቻችቷል። በዚህም በጀቱ ለታለመለት ዓላማ እንዲውል በማድረግ የመንግሥትና የህዝብን ሃብት ከብክነት መታደግ እንደሚቻል ታምኖበታል።

በቅርቡ የመንግሥት ግዥና ንብረት ባለሥልጣን ስራ ላይ ያዋለውን የኤሌክትሮኒክ የግዥ ሥርዓት በተመለከተ አንድ አካል ከሆኑት ከአቅራቢዎች ጋር ውይይት ባደረገበት ወቅት እንደተጠቆመውም፤ የመንግሥት ግዢ ዘመኑ የደረሰበትን ቴክኖሎጂ ተጠቅሞ ከሰው እጅ ንክኪ ውጭ በሆነ መንገድ በኤሌክትሮኒክስ መንገድ መፈጸሙ ከፍተኛ ጠቀሜታው አለው።

በውይይቱ የተሳተፉት የተጎና ኮንስትራክሽኑ አቶ ሄነሪ ነጋሽ፤ የግዢ ስርዓቱን ለማዘመን የተደረገው ጥረት እጅግ በጣም ጥሩና አበረታች መሆኑን ይገልጻሉ። ድርጅታቸውም በዚሁ ስርዓት ውስጥ ገብቶ መሥራት ከጀመረ ከአምስት ወራት በላይ ማስቆጠሩን ነው የጠቀሱት። የግዥ ስርአቱ ለአጠቃቀም ምቹና ከሰዎች ንክኪ ነጻ መሆኑን ጠቅሰው፣ ከሙስና ነጻ የመሆን ዕድል እንዳለውና ለአቅራቢዎችም በርካታ ጥቆሞች እንደሚሰጥ ተናግረዋል።

እሳቸው እንዳሉት፤ በዋናነት ቴክኖሎጂውን መጠቀም ጊዜን ያስችላል። ከሁሉም በላይ የጨረታ ሰነዶችን ለመግዛት ሲባል ይደረጉ የነበሩ ምልልሶችን የሚያስቀር በመሆኑ ጠቀሜታው ዘርፈ ብዙ ነው። ለወረቀትና ለሌሎች አገልግሎቶች የሚውለውን ሃብትም ከብክነት ይታደጋል።

በቀደመው አሰራር በደብዳቤ ይደረጉ የነበሩ ምልልሶችም ለቁጥር የበዙ መሆናቸውን አስታውሰው፣ እነዚህን አላስፈላጊ ሂደቶች ማስቀረት እንደቻለና ይህም በብዙ ገንዘብ ሊተመን እንደሚችል አብራርተዋል።

አሁን ላይ በኤሌክትሮኒክ በሚደረገው ግዢ ቢሮ ተቀምጦ በኦንላይን ጨረታውን መሳተፍና ውጤቱንም ማወቅ የሚቻልበት የአሰራር ስርዓት መሆኑን ጠቅሰው፣ ጠቀሜታው ዘርፈ ብዙ ነው ብለዋል። ለብልሹ አሰራር ዕድል እንደማይሰጥም ተናግረው፣ እንደ አገርም የሚኖረው አበርክቶ ጉልህ መሆኑን ነው ያስታወቁት።

አቶ ሄነሪ እንዳሉት፤ የኤሌክትሮኒክ የግዢ ስርዓት ገና አዲስ የተጀመረ ከመሆኑ ጋር ተያይዞ አንዳንድ ችግሮች ሊያጋጥሙ ይችላሉ። ይህም ከመሰረተ ልማት አለመሟላት ጋር ተያይዞ ሊከሰት የሚችል ነው፤ ከእነዚህ ችግሮች መካከል የኢንተርኔት መቆራረጥ አንዱ ነው። ለዚህም የሚጠቀሟቸው የኤሌክትሮኒክ መሳሪያዎች ሂደቱን ፕሮሰስ ለማድረግ ምን ያህል አቅም አላቸው የሚለውን መፈተሽ ከአቅራቢዎች ይጠበቃል። ይህም በቀጣይ ከቴክኖሎጂው ጋር በሚኖር መላመድ እየተቀረፈ የሚመጣ ችግር ነው።

ከደህንነት ጋር በተያያዘም እንዲሁ ስጋት ነበረኝ ያሉት አቶ ሄነሪ፤ ስጋታቸውም የአቅራቢው ሰነድ ሶስተኛ ወገን ዘንድ ይደርሳል የሚል እንደነበር ያስታውሳሉ። አሁን ላይ ግን ባገኙት ስልጠና መሰረት በኢንሳ በኩል የሚደረግ ጥበቃ ስለመኖሩ መረዳት እንደቻሉና ስጋታቸውም የተወገደላቸው መሆኑን አጫውተውናል።

ሌላው አስተያየት ሰጪ የዋይ ኮንስትራክሽኑ አቶ ይደሰት ተስፋዬ ነው። አቶ ተስፋዬ ቴክኖሎጂው ሲተዋወቅ አንስቶ የመጀመሪያው ተመዝጋቢ እንደነበርና በዚህም ደስተኛ መሆኑን ይገልጻል። እሱም እንደ አቶ ሄነሪ ቴክኖሎጂው ዘርፈ ብዙ ጠቀሜታ እንዳለው ይናገራል።


**አቶ ሀጂ ኢብሳ**

አቶ ይደሰት እንዳለው፤ የኤሌክትሮኒክ ግብይት ስርአቱ በርካታ ውጣ ውረዶችን ማቃለል የቻለ ነው። መንግሥት ወደዚህ ስርዓት ከመግባቱ አስቀድሞ አንዳንድ የውጭ ድርጅቶች ቴክኖሎጂውን ሲጠቀሙበት ነበር፤ ለወደፊት የተሻለ አበርክቶ እንደሚኖረውና ሰዎች እኩል ዕድል እንዲኖራቸው በማድረግ በኩልም ሰፊ ድርሻ አለው።

‹‹አንዳንድ ጊዜ ጨረታ ላይ ሰፊ የኩባንያ ፕሮፋይል ያላቸው ይገጥማሉ›› የሚለው አቶ ይደሰት፤ እነዚህን ፕሮፋይሎች ለመለየት ብዙ ጊዜ ይወስድባቸው እንደነበር ይናገራል። የግዢ ስርዓቱ በዘመናዊ ቴክኖሎጂ በኤሌክትሮኒክ መሆኑ ሥራውን በእጅጉ ማቃለል የቻለና ለሁሉም እኩል ዕድል የሚሰጥ ሆኗል ይላል።

አልፎ አልፎ እንደ ችግር የሚታዩ ሂደቶች ቢኖሩም የኤሌክትሮኒክስ ግዢ የጎላ ጠቀሜታ አለው ሲል ገልጾ፤ ይህን የግብይት ስርአት ሁሉም ሰው በቅድሚያ አምኖ መቀበል እንዳለበት ተናግሯል። በተለይም ሁሉም ሰው እኩል ዕድል አግኝቶ መወዳደር የሚችልበት ስርዓትና የተሻለው ሰው የሚመረጥበት በመሆኑ ትልቅ ዕድል ነው ብሏል።

ከደህንነት ጋር በተያያዘም አሁን ላይ ምንም አይነት ስጋት እንደሌለበት አቶ ይደሰት አስታውቆ፣ ምናልባት በቀጣይ አንዳንዶች ቴክኖሎጂው ይበልጥ ሲገባቸውና ዕውቀቱን እያገኙ ሲሄዱ ክራክ አድርገው የሚገቡበት ሁኔታ ይፈጠራል የሚል ስጋት እንዳለውም ገልጸዋል።

አቶ ይደሰት እንዳብራራው፣ መንግሥት ለጉዳዩ ትኩረት ሰጥቶ አቅራቢዎችን በአንድ አሰባስቦ ስልጠናና የግንዛቤ ማስጨበጫ መስጠቱ እጅግ የሚበረታታና የሚደገፍ ነው። በኮንስትራክሽን ዘርፍ የተሰማሩ አካላት በርካታ ቁጥር ያላቸው ቢሆኑም፣ እስካሁን ወደ ስርዓቱ የመጡት ጥቂቶች ናቸው። አሁን ላይ በርካቶች እየመጡ ነው፤ በቀጣይም ይመጣሉ። ለዚህም የግዢና ንብረት ባለስልጣን መስሪያ ቤት ኃላፊነት ወስዶ በቴክኖሎጂው ዙሪያ እየሰጠ ያለው ስልጠናና የግንዛቤ ማስጨበጥ ስራ እጅግ ጠቃሚና የሚበረታታ ነው።

ውይይቱን የመሩት የመንግሥት ግዥና ንብረት ባለሥልጣን ዋና ዳይሬክተር አቶ ሀጂ ኢብሳ በበኩላቸው እንዳሉት፤ የመንግሥት ግዢ ስርዓትን በማዘመን የኤሌክትሮኒክ የግዥ ስርአትን ተግባራዊ ለማድረግ ለሶስት ዓመታት ጥናት ተካሂዷል። ከጥናቱ በኋላ በ2014 በጀት ዓመት በዘጠኝ የፌዴራል ተቋማት ነው ሥራው የተጀመረው። በ2015 ደግሞ 74 የፌዴራል ተቋማት ወደ ትግበራ እንዲገቡ ተደርጓል። ከእነዚህ መካከል 70 የፌዴራል ተቋማት ሙሉ ለሙሉ ግዢያቸውን በኤሌክትሮኒክ መፈጸም ችለዋል። የቀሩት 95 ተቋማት በአሁኑ ወቅት በስልጠና ላይ የሚገኙ ሲሆን፣ እስከ ሰኔ 30 ቀን 2015 ዓ.ም ስልጠናውን አጠናቀው ለ2016 በጀት ዓመት ሙሉ ለሙሉ ወደ ስርዓቱ ይገባሉ።

‹‹በ2016 በጀት ዓመት 169 የፌዴራል ተቋማት ከተለመደው ግዢ ወጥተው ዘመናዊና ዓለማቀፋዊ በሆነ መንገድ ግዢያቸውን በኤልክትሮኒክ የሚፈጽሙ ይሆናል›› ያሉት ዋና ዳይሬክተሩ፤ ያደጉ አገራት ዘመናዊ የግዢ ስርዓቱን ላለፉት 50 ዓመታት ሲጠቀሙበት እንደነበር አስታውሰዋል። በቀጣዩ በጀት ዓመት ማንኛውም የመንግሥት ግዢ ከኤሌክትሮኒክስ ግዢ ውጭ እንደማይፈጸም አስገንዝበዋል።

‹‹የኤሌክትሮኒክስ የግዥ ሥርዓት ምንም አይነት የሰው ኃይል ሳያስፈልግ መተግበሪያውን በራሱ ኦዲት ማድረግ ስለሚያስችል ከሙስናና ከብልሹ አሠራር የፀዳ የግዥ ሥርዓት እንዲኖር ያስችላል›› ያሉት ዋና ዳይሬክተሩ፤ ይህም በግዥ ሰበብ የሚፈጸመውን ሌብነት ሙሉ ለሙሉ በመቅረፍ በተለይም ሰኔ ላይ የሚፈጠርን የግዢ ግርግር ሙሉ ለሙሉ የሚያስቀርና እጅግ ውጤታማ እንደሆነ አስረድተዋል።

በፌዴራል ተቋማት የጀመረው ይህ የኤሌክትሮኒክ የግዢ ስርአት ወደ ክልሎች፣ ዞኖች፣ ወረዳዎችና ቀበሌዎች እንደሚወርድ የጠቀሱት ዋና ዳይሬክተሩ፤ በተያዘው በጀት ዓመት ከክልሎች የሲዳማ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ወደ ስልጠናው መግባቱን ጠቁመዋል። በትግበራው የሚገኘውን ውጤት መሰረት በማድረግ የለማውን ሶፍትዌር በቀጣይ ለሁሉም ክልሎች ተደራሽ በማድረግ መጠቀም እንደሚቻል ነው ያስረዱት።

በአንድ አገር አንድ የግዢ ስርዓት ነው ሊኖር የሚገባው ያሉት ዋና ዳይሬክተሩ፤ በዚህ ልክ የተናበበ አንድ አገራዊ ኢኮኖሚ ለማድረግ ከ2017 ዓ.ም ጀምሮ ሁሉም ክልሎች ወደዚሁ ስርዓት እንደሚገቡም አስታውቀዋል። ከ2017 ዓ.ም በኋላ ወደ ወረዳ፣ ዞንና ቀበሌ በማውረድ በቀጣይ አራትና አምስት ዓመታት ጊዜ ውስጥ ደግሞ ኢትዮጵያ ውስጥ እስከ ቀበሌ ድረስ ባለው መዋቅር የግዢ ስርዓቱ ሙሉ ለሙሉ በዘመናዊ ቴክኖሎጂ የሚተካ እንደሆነ አመልክተዋል።

እንደ አቶ ሀጂ ማብራሪያ፤ ከተቋማቱ በተጨማሪ አቅራቢዎችም በዚሁ የግዢ ስርዓት ውስጥ መግባት አለባቸው። አንድ ጊዜ በፌዴራል ተቋም የተመዘገቡ ማለት ለክልል፣ ለዞን፣ ለወረዳና ለቀበሌ ማገልገል ይችላሉ። በቀጣዮቹ ዓመታት የቀደመው የግዢ ስርዓት በሥራ ላይ የማይውል በመሆኑ ከወዲሁ በግዢው ስርዓት ውስጥ በመግባት ተመዝግበው እንዲጠባበቁና ዕድሉን እንዲጠቀሙ አመላክተዋል። ለዚህም እንዴት መመዝገብ እንዳለባቸው ስልጠና ተዘጋጅቶ እየወሰዱ መሆናቸውን ጠቅሰው፣ ከስልጠናው በተጨማሪም በአካል ሄደው መረዳት የሚችሉበት መንገድ መፈጠሩን ተናግረዋል።

ዋና ዳይሬክተሩ እንዳብራሩት፤ በዚህ መሰረት አቅራቢዎች በሙሉ የአሰራር ስርዓቱን አውቀውና ተረድተው ወደ ሥራው እንዲገቡ ተደርገዋል። ትግበራው ሀምሌ ላይ ሲጀመር ለ74 ተቋማት 100 አቅራቢዎች ብቻ ተመዝግበው ነበር። አሁን 15 ሺ የአገር ውስጥ አቅራቢዎች እና አንድ የውጭ አገር አቅራቢ ወደ ትግበራው ገብተዋል። ይህም በግዢ ወቅት የሚፈጸም ሌብነትን ሙሉ ለሙሉ ከማስቀረት ባለፈ ለዓለም አቀፋዊ የግዢ ስርዓት ዝግጁ መሆን መቻሉን ማሳየት ያስቻለ ነው።

አንድ አቅራቢ ባልተመዘገበበትና ፈቃድ ባላወጣበት ሁኔታ መወዳደር እንደማይችልም አቶ ሀጂ አስታውቀዋል። የዓመቱን ግብር ገብሯል ወይስ አልገበረም የሚሉና የተለያዩ ሂደቶችን ለማወቅ ከገቢዎች ሚኒስቴር፣ ከገንዘብ ሚኒስቴር፣ ከባንክ፣ ከቴሌ ብር፣ ከኢንሹራንስና ከንግድ ሚኒስቴርና የተገናኘ ስለመሆኑ ዋና ዳይሬክተሩ አስታውቀዋል። ይህም የሰውዬውን ማንነት በግልጽ የሚያሳይ መሆኑን ጠቅሰው፣ አካሄዱ የሰለጠነና ኢትዮጵያን ካደጉ አገራት ተርታ የሚያሰልፍ እንዲሁም ሌብነትን የሚያስቀር መሆኑን አመልክተዋል።

በአሁኑ ወቅት የክልል የመንግሥታት ከወረቀት የግዥ ሥርዓት ተላቀው የኤሌክትሮኒክ የግዥ ሥርዓትን እንዲከተሉ የማድረግ ሥራ እየተሰራ እንደሆነም ዋና ዳይሬክተሩ ገልጸው፣ በ2017 በጀት ዓመት ክልሎች ሙሉ ለሙሉ ወደ ሥርዓቱ እንደሚገቡ አስገንዝበዋል። የኤሌክትሮኒክ የግዥ ሥርዓት ብልሹ የግዢ አሰራርን በመቅረፍ የመንግሥት በጀት ለታለመለት አገልግሎት እንዲውል እንደሚያደርግም ተናግረዋል። ከዚሁ ጋር በተያያዘ ከፌዴራል የመንግሥት ተቋማት በተሻለ የግል አቅራቢዎች ግዥዎቻቸውን በኤሌክስትሮኒክ እየፈጸሙ እንደሆነም ጠቅሰው፣ የመንግሥት ተቋማትና አቅራቢዎች ግዥዎቻቸውን በኤሌክስትሮኒክ የግዥ ስርአት በማድረግ በግዥ ሰበብ የሚፈፀምን ሌብነት መቀነስ ይገባቸዋል ሲሉ አጽንኦት ሰጥተው ተናግረዋል።

ዋና ዳይሬክተሩ እንዳብራሩት፤ ሌብነት በተንሰራፋበት በዚህ ወቅት የኤሌክትሮኒክ ግዢ ፍቱን መድሃኒት ነው። ግዢ ሲባል ቀድሞ የሚመጣው ሌብነት የሚለው ነው። ሁሉም ነገር ግልጽ በሆነ መንገድ መሄድ ከቻለ ሌብነት በራሱ ጊዜ ይጠፋል። ግልጽነቱ ጊዜና ቦታ የማይገድበው ሲሆን፣ የአንድ ሚሊዮን ብር ጨረታን አሜሪካና አውሮፓ ሆኖ መከታተልና መመልከት ይቻላል። ግልጽነቱ በዚህ ልክ የሰፋ በመሆኑ በመንግሥትና በህዝብ መካከል እንዲሁም በንግዱ ማህበረሰብና በህዝብ መካከል ተቋርጦ የነበረውን እምነት ማስቀጠል ይቻላል።

ተቋማት ግዥዎቻቸውን በኤሌክትሮኒክ ስርአት ሲያደርጉ ከአምስት እስከ 25 በመቶ የሚሆን በጀት ከምዝበራ ማዳን እንደሚቻል የጠቆሙት ዋና ዳይሬክተሩ፤ በትንሹ አምስት በመቶ ያህሉን ማዳን ቢቻል እንኳ እስከ 40 ቢሊዮን የሚደርስ የመንግሥትና የህዝብ ሃብትን ከብክነት ማዳን እንደሚቻል አመላክተዋል።

በአገር ደረጃ መሰረታዊ ለውጥ ለማምጣት እንዲያስችል ታስቦ ከአስር ዓመቱ አገራዊ የልማት ዕቅድ ከተያዙ ስትራቴጂክ ግቦች አንዱ የሆነው የዲጅታል ኢኮኖሚ ግንባታ ላይ አስተዋጽኦ እያበረከተ ያለው የመንግሥት ግዢና ንብረት ባለስልጣን የመንግሥት ግዢን ወረቀት አልባ፣ ግልጸኝነትና አሳታፊነትን ወደሚያሳድገው ኤሌክትሮኒክ የመንግሥት ግዢ (Electronic Goverenment Procurement /e-GP) ስርዓት እንዲሸጋገር እያደረገ ይገኛል።

መዝናኛ

# ማረፊያ/ትዝብት

## ትምህርት ቤት ሲዘጋ መጽሐፍ እንዳይዘጋ!

**ዋስልኝ አየለ**

የሰኔ እና የመስከረም ወር ከትምህርት ጋር በጥብቅ ይቆራኛሉ። መስከረም የትምህርት መጀመሪያ ነው፤ ሰኔ ደግሞ መጨረሻ። በመስከረም ተማሪዎች ለመገናኘት ይነፋፈቃሉ፤ በሰኔ ደግሞ ከትምህርት እፎይ ብለው ትንሽ ዘና ለማለት የሚጓጓበት ነው። የሰኔ ወር አገር አቀፍ ፈተና ከሚሰጥባቸው ክፍሎች በስተቀር ደከም ያለ ተማሪ ጉዱን የሚያውቅበት ነው። አልፏል አላለፈም የሚለውን ለማወቅ ማለት ነው። ጎበዝ ተማሪም የዓመቱን የደረጃ ውጤት ለማወቅ በጉጉት የሚጠብቀው ነው። ለዚህም ነው ሰኔ ሰላሳ የተማሪ አበሳ ይባል ነበረው።

በዚሁ እግረ መንገድ ስለትምህርት እናውራ። የትምህርት ጉዳይ የዘወትር አጀንዳ መሆን ቢገባውም በሰኔ እና በመስከረም ደግሞ የበለጠ ይደጋገማል። ሰኔ የልጆቹ ውጤት የሚታወቅበት ስለሆነ ማለት ነው።

በዚህ ዘመን ያለውን የተማሪዎች ሁኔታ በተመለከተ ከመምህራን ጓደኞቼ ብዙ ትዝብቶችን እሰማለሁ፤ ራሳቸውንም እታዘባቸዋለሁ። መምህር በዚህ ልክ ግዴለሽ መሆን አለበት? ብየ እገረማለሁ፤ ጓደኞቼንም በቀልድም በቁም ነገርም መምህር እንዲህ ነው ማድረግ ያለበት እያልኩ እነግራቸዋለሁ። እነርሱ የሚነግሩኝ ግን ምን ያህል አሰልቺ እንደሆነ ነው። በተለይም አንዳንድ ተማሪዎች ተስፋ አስቆራጭ መሆናቸውን ነው። የነገሩኝን ልጠቃቅስ።

በአንድ ወቅት ወደ አገር ቤት በሄድኩበት አጋጣሚ አንድ ጓደኛዬን አገኘሁት። ይህ ጓደኛዬ አብረን የተማርን ሲሆን እሱ እዚያ የተማርንበት ትምህርት ቤት ውስጥ መምህር ሆነ። በተገናኘን ቁጥር ያለፈ ትዝታችንን እያነሳን እንጫወታለን። በዚያ አጋጣሚምም ተገናኝተን ተጫወትን።

በጨዋታችን ውስጥም ያው ‹‹ሥራ እንዴት ነው?›› የሚለው በሁለታችንም በኩል ተነሳ። በተገናኘን ቁጥር የሚነግረኝ ነገር የተማሪዎችን ጎበዝ አለመሆን ነበር። እኔም የቅርብ ጓደኛዬ ስለሆነ ‹‹መምህሩ ጎበዝ ሲሆን ነው ተማሪ ጎበዝ የሚሆን›› እያልኩ በቀልድም በቁም ነገርም እነግረዋለሁ። እሱም ‹‹ስላላየኸው ነው የምትፈርድ! ምንም ማንበብና መጻፍ የማይችልን ተማሪ ከየት ጀምሮ ነው ጎበዝ ማድረግ የሚቻል?›› እያለ ይሞግተኛል (እሱ የሚያስተምረው ሁለተኛ ደረጃ ነው)። ይሄም ከታች ክፍል ያሉ መምህራን ችግር ነው እየተባባልን እንከራከራለን። ሁለተኛ ደረጃ ላይ የማያነቡ ተማሪዎች አጋጥመውታል ማለት ነው።

አንዳንዴ የሚነግረኝ ግን ከዚህም ከበድ ያለ ይሆናል። ‹‹ተማሪዎችን ‹ምን መሆን ትፈልጋላችሁ?› ብትላቸው፤ እንደ ድሮው ‹ዶክተር፣ ኢንጂነር...› የሚሉ እንዳይመስልህ! ምኞታቸው፤ ሴቶች ወደ አረብ አገር፣ ወንዶችም ወደ ወርቅ ቁፋሮ ነው የሚሉህ›› አለኝ። ምኞታቸው ብር የሚያገኙበትን አጋጣሚ ማመቻቸት ነው። ትምህርት የማይማሩ ጓደኞቻቸው ሄደው የመጡበት አካባቢ መሄድ ነው ፍላጎታቸው። ወላጆችም ገንዘብ ካመጡልን በማለት ብዙም አይቆጧቸውም፤ እንዲያውም ይባስ ብሎ የሚፈቅዱላቸውና ሂዱ የሚሏቸውም አሉ። በብዛት የሚማሩት ከ5ኛ ክፍል በታች ያሉት ናቸው። እነሱም ዕድሜያቸው ገና ለመሄድ ስላልደረሰ ነው። ይህ እንግዲህ በገጠሩ አካባቢ ነው።

ይሄ የመሄድ ፍላጎት ገና በልባቸው ሲጠነሰስ ለትምህርቱ ትኩረት አይሰጡም። መሄድ ሳይችሉ ቢቀሩ እንኳን ፈተና አያልፉም፤ ምክንያቱም ቀልባቸው ሌላ ነበር። እንኳን ሀገር አቀፍ ፈተናዎች ላይ የክፍል ውስጥ ፈተና እንኳን የሚያመጡት ውጤት ዝቅተኛ ነው።

ከዚህም በላይ አሳዛኙ ደግሞ የተማሪዎች ብቻ ሳይሆን የመምህራኑም ተስፋ መቁረጥ ነው። ‹‹ምክንያቱ ምን ይሆን›› ያልኩት ጓደኛዬ እንደሚለው የብዙ መምህራን ቅሬታ ከደሞዝና ጥቅማጥቅም ጋር፣ ከሥራ መሰላቸት ጋር የመጣ ነው። የሥራ መሰላቸቱንም ያመጣው ከኑሮ ውድነት ጋር የሚከፈለን ክፍያ አይመጣጠንም በሚል ቅሬታ ነው።

ይሄ ነገር ትውልድ ገደላ ነው። መምህራን በኑሮ ውድነት ላይ ያላቸውን ቅሬታ የሚገልጹት ተማሪ ላይ ከሆነ ይሄ የእውቀት አባትነት ሳይሆን ጨለማን ማውረስ ነው። እርግጥ ነው የሚከፈለው ክፍያ በቂ ነው ማለት አይደለም። በቂ አለመሆኑ ግን የተማሪዎችና የወላጆች ችግር አይደለም፤ ችግሩን መነጋገር ከመንግሥት ጋር ነው። እልሃቸውን ተማሪ ላይ አይደለም መወጣት ያለባቸው። የጠየቁት ጥያቄ ካልተመለሰ ወይም በውይይት መፍትሔ ላይ ካልደረሱ ሥራውን መልቀቅና የተሻለ ካለ መፈለግ ነው!

በነገራችን ላይ ይሄ ችግር የሚታየው መምህራን ላይ ብቻ አይደለም። በብዙ የመንግስትም ሆነ የግል ተቀጣሪ ሰራተኞች ላይ የሚታይ ነው። የግል ላይ ቢዝረከረክ በነገታው እንደሚባረር ስለሚያውቀው ማንም አይዝረከረክም። የመንግስት ተቋማት ላይ ግን ይሄ ነገር ጎልቶ ይታያል። ብዙ ጊዜ የታዘብኩትን ነገር ልንገራችሁ።

የመንግስት መስሪያ ቤቶች ሾፌር ይቀጥራሉ። ሹፌሮችም ሰራተኞችን ወደ ሥራ ቦታ ይወስዳሉ። ይህ ሲሆን ታዲያ ሾፌሮች በለቅሶና በጭቅጭቅ ነው። ከመስሪያ ቤት ሲወጡ አለቃቸው ያዘዛቸውን ‹‹እሺ›› ብለው ይወጣሉ። ከዚያ በኋላ ከሰራተኛው ጋር ጭቅጭቅ ይፈጥራሉ። ‹‹እዚህ ቦታ አልሄድም፣ በዚህም አልሄድም፣ እዚህ አልጠብቅህም›› ይላሉ። ይባስ ብሎ በፉከራ ‹‹ማን አባቱ ነው የሚያዝዘኝ፣ እስኪ ማን እንዲህ አድርግ እንደሚለኝ አያለሁ!›› እያሉ ፉከራ!

የቅሬታቸውን ምክንያት ሲናገሩም፤ ‹‹በዚህ ደሞዝ አልሰራም! አንተ ይህን ያህል እየተከፈለህ እኔ ልፈጋልህ ነው!›› እና ታዲያ ሥራውን ለቆ የተሻለ ካለ መፈለግ ነዋ!

ወደ መምህራኑ ስንመለስ የእነርሱ ደግሞ ከዚህም ይከፋል። የእነርሱ ማኩረፍ እንደሌላው ማኩረፍ አይደለም። ትውልድ ላይ ነው እየሰሩ ያሉት።

የተማሪዎች ተስፋ መቁረጥ ግን የመምህራን ችግር ብቻም አይደለም። ይሄ የወላጆችም ችግር ነው። አለፍ ሲልም የትምህርት ተገቢውን ዋጋ አለማግኘት ነው። ከእነርሱ በፊት የተማሩ ሲያማርሩ ከሰሙ ከታች ያሉት ተስፋ ይቆርጣሉ። ተምሮ ሥራ የለም፤ በደመወዝ መኖር ከባድ ነው፣ ሥርዓተ ትምህርቱ ሀገር በቀል እውቀት ላይ ያተኮረ አይደለም... የሚሉ ቅሬታዎች ተደጋግመው የሚሰሙ ናቸው። ታዲያ ይሄን እየሰሙ ይሆን?

የትምህርት ነገር ገና ብዙ ያልተስተካከለ ነገር አለው። አዲስ በወጣው የትምህርት ፍኖተ ካርታ ላይ ከአንደኛ ደረጃ ጀምሮ ዲግሪ ያለው እየሆነ ነው። ይሄ ጥሩ ነገር ነው። የመምህራን ብቃትና ቆራጥ ውሳኔም አንዱ አጠያያቂ ነገር ስለነበር ማለት ነው። ከ10ኛ እና ከ12ኛ ክፍል ውጤት ያልመጣለት ተማሪ ነበር እኮ መምህር የሚሆነው! ከዩኒቨርሲቲ የተመረቀውም ቢሆን ብዙም የተሻለ አይደለም። ባዮሎጂ፣ ኬሚስትሪ፣ ፊዚክስ ትምህርት ክፍል የሚመደቡት ከ12ኛ ክፍል ዝቅተኛ ውጤት ያመጡት ናቸው። እነዚህ ወሳኝ እና ለሁሉም የትምህርት ክፍል መሰረት የሆኑት የትምህርት አይነቶች ‹‹ኮምፒቴሽናል ሳይንስ›› በሚለው ውስጥ ነበሩ። ይሄ ዘርፍ ማለፊያ ነጥቡን ብቻ ያመጡ ተማሪዎች ሳይመርጡት የሚመደቡበት ነው። እንደ ህክምና፣ ምህንድስና፣ ጤና፣ መሬት አስተዳደር፣ የመሳሰሉ የትምህርት ክፍሎችን መርጠው የሞሉ ተማሪዎች ያንን ካላገኙ የሚመደቡት ‹‹ኮምፒቴሽናል›› እና ‹‹አዘር ሳይንስ›› የሚባለው ውስጥ ነው። መምህር የሚወጣው ደግሞ ከዚህ ዘርፍ ውስጥ ነው። አሁን አሁን ግን እነዚህ ነገሮች እየተስተካከሉ ነው፤ መምህር ለመሆን ከዩኒቨርሲቲ ጀምሮ ትኩረት እየተሰጠው ነው።

ለማንኛውም የመምህራንን እና የሥርዓተ ትምህርቱን ጉዳይ ለሚመለከተው አካል እንተወውና ተማሪዎችና ወላጆች ግን ክረምቱን እረፍት ነው ብለው ሙሉ በሙሉ ከትምህርት እንዳይርቁ። ተማሪዎች የሚቀጥለውን ዓመት ክፍል በክረምት ማጥናት እንዲጀምሩ ወላጆች መንገር አለባቸው። ለምሳሌ ከ5ኛ ወደ 6ኛ ክፍል የተዛወረ ተማሪ የ6ኛ ክፍል ማንበብ እንዲጀምር ማለት ነው። ወላጆች ደግሞ ለትምህርት አጋዥ የሆኑ መጻሕፍትን ሊገዙላቸው ይገባል፤ ምክንያቱም የሚፈልጉት ደረጃ ላይ የሚደርሱት ዘመኑ የሚጠይቀውን ግብዓት ሲያገኙ ነው። ስለዚህ ክረምት የእረፍት ብቻ ሳይሆን የንባብም ወቅት ይሁን!

# ዓለም አቀፍ

## የቻይና የስለላ ፊኛዎች በእስያ ሰማይ ላይ መታየታቸውን አዳዲስ ምስሎች አሳዩ

**በጋዜጣው ሪፖርተር**

በጃፓን እና በታይዋን ላይ የተደረገውን በረራ ጨምሮ የቻይና የስለላ ፊኛ ፕሮግራምን በተመለከተ የወጣ አዲስ መረጃ በቢቢሲ ፓናሮማ ተጋለጠ።


ጃፓን ፊኛዎች በግዛቷ ሲበሩ መመልከቷን ያረጋገጠች ሲሆን፣ ወደፊትም ፊኛዎቹን መትታ ለመጣል መዘጋጀቷን ገልጻለች። ቻይና ግን በቢቢሲ ለቀረበው መረጃ ቀጥተኛ ምላሽ አልሰጠችም። በዚህ ዓመት መጀመሪያ ላይ የቻይና የስለላ ፊኛ በአሜሪካ የባሕር ዳርቻ ላይ ተመትቶ መጣሉ ይታወሳል። ይህንንም ተከትሎ የአሜሪካ እና የቻይና ግንኙነት ችግር ውስጥ ገብቶ ነበር።

ቻይና ጥር ወር መጨረሻ ላይ በሰሜን ምዕራብ አሜሪካ ሰማይ ላይ የታየው ፊኛ የአየር ሁኔታን ለመሳሰሉ ሳይንሳዊ ምርምር የሚያገለግል የሲቪል የአየር መርከብ መሆኑን ጠቅሳ፣ ያጋጠመው ክስተት ያልታሰበ ነው ብላ ነበር። በአሜሪካ የስለላ ተቋም (ሲአይኤ) የቀድሞው የምሥራቅ እስያ ተንታኝ የሆኑት ጆን ኩልቨር ይህ የአንድ ጊዜ በረራ ብቻ ሳይሆን በተከታታይ ቢያንስ ለአምስት ዓመታት ያህል ሲካሄድ የነበረ መሆኑን ለቢቢሲ ፓናሮማ ተናግረዋል።

ተንታኙ ጨምረውም “የቻይና ፊኛ በተለየ የሚሰሩት ለእንዲህ ዓይነት የረጅም ጊዜ ተልዕኮ ነው። እናም አንዳንዶቹ ዓለምን ያሰሱ ይመስላል” ብለዋል። ቢቢሲ በሳተላይት የተነሱ በርካታ መረጃዎችን ከሚመረምረው የሰው ሰራሽ አስተውሎት (አርተፊሻል ኢንተለጀንስ) ድርጅት - ሳይንቴቴክ ጋር በመሥራት ፊኛዎቹ ምሥራቅ እስያን ሲያቋርጡ የሚያሳዩ በርካታ ምስሎችን ማግኘት ችሏል።

የድርጅቱ መሥራች የሆኑት ኮሪይ ጃስኮልስኪ እንደ አውሮፓውያኑ መስከረም 2021 አንዲት ፊኛ በጃፓን ሰሜናዊ ክፍል ስታቋርጥ የሚያሳይ መረጃ አግኝተዋል። ይሁን እንጂ እነዚህ ምስሎች ከዚህ ቀደም ይፋ አልተደረጉም።

ጃስኮልስኪ ፊኛው ከሞንጎሊያ በስተደቡብ ከቻይና የተነሳ መሆኑንም ያምናሉ። ቢቢሲ ግን ይህንን ማረጋገጥ አልቻለም።



## ቭላድሚር ፑቲን ላይ አመጽ ቀስቅሶ የነበረው የዋግነር ቡድን ትጥቅ ሊፈታ ነው ተባለ

**በጋዜጣው ሪፖርተር**

ባለፈው ቅዳሜ በቭላድሚር ፑቲን አስተዳደር ላይ አመጽ ቀስቅሶ ሩሲያን ለ24 ሰዓታት ትርምስ ውስጥ ከቷት የነበረው ዋግነር ቅጥረኛ ተዋጊ ቡድን የከባድ መሳሪያ ትጥቅ ሊፈታ ነው ተባለ።

የሩሲያ መከላከያ ሚኒስቴር እንዳስታወቀው ዋግነር የከባድ ጦር መሳሪያዎችን እንዲያስረክብ ቅድመ ዝግጅቶች እየተከናወኑ ነው ብሏል። ይህ የተባለው በወታደራዊ አመጻ ተግባር ላይ ተሳታፊ የነበሩት የዋግነር አባላት ክስ እንደማይመሰርትባቸው ከተገለጸ በኋላ ነው።

ፕሬዚዳንት ቭላድሚር ፑቲን ዛሬ ከሰዓት ባደረጉት ንግግር የዋግነር አባላትን ወደ ወንጀል ተግባር ተሳስተው እንዲገቡ የተደረጉ “እውነተኛ አገር ወዳድ ተዋጊዎች ናቸው” ብለዋል። አክለውም የቡድኑ አባላት ካሻቸው ወደ መደበኛ ጦር ሠራዊት መቀላቀል፣ ወደ ቤተሰቦቻቸው መመለስ አልያም ወደ ቤላሩስ ማቅናት ይችላሉ ብለዋል።

ፑቲን 2500 የሚሆኑ ወታደሮችን፣ የፖሊስ አባላትን፣ የሩሲያ ብሔራዊ ዘብ እና የደኅንነት ኃላፊዎችን ሰብስበው ስለታማኝነታቸው እና አመጹን ስለማስቆማቸው ምስጋናቸውን



አቅርበዋል።

ፑቲን ንግግራቸውን ሲያደምጡ ለነበሩት፤ “የሩሲያን ሕገ-መንግሥታዊ ሥርዓት አስከብራችኋል፣ የሩሲያውያን ሕይወት እና ነጻነት አስጠብቃችኋል” ካሏቸው በኋላ “የእርስ በርስ ጦርነት አስቁማችኋል” ሲሉ አሞግሰዋቸዋል።

ዋግነር የተባለው ቅጥረኛ ተዋጊ ቡድን የቀሰቀሰውን አመጽ ለማስቆም ስለተደረሰው ስምምነት ግን ፑቲን በንግግራቸው ያሉት ነገር የለም። በየቭጌኒ ፕሪጎዢን የሚመራው ዋግነር ባሳለፈው ቅዳሜ በሩሲያ የጦር አመራሮች ላይ በይፋ ካመጸ በኋላ፣ ሁለት የሩሲያ ከተሞችን ተቆጣጥሮ ወደ ሞስኮ ሲገሰግስ ነበር።

የቡድኑ መሪ የቭጌኒ ፕሪጎዢን በዩክሬኑ ጦርነት “ስህተት” የፈጸሙ የጦር አመራሮች ለመቅጣት ወደ ሞስኮ “ለፍትሕ” ሲል እንደሚያመራ ገልጾ ነበር። ይሁን እንጂ የቡድኑ መሪ በቤላሩሱ ፕሬዚዳንት አሸማጋይነት ከፑቲን ጋር ከተነጋገሩ በኋላ ወደ ሞስኮ የሚያደርጉትን ዘመቻ አቁመው ወደ ቤላሩስ ማቅናታቸው ተገልጿል።

ዛሬ ከሩሲያ የወጡ ይፋዊ ሪፖርቶች በአመጹ ላይ ተሳታፊ በነበሩ የዋግነር አባላት ላይ ክስ እንደማይመሠረት አረጋግጠዋል። የሩሲያ የአገር ውስጥ የደኅንነት ቢሮ (ኤፍኤስቢ) በአመጽ ተግባሩ ላይ የተሳተፉ ሰዎች ላይ ተመስርቶ የነበረው ክስ ሙሉ በሙሉ ውድቅ ተደርጎ መዝገቡ ተዘግቷል ብሏል።

የደኅንነት ቢሮው ዛሬ ይህን ይበል እንጂ ፕሬዚዳንት ቭላድሚር ፑቲን ትናንት ምሽት በቴሌቪዥን መስኮት ቀርበው አመፅ ያነሱትን የዋግነር ቡድን አባላት አገራቸውን ለከባድ ጉዳት በማጋለጥ ተጠያቂ ይሆናሉ ብለው ነበር።

ፑቲን በትናንቱ ንግግራቸው “ሩሲያ በደም ጎርፍ ስትታጠብ ማየት የጓጉ” ናቸው ያሏቸውን የአመጹ መሪዎችን “ለፍትሕ” ይቀርባሉ ይበሉ እንጂ፣ በዛሬው ንግግራቸው የዋግነር አባላት ወደ ፈለጉት እንዲሄዱ አማራጮችን አቅርበዋል።

ዜና

# “የሚያጋጥሙንን ተግዳሮቶች...

ከ1ኛው ገጽ የዞረ

አሁን ያለው የዓለምአቀፉ አስተዳደር ቅርጹ ጊዜ ያለፈበት፣ ፍትሃዊ ያልሆነና እነዚህን ውስብስብ ፈተናዎች መፍታት የማይችል ነው ያሉት አቶ ደመቀ፤ ዓለም አቀፋዊ ተለዋዋጭነት በመኖሩ የባለ ብዙ ወገን ትብብርን የሚደግፉ አዳዲስ የአስተሳሰብ መንገዶችን ይፈልጋል ብለዋል።

ለተለዋዋጩ ዓለም ሕጋዊ ጥያቄዎች ምላሽ የሚሰጥ፣ ሁሉን አቀፍ፣ ፍትሃዊ እና ውጤታማ የሆነ ሥርዓት መፍጠር ከዓለም አቀፍ አጀንዳዎች ግንባር ቀደም መሆን እንዳለበትም ጠቁመዋል። የህዝቦቻችንን የሰላም፣ የጸጥታ እና የብልጽግና ምኞቶች ወደ ላቀ ደረጃ ለማሸጋገር ለ21ኛው ክፍለ ዘመን የሚመጥን እውነተኛ ዓለም አቀፍ ትብብር መፍጠር አለብን ሲሉ አሳስበዋል።

እንደ አቶ ደመቀ ገለጻ፤ ኢትዮጵያ የብዙሃዊነት ደጋፊ እና አሸናፊ ሀገር ናት፡፡ ሰላም አስከባሪ ወታደሮችን በመላክ ለዓለም አቀፍ ሰላምና ደህንነት መጠበቅ የበኩሏን አስተዋፅኦ እያደረገች መሆኑን ጠቁመው፤ ከጎረቤት ሀገራት የሚመጡ ስደተኞችን በማስተናገድ ላይ ባላት ቁርጠኝነት ዓለም አቀፋዊ ትብብርን እያሳየች ነው ሲሉም ተናግረዋል።

ኢትዮጵያ የዓለም አቀፉን የትምህርት ትብብር ድርጅት (ኦኢሲ) የተቀላቀለችው የባለብዙ ወገንተኝነት መንፈስ በመላበስ የሚያጋጥሙንን ተግዳሮቶች በትብብርና አጋርነት መንፈስ ለመፍታት ነው ሲሉም አቶ ደመቀ ገልጸዋል፡፡

የዓለም አቀፉ የትምህርት ትብብር ድርጅት (ኦኢሲ) ዋና ጸሃፊ ማንሱር ቢን ሙሳላም በበኩላቸው፤ ትምህርት በህብረተሰቡ ውስጥ ያለውን ኢፍትሃዊነት ያጠናክራል ወይም ያፈርሰዋል። መካከለኛ ቦታ የለም ሲሉ አፅንዖት ሰጥተው ተናግረዋል።

የዘላቂ ልማት ግቦችን በተሟላ መልኩ ተግባራዊ በማድረግ የማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ልማት ምኞቶቻችንን እውን እንዲሆኑ አባል ሀገራት በዚህ ረገድ የትምህርትን ደጋፊነት ሚና ለመወጣት ያለማቋረጥ በቁርጠኝነት ድጋፍ ሊያደርጉ ይገባል ሲሉ ዋና ጸሃፊው ለተሳታፊዎች አስረድተዋል።

አያይዘውም ተመራማሪዎች፣ ምሁራን፣ ወጣቶች ዓለም አቀፍ የልማት አጀንዳዎችን በማጠናከር የበኩላቸውን ድርሻ ሊወጡ እንደሚገባ ጠቅሰው በዚህ ረገድ ድርጅቱ አስፈላጊውን የገንዘብ፣ የቴክኒክና የቁሳቁስ ድጋፍ እንደሚያደርግ አመልክተዋል።

ጉባዔው ትናንትን ጨምሮ ለአራት ቀናት ሲቆይ ለሁለት ቀናት በሚኒስትሮች ደረጃ የሚካሄድ ሲሆን በቀሪዎቹ ቀናት የተቋሙ አባል ሀገራት መሪዎች ምክክር እንደሚያደርጉ ከወጣው መርሐ-ግብር ለመረዳት ተችሏል።

# “የሀገርን ሉዓላዊነት የሚያስከብር...

ከ1ኛው ገጽ የዞረ

ትናንት አስመርቋል።

በምረቃ መርሃግብሩ ላይ የጦር ኃይሎች ኢታማዦር ሹም ፊልድ ማርሻል ብርሃኑ ጁላ፣ የሠራዊቱ ጥንካሬ ከኢትዮጵያ መኖርና አለመኖር ጋር የተያያዘ ነው፤ ሠራዊቱ ከመቼውም ጊዜ በበለጠ በመቀናጀትና በመሰናሰል የህዝብን ደህንነትና የሀገርን ሉዓላዊነት ለማስከበር ጠንክሮ ይሰራል ብለዋል፡፡ በዚህም የህዝብን ደህንነትና የሀገርን ሉዓላዊነት የሚያስከብር ጠንካራ ሠራዊት በመገንባት ለቀጣዩ ትውልድ እናስረክባለን ሲሉ አረጋግጠዋል፡፡

ኢትዮጵያ ቀደም ሲል የባህር ኃይል የነበራት ሰፊና ሃያል ሀገር የነበረች ፤ በራሳችን ድክመት ችግሮቻችንን በመነጋገር በሰላም መፍታት እየተቻለ ቅራኔ እያደገ ሂዶ ባህር ኃይል እንድናጣ ምክንያት ሆኗል ያሉት ፊልድ ማርሻል ብርሃኑ፤ በ1982 ዓ.ም ኢትዮጵያ ወደቧ ተዘግቶ ባህር ኃይሏ እንዲበተን መደረጉን አስታውሰዋል፡፡ አሁንም የሚከሰቱ ችግሮችን በውይይት መፍታት ካልተቻለ ችግር ያስከትላል ብለዋል።

ከለውጡ በኋላ የመከላከያ ሠራዊት ራሱን የቻለ ዘመናዊ የመከላከያ ሠራዊት እንዲኖር ሰፊ ስራዎች ተሰርተዋል ያሉት ፊልድ ማርሻል ብርሃኑ፤ ከእነዚህም መካከል የቀደሞው የባህር ኃይል በአዲስ መልክ እንዲደራጅ መደረጉ አንዱ መሆኑን ተናግረዋል።

በተለያዩ የውጭ ሀገራት በአስር ሺዎች የሚቆጠሩ የባህር ሃይሎች እየሰለጠኑ እንደሚገኙ ጠቁመው፤ ኢትዮጵያን የሚመጥን ሠራዊት ገንብተን ለሚቀጥለው ትውልድ እናስረክባለን ነው ያሉት።

የኢትዮጵያ ሠራዊት በኢትዮጵያ ሉዓላዊነትና ደህንነት አይደራደርም ያሉት ፊልድ ማርሻል ብርሃኑ፤ ሠራዊቱ በጥብቅ ዲስፕሊን የሚመራ የኢትዮጵያ ከለላና መከታ መሆኑን ገልጸዋል።

ተመራቂ የባህር ሃይል ሠልጣኞችም በዲስፕሊን በመመራት የኢትዮጵያ ሉዓላዊነትና ደህንነት ለማስጠበቅ መሥራት እንደሚገባቸው አሳስበዋል።

ከቅርብ ጊዜ ወዲህ የሠራዊቱን ስም በማብጠልጠል ትርፍ እናገኛለን ብለው የሚያስቡ ሃይሎች ሠራዊቱ ፈርሷል፣ ተበትኗል፣ እርስ በርሱ ተጋጭቷል በሚል ዘመቻ ላይ ቢጠመዱም ሠራዊታችን በወሬ አይበተንም፤ አይደመሰስም፤ ይልቅስ ህዝባዊነቱን ጠብቆ ግዳጁን በጀግንነት የሚፈፅም ነው ብለዋል ፊልድ ማርሻል ብርሃኑ ጁላ።

የኢትዮጵያ ባህር ኃይል ዋና አዛዥ ሬር አድሚራል ክንዱ ገዙ በምረቃ ሥነ ሥርዓቱ እንደገለጹት፣ ኢትዮጵያ ነባር የባህር ኃይል ቢኖራትም ላለፉት አስር ዓመታት የባህር ኃይል ሳይኖራት ቆይቷል። መንግሥት በ2011ዓ.ም የባህር ኃይል እንደገና እንዲደራጅ አድርጓል።

ኢትዮጵያ ምንም እንኳን የባህር በር ባይኖራትም 95 በመቶ የሚሆነው የወጪ ንግዷ የሚከናወነው በባህር በር በመሆኑ የባህር ኃይል ወሳኝ ሚና እንዳለው አመልክተው፤ የቀይ ባህር ቀጣና አሜሪካን ጨምሮ የበርካታ ሃያላን አገራት ትኩረት የሚስብ በመሆኑ በተለይም የባህር ላይ ውንብድናን ለመከላከል ብቁ የባህር ሃይል ማደራጀት አስፈላጊ መሆኑን ገልጸዋል፡፡

ከብሔራዊ ጥቅም አኳያ እየተወሳሰበ ከመጣው የውሃ ላይ ውንብድና እና ተግዳሮቶች አኳያ ሀገራችን ኢትዮጵያ የባህር ኃይል ያስፈልጋታልም ብለዋል።

ብሔራዊ ጥቅማችንን የሚጎዳ ኃይል ከውሃማ አካል ወደ ውሃማ ወይም ከውሃማ አካል ወደ የብስ ሊቃጡ የሚችሉ ስጋቶችን የባህር ኃይላችን ይከላከላል ያሉት ሬር አድሚራል ክንዱ፤ ከዚህ አኳያም ባህር ኃይል ብቁ ተዋጊዎችና የማሪን ኮማንዶ በማሰልጠን ላይ እንደሚገኝ ገልጸዋል።

የኢትዮጵያ የባህር ኃይል አካዳሚ አዛዥ ኮማንደር ከበደ ሚካኤል በበኩላቸው፣ አካዳሚው ከሚያከናውናቸው ተግባራት መካከል የመሰረታዊ የባህረተኞችን ማሠልጠን አንዱ መሆኑን ጠቁመው፤ በዚህም የመጀመሪያ ዙር ባህረተኞችን የባህር ደህንነት፣ በኢንጂን፣ በናቪጌሺን ፣ በኢንጂነሪንግ፣ በኤሌክትሪክ ሲቲ፣ በኮሙኒኬሽንና በአርማመንት አሰልጥኖ አስመርቋል፤ የላቀ ውጤት ያስመዘገቡ ባህርተኞች ከጠቅላይ ኢታማዦር ሹም ፊልድ ማርሻል ብርሃኑ ጁላ ሽልማታቸውን ተቀብለዋል።

የኢትዮጵያ ባህር ሃይል ጠንካራና ብቃት ያለው በየትኛውም የውሃ አካል ላይ ግዳጅን መወጣት የሚችልና በኢፌዴሪ መከላከያ ኃይል ላይ ተጨማሪ የማድረግ አቅም የሚፈጥር የባህር ኃይል መገንባት ራእይ ይዞ እየሰራ ያለ ተቋም ሲሆን ዋና ተልእኮው በሀገሪቱና ብሄራዊ ጥቅሞቿ ላይ በአካባቢው ከሚገኙ የውሃ አካላት ሊሰነዘር የሚችል ጥቃትን መከላከልና መመከት ነው።

ማህበራዊ

# ባለውለታዎቻችን

## ያልተዘመረለት- አርበኛው ደራሲ ተመስገን ገብሬ

ሶሎሞን በየነ




የፕየሞንቴው መስፍን የጣሊያን መንግሥት አልጋ ወራሽ ባለቤት በመውለዷ በአዲስ አበባ ገነተ ልዑል ግቢ ውስጥ የካቲት 12 ቀን 1929 ዓ.ም ድግስ ተደግሷል። ሕዝቡም በቦታው ተሰብስቧል። ግራዚያኒ ሰገነቱ ላይ ንግግር እያደረገ በነበረበት ወቅት ሞገስ አስገዶም እና አብርሀ ደቦጭ አከታትለው የእጅ ቦምብ ወረወሩ። ከግራዚያኒ በተጨማሪ ሌሎች ሹማምንት ሁሉ ቆሰሉ። ግራዚያኒ ላይ ቦምብ ከጣሉት ሰዎች ጀርባ እጁ አለበት በሚል ፋሺስት ጣሊያኖች ይዘው ሊሰቅሉት በእግር በፈረስ ያፈላልጉት ጀመር።

ይህንን ግለሰብ የገባበት ሁሉ ገብተው ለመያዝ ጣሊያኖች አደናቸውን አጠናክረው ቀጠሉ። በመጨረሻም በጥብቅ የሚፈልጉት ግለሰብ በእጃቸው ቢገባም ማንነቱን ግን አላወቁትም ነበር። እርሱም ጣሊያኖችን አንድ ጥያቄ አቀረበላቸው፤ “ማንን ነው የፈለጋችሁት”? አላቸው። እነርሱም፣ የእርሱን ስም ጠርተው “እገሌ የሚባል ሰው” አሉት። እርሱም “የምትፈልጉትን ሰው ጠንቅቄ አውቀዋለሁ፤ አብሬያችሁ በከተማው ዘወር ዘወር ብል እናገኘዋለን” አላቸው። ጣሊያኖቹም እውነት መስሏቸው የሚፈልጉትን ሰው በእጃቸው ይዘው እራሱን መፈለግ ጀመሩ። እርሱም በዛ አጋጣሚ በሥርቤት ከተመለከተው የፋሺስቶች በደል ባለፈ በከተማዋ የተፈፀመውን ዘግናኝ ጭፍጨፋ በአይኑ ተመለከተ። በኋላም የሚፈልጉት ሰው እንደነበር ሳያውቁት ከሌሎች እስረኞች ጋር አብሮ እንዲረሸን እጣው ደረሰ።

እርሱም በወቅቱ የነበረውን ሁኔታ ሲገልጸው “ጣልያኖች እየጠሩ ከሚወስዷቸዉ ሰዎች መካከል ሆኘ ተወሰድኩ። ከሰው መሀል ጠርተው ወስደው መረሸን ልማዳቸው ስለነበረ ወደ ሞት እየሄድን እንደሁ ታውቆኛል። የተቆፈረ ጉድጓድ አፋፍ ስር ቁመናል። ከጀርባችን ደግሞ አናታችን ላይ ተነጣጥረው የተደቀኑ መድፎች አሉ። እስከዛሬ ሰዎች ሲገደሉ አይቻለሁ። አሁን ተራው የእኔ ነው። ሞት ምን ይመስል ይሆን? መድፎች ተናገሩ፤ ተተኮሰ። ወደ ጉድጓዱ ወደቅን። መድፉ ብዙዎችን የገደለ ቢሆንም እኔ ግን አልተመታሁም። እንደ ሞተ ሰው ከሟቾች ጋር ተኛሁ። ሲጨላልም ከወደቅኩበት ጉድጓድ ወጥቼ አመለጥኩ” በዚህ ቅፅበት ከመረሸን የተረፈው አርበኛ፣ ደራሲ፣ ጋዜጠኛ፣ ጠበቃ እና ባለቅኔው ተመስገን ገብሬ የካቲት 12 ቀን 1929 ዓ.ም ፋሽስት ጣሊያን በአዲስ አበባ ላይ የፈፀመውን የግፍ ጭፍጨፋ በአይኑ አይቶ ሕይወቴ በሚለው በግል ታሪኩ ላይ በሚያጠነጥነው መጽሃፉ ላይ ያሰፈረው ነው።

በየአመቱ የካቲት 12 ቀን ሲታወስ በቀዳሚነት ከሚዘከሩ አርበኞችና የሀገር ባለውለተኞች ውስጥ አንዱ ታላቁ አርበኛና ደራሲ ተመስገን ገብሬ፤ ደብረ ማርቆስ ከተማ ውስጥ ግንቦት 15 ቀን 1901 ዓ.ም ተወለደ። ቤተሰቦቹ ካህን ስለነበሩ ተመስገን አራት ዓመት፣ ከአራት ወርና በአራተኛው ቀን ከቤታቸው አጠገብ ከሚገኘው ቤተክርስቲያን ከነ የኔታ (መርጌታ) እግር ስር ቁጭ ብሎ የፊደል ገበታን ቀስሟል።

ተመስገን ገና አስር ዓመት ሳይደፍን ከወላጆቹ ጠፍቶ በጨቅላ እድሜው ቀየውን ለቆ ሞጣና ቢቡኝ እየተዘዋወረ የቤተ ክህነት ትምህርት እስከ ቅኔ ድረስ ተምሯል። በኋላም በቢቡኝ ውስጥ ረዳት የቅኔ መምህር ሆኖ አስተምሯል። በትምህርቱና ቅኔ አዋቂነቱ የአንቱታን ካባ የደፋ ድንቅ ሰው ነበር። በትምህርቱ እጅግ ጐበዝ የሚባል በመሆኑ ገና በ15 ዓመቱ የቅኔ መምህር ለመሆን በቅቷል፡፡ በቤተ-ክህነት ትምህርት በዚህ እድሜ የቅኔ መምህር የሆነ ሰው ከተመስገን ሌላ አልተገኘም ይባላል፡፡

እርሱም “ሕይወቴ” በሚለው መጽሃፉ “ትምህርት ቅኔ ነው እንጅ”! ይላል፡፡ ከቅኔ በላይ ምን ትምህርት አለ ማለቱ ነው፡፡ በቅኔ ትምህርት የሚመሰጥ ሰው ነበር፡፡ በዚህ መጽሀፍ ገጽ-19 “ቅኔ የኢትዮጵያ ታላቅ የመጨረሻው ትምህርት ነው” ይላል፡፡ እንዲሁም በገጽ-23 “ቅኔ ካወኩ በኋላ ትዕቢተኛ ሆንኩ” ሲል ቅኔ አዋቂ በመሆኑ የሚሰማውን ኩራት ተሜ ይናገራል፡፡

በሞጣና ቢቡኝ እየተዘዋወረ ቅኔውን ፉት ካደረገ በኋላ ወደ ትውልድ መንደሩ ደብረ ማርቆስ ተመልሶ በራስ ኃይሉ ተክለኃይማኖት ዙፋን ዙሪያ ደንበኛ አቤቱታ ፀሐፊ በመሆን ገና በለጋ እድሜው ህዝብን አገልግሏል። በወቅቱ የነበረውን የእጅ መንሻ (ጉቦ) አጥብቆ ይቃወም ስለነበር ከመኳንንቱ ጋር ባለመስማማቱ ወደ አዲስ አበባ ተሰደደ። በ1918 ዓ.ም ወደ አዲስ አበባ አቅንቶም በትርፍ ጊዜው እየሠራ በስዊድን ሚሲዮን ትምህርት ቤት ገብቶ ዘመናዊ ትምህርቱን ተከታትሎ ጨርሷል።

አርበኛና ደራሲ ተመስገን ገብሬ የዓለምን ወቅታዊ ሁኔታና የፖለቲካ አሰላለፍ በንቃት የሚያውቅና የሚከታተል ባለብሩህ አእምሮ ስለነበር “አድዋ ላይ የሽንፈትን ካባ የተከናነበችው ኢጣሊያ ዳግም ኢትዮጵያን እንደምትወር ቀድሞ ያወቀና የነቃ ሰው ነበር። በዚህም በ1920ዎቹ ውስጥ ጣሊያን ኢትዮጵያን ዳግም ከመውረሯ በፊት በሕዝብ አደባባይ የጣሊያንን የወረራ ዝግጅት እና ዕቅድ ለኢትዮጵያውያን አስገንዝቧል። ወረራው የማይቀር መሆኑንና ህዝቡ አንድ ሆኖ ጠላትን እንዲመክት በየአደባባዩ ያስተምር፣ ያነቃ ነበር፡፡ ህዝቡም ወረራውን ለመመከት ዝግጅት እንዲያደርግና ተዘጋጅቶ እንዲጠብቅ አጥብቆ ወትውቷል። በሀገር ፍቅር ቴአትር ቤት ውስጥ ታዋቂ ንግግር አድራጊ ስለነበረ፤ ‹‹ኢጣሊያ ኢትዮጵያን ልትወር ነው፤ ለጦርነት እንዘጋጅ›› እያለ ዲስኩር የሚያሰማ ንቁ ኢትዮጵያዊ ነበር። በአንድነቷ የጠነከረች ኢትዮጵያን ለመመስረት ብርቱ ትግልም አድርጓል፡፡

ያ በእንዲህ እንዳለ ጣሊያን አዲስ አበባ ገባች። የተመስገን የአርበኝነት ትግል ከዚህ ይጀምራል። በሞገስ አስገዶም እና አብርሀ ደቦጭ አማካይነት ተወርውራ ግራዚያኒን ካቆሰለችው ቦምብ ጀርባ ተመስገን እጁ አለበት ተብሎ ይታሰብ ስለነበር፤ ጣሊያኖች ያሳድዱት ጀመር። ቆይቶም በጣሊያኖች እጅ ወደቀ። ያኔ ጉድጓድ አፋፍ ላይ ቆመው ከተረሸኑ ዜጎች አንዱ የነበረው ተመስገን፤ “ከንፍሮ መሃል ጥሬ” እንደሚገኘው በጭፍጨፋው ዕለት በተአምር ከሞት ተረፈ። እሱም ከክምር አስከሬን መሀል ተነስቶ ወደ ሱዳን ተሰደደ። ሱዳን ውስጥ ሆኖ ዋነኛው የአርበኞች ትግል አቀጣጣይ ነበር።

ተመስገን፤ በጣሊያን ወረራ ጊዜ፤ ብዙ ተንገላቷል። ወገኖቹ ተማርከው በውሃ ጥም ምክንያት ደም የተቀላቀለበት ውሃ ሲጠጡ አይቷል። በእሱ እና በወገኖቹ ላይ ይደርስ የነበረውን በደል ለጃንሆይ ይጽፍላቸው ነበር። ጃንሆይም በስደት አገር በለንደን ሆነው የፃፈላቸውን ደብዳቤ እያነበቡ ያለቅሱ እንደነበር ተጽፏል። እንዲሁም ጃንሆይ ጄኔቫ ላይ የሊግ ኦፍ ኔሽን ስብሰባ ንግግር ሲያደርጉ የንግግራቸው አብዛኛው ሃሳብ ተመስገን ገብሬ ሱዳን ሆኖ ከፃፈላቸው ደብዳቤ የተወሰደ ነበር።

ያኔ በሲልቪያ ፓንክረስት አማካኝነት በለንደን በሚታተመው “new times and Ethiopia news” በሚል በሚታወቅ ጋዜጣ ላይ ተመስገን የፃፋቸው ፅሁፎች ይወጡ ነበር። “The Addis Ababa Massacre Italy’s National Shame” የሚል መፅሃፍ ላይ የተመስገንን የአይን እማኝነት እና ጋዜጣው ላይ የወጡ ፅሁፎቹን በዋቢነት ተጠቅሷል። ከዚህ ባሻገር ከእንግሊዝ መንግሥት ጋር በመላላክ እንግሊዝ ከኢትዮጵያ ጎን እንድትሰለፍ የዲፕሎማሲ ሥራ ሰርቷል። “ሀገራችን ነፃ መሆኗ አይቀርምና ሀገር የሚረከብ ትውልድ በትምህርት መቅረፅ አለብን” በሚል በሀገረ ሱዳን በስደት በነበረበት ወቅት ጋዳሪፍ ውስጥ የነበሩ ኢትዮጵያውያንን በተለይ ህፃናትን ያስተምር ነበር።

በጥቅሉ 30 ሺህ የአዲስ አበባ ኗሪዎችን ጭፍጨፋ በአይኑ በብረቱ ተመልክቶ የጣሊያንን ነውረኝነት በዓለም አደባባይ በማስጣት ታሪክ ከማጋራቱ ባለፈ የፋሽስቶችን ግብአተ-መሬት ካፋጠኑ የኢትዮጵያ ታላላቅ ደራሲያን መካከል ከግንባር ቀደሞቹ አንዱ ነበር።

የየካቲቱ ፋሺስታዊ ጭፍጨፋ የገፈቱ ቀማሽ የሆኑት አርበኛው ደራሲ ‹‹ዓለም በድንገት ተለውጣ፣ አዲስ አበባም ኢጣሊያኖች ኢትዮጵያውያንን የሚያርዱበት ቄራ ሆና ነበር›› ሲሉ ገልጸውታል። ይህንን ወደር የለሽ ጭፍጨፋም “የካቲት 12” በሚል ርዕስ እና “ሊቀ-ጠበብት እውነቱ” የተሰኙ ሁለት አጫጭር ልብወለዶችን ጽፎ ለትውልድ ታሪኩን ከትቦ አስተላልፏል። በአምስቱ ዓመት የፋሺስት ወረራ ጊዜም በደረሱት ‹‹በለው በለው አትለውም ወይ፤ የጥቁር አንበሳ አይደለህም ወይ›› በሚለው መዝሙሩም ይታወሳል፡፡

ከዚህም ሌላ የየካቲት 12 ቀን 1929 ዓ.ም የተደረገውን ጭፍጨፋ እና በአጠቃላይ በርሱ ሕይወት ዙሪያ ያለውን ውጣ ውረድ “ሕይወቴ” በሚል ርዕስ ፅፎታል፡፡ ይህ መፅሐፍ እርሱ ከሞተ ከ60 ዓመታት በኋላ የታተመ ሲሆን፤ የእርሱን የሕይወት ታሪክ ብቻ ሳይሆን የኢትዮጵያን ታሪክ የያዘ ነው። ምን ይሄ ብቻ በ1941 ዓ.ም በኢትዮጵያ የሥነ ፅሁፍ ታሪክ የመጀመሪያ የሆነውን አጭር ልቦለድ “የጉለሌው ሰካራም” በሚል ርዕስ ለንባብ አብቅቷል።

እዲሁም አርበኛው ተመስገን ገብሬ ከነፃነት ማግስት ወደ ሀገሩ ገብቶ የኤርትራ ድምጽ የተሰኘችው ጋዜጣ ዋና አዘጋጅ በመሆን አገልግሏል። ፋሺስት ኢጣሊያ ከለቀቀች በኋላ በሀገሪቱ ዘመናዊ አስተሳሰብና ዕድገት ዕውን እንዲሆንም ፍፁም የለውጥ አርበኛ በመሆን ሠርቷል።

በአማርኛ ቋንቋ ችሎታውና በአፃፃፍ ቴክኒኩ እጅግ የተዋጣለት ደራሲ መሆኑን የሀገሪቱ ጉንቱ ሃያሲያን መስክረውለታል። ለአብነት ሀዲስ አለማየሁ “ትዝታ” በሚለው መጽሃፋቸው በአምስቱ ዓመት የፋሺስት ወረራ ወቅት ወደ ሱዳን ተሰደው ለሀገራቸው ብዙ ሥራ ከሠሩ ሰዎች ውስጥ ግንባር ቀደሙ አርበኛው ደራሲ ተመስገን ገብሬ እንደነበር ጠቅሰው፤ “መቼም በድርሰት ዓለም ተወዳዳሪ የለውም” ብለው በእርሳቸው ብዕር ወደር የለሽ ደራሲ እንደነበር ተገልጿል።

ፀሃፊ እንዳለኔታ ከበደ በበኩሉ ሕይወቴ” የተሰኘው የአርበኛው ደራሲ መጽሀፍ እሱን ብቻ ሳይሆን፤ የዘመኑን መንፈስ ቃኘንበት፤ የአተራረክ ብቃቱን ብቻ ሳይሆን እሱና ሌሎች አርበኞች፤ በየካቲት 12/1929 ዓ.ም ስለተጎነጩት የመስዋዕትነት ፅዋ ያወቅንበት፤ በጣሊያን ወረራ ጊዜ የዚያን ዘመን ትውልድ አባላት፤ ሀገር እና ባንዲራ የሚባል መስቀል ተሸክመው፤ ምን ያህል ጊዜ እንደተገረፉ፤ ምን ያህል ጊዜ እንደተወገዙ፤ ምን ያህል ጊዜ ቀራኒዮ ተራራ ላይ ወጥተው ለነፃነት ብለው በፋሽስት ምስማር እንደተቸነከሩ ያየንበት ነው፡፡

እንደዚህ ዓይነት ሰዎች፤ በቁጥር ጥቂቶች ናቸው። አስፈላጊነታቸው የሚገባን ዘግይቶ ነው። ለመታየት በሚጓጉ እና ሌላውን ዝቅ አድርገው ከፍታ ቦታ ላይ ለመቆም በሚታትሩ ሰዎች ይሸፈናሉ። አርበኝነታቸው ጦር ሜዳ ሄዶ ተጋድሎ ለመፈፀም ብቻ የሚዘከር አይደለም። አንደበታቸውም፤ ብዕራቸውም ለሃቅ የቆመ እና ለእውነት የተገራ ነው፡፡ እንዲህ ናቸው ተመስገን ገብሬዎች” ሲሉ ፀሀፊው መስክረውለታል።

ሌላው ደራሲና ጋዜጠኛ ጥበቡ በለጠ ተመስገንን በአይነ ሥጋ ለማየት ባይታደልም አርበኛው ደራሲ በተለይ በኢትዮጵያ የሥነ- ጽሁፍ ታሪክ ያበረከተውን አስተዋጽዖ እየፈለፈሉ ለህዝብ እንዲደርስና ተመስገን ማን እንደነበር ትውልድ እንዲያውቀው የአንበሳውን ድርሻ ተወጥተዋል። ደራሲ ጥበቡም፤ “በ1930ዎቹ ኮሚኒዝም፣ ሶሻሊዝም፣ ካፒታሊዝም፣ ኢምፔሪያሊዝም ወዘተ. የመሳሰሉ የፖለቲካ ርዕዮተ ዓለም ጽንስ ሃሳቦችን በኢትዮጵያ ለመጀመሪያ ጊዜ ያስተዋወቀ የብዙ ነገሮች ፈር ቀዳጅ ነበር። የዓለምን እድገት፣ ግስጋሴ የሚያውቅና የሚከታተል ባለምጡቅ አዕምሮ ሰው ነበር። የተለያዩ አንቱታን ያተረፉ ደራሲያን የተሜን ድርሰት በሥነ-ጽሁፍ አላባውያን መዝነው፤ ሥራዎቹ ዘመናዊ፣ በሥነ-ጽሁፍ ብቃቱ ወደር የለሽ፤ ከዘመኑ የቀደመ ሰው እንደነበር መጻፋቸውን” ይናገራል።

…ተመስገን ገብሬ ከርቀት ይኼ ነው፤ በቅርበት ለማወቅ ‹ሕይወቴ›ን ማንበብ ግድ ነው፡፡ በመጨረሻም ይህ የቅኔ ጠበብት፣ አርበኛ፣ መምህር፣ ደራሲ እና ጋዜጠኛ ማንነታቸው ያልታወቁ እኩይ ግለሰቦች የተመረዘ ምግብ አብልተውት በ1941 ዓ.ም በተወለደ በ40 ዓመቱ ይህን የድካም ዓለም ተሰናብቷል። የሁለት ሴት ልጆች እና የአንድ ወንድልጅ አባት ነበረ። ታዲያ ለዚህ እውቅ ባለቅኔ፣ ደራሲ እና የነፃነት ታጋይ አርበኛ እንዴት እኛ ኢትዮጵያውያን ለባለውለታችን አንድ የመታሰቢያ ሐውልት ማቆም ከበደን? ቢቻል በመዲናዋ ካልሆነ ደግሞ በትውልድ ቦታው ደብረ ማርቆስ ከተማ ውስጥ ሥሙን፣ ዝናውንና ሥራውን የሚያወሳ የመታሰቢያ ሐውልት ቢተከልለት ስንል የሚመለከታቸው አካላትንና የኢትዮጵያ ሕዝብን በዝግጅት ክፍሉ ስም እንጠይቃለን።

The Ethiopian Herald
አዲስ ዘመን
BARIISAA
العلم
ወጋሕታ
BAKKALCHO
ዘመን
የህትመት ውጤቶቻችንን ለማንበብ
ድረገጾችንንና ፌስቡክ ገጾችንን ይጎብኙ!
የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት
ዌብሳይት፡- www.press.et
ፌስቡክ፡- Ehiopian Press Agency

አዲስ ዘመን
ረቡዕ
ስፖርት

ይህ ቦታ
ለማስታወቂያ ክፍት ነው!

# ተንታ የአትሌቲክስ ማሰልጠኛ ማዕከል- በስኬት ጎዳና

**ዓለማየሁ ግዛው**

በወሎ ዩኒቨርሲቲ የተንታ አትሌቲክስ ማሰልጠኛ ማዕከል በኢትዮጵያ አትሌቲክስ ፌዴሬሽን ድጋፍ ከሚደረግላቸው ሰባት ማሰልጠኛ ማዕከላት አንዱ ነው፡፡ ማሰልጠኛ ማዕከሉ ሙሉ የትጥቅ ድጋፍን ጨምሮ ለአትሌቶች የላብ መተኪያ እና ለአሰልጣኞች የደመወዝ ክፍያ ከፌዴሬሽኑ ያገኛል። ይህ መቀመጫውን በአማራ ክልል ደቡብ ወሎ ዞን ያደረገ ማሰልጠኛ ማዕከል ከተለያዩ የፕሮጀክቶችና የክልል ውድድሮች ታዳጊ አትሌቶችን መልምሎ በማሰልጠን ተስፋ ሰጪ እንቅስቃሴን በማድረግ ላይ ይገኛል፡፡

የማሰልጠኛ ማዕከሉ አትሌቶች የኢትዮጵያ አትሌቲክስ ፌዴሬሽን በሚያዘጋጃቸው የውድድር መድረኮች ላይ ከዓመት ዓመት በሚያደርጉት ተሳትፎ ተስፋ ሰጪ ውጤትን እያስመዘገቡ ይገኛሉ፡፡ ዘንድሮ ለ3ኛ ጊዜ በተካሄደው የማሰልጠኛ ማዕከላት አትሌቲክስ ቻምፒዮና ይህንኑ የስኬት ጎዳና በማስቀጠል በሁሉም ውድድሮች የበላይ የሆኑበትን ውጤቶችን ማስመዝገብ ችለዋል፡፡

ተንታ አትሌቲክስ ማሰልጠኛ በቻምፒዮናው በሴቶች 183 እና በወንዶች 376 ነጥቦችን በመሰብሰብ የአጠቃላይ አሸናፊና የዋንጫ ተሸላሚ በመሆን ጨርሷል፡፡ ማዕከሉ ከተመሠረተ የሦስት ዓመታት ዕድሜ ብቻ ቢያስቆጥርም በሀገር ውስጥ ተሳትፎ ከሚያስመዘግበው ተስፋ ሰጪ እንቅስቃሴ በተጨማሪ ኢትዮጵያን በዓለም መድረክ በመወከል ውጤታማ የሆኑ ወጣት አትሌቶችን በማበርከት ከዕድሜው በላይ ስኬታማ እየሆነ ይገኛል።

ማሰልጠኛ ማዕከሉ ያፈራቸውና ትልቅ ደረጃ የደረሱ ውጤታማ አትሌቶች ጥቂት አይደሉም። የኢትዮጵያን ስም ማስጠራት ከቻሉት የማዕከሉ ፍሬዎች መካከል አትሌት ጀማል ይመር፣ አትሌት ሶፊያ አሰፋና አትሌት ዘይነባ ይመር በትልቁ ተጠቃሽ ናቸው፡፡

ዩኒቨርሲቲው ከደቡብ ወሎ ዞን አስተዳደር እና ከተንታ ወረዳ አስተዳደር ጋር የሦስትዮሽ ስምምነት በመፈራረም ከታኅሣሥ 9 ቀን 2008 ዓ.ም ጀምሮ የተንታ አትሌቲክስ ማሰልጠኛ ማዕከልን በፕሮጀክት ደረጃ ተረክቦ ሲያስተዳደር ቆይቷል፡፡ ዩኒቨርሲቲው 2.5 ሚሊዮን ብር በጀት በመመደብ በአትሌቲክስ ዘርፍ መሠረታዊ ለውጥ ለማምጣትና የአትሌቶችን የምልመላና መረጣ ሂደት ሳይንሳዊ በማድረግ በጥናት የተደገፈ አሠራርን ዘርግቶ ለመጀመሪያ ጊዜ 40 አትሌቶችን በማቀፍ ነበር በ4 ዓመት ስልጠና ወደ ሥራ የገባው።



**የተንታ አትሌቲክስ ማሰልጠኛ ማዕከል ከ60 በላይ አትሌቶችን አቅፎ በማሰልጠን ላይ ይገኛል፣**

ማዕከሉን የምርምርና የተተኪ አትሌቶች ማፍሪያ ለማድረግ በ2013 ዓ.ም በጀቱን ወደ 39 ሚሊዮን ብር ያደገ ሲሆን፣ 50 አትሌቶችን በአጭር፣ በመካከለኛ፣ በረጅም ርቀትና በሜዳ ተግባራት ለማሰልጠን ወደ ሥራ ገብቷል። በአሁኑ ወቅት ከ60 በላይ አትሌቶችን አቅፎ በማሰልጠንም ሥራውን አጠናክሮ ቀጥሏል፡፡ ማዕከሉ በጦርነት ተደጋጋሚ ጉዳት ቢደርስበትም ዛሬ ላይ በማገገም ውጤታማነቱን አስቀጥሎ እየተጓዘ ይገኛል፡፡

በ3ኛው የአትሌቲክስ ማሰልጠኛ ማዕከላት ቻምፒዮና ማዕከሉን በመወከል የ10ሺ ሜትር አሸናፊ የሆነው አቤል በቀለ ማሰልጠኛ ማዕከሉን ከተቀላቀለ ሦስት ዓመት ሆኖታል፡፡ አትሌቱ ማሰልጠኛ ማዕከሉን በመወከል በክልልና በሀገር አቀፍ ደረጃ በሚደረጉ ውድድሮች ተሳትፎ በውጤታማነቱ ቀጥሏል፡፡ ለውጤቱ ማማር በማዕከሉ የሚሰጣቸው ጥሩ ስልጠናና የአየር ንብረቱ አስተዋጽኦ እንዳለው ያስረዳል፡፡ ደመወዝን ጨምሮ ለስልጠና የሚያስፈልጉ ድጋፎችን ወሎ ዩኒቨርሲቲ እንደሚያደርግላቸው ጥቅሶም አትሌቶች የሚያገኙት እንክብካቤ እንደሚያስመሰግን ተናግሯል፡፡ አትሌቱ ከአሰልጣኝ ሁሴን ሼቦ ጋር በመሆን ጠንካራ ዝግጅት በማድረግ በዓለም ቻምፒዮናና ኦሊምፒክ ለሀገሩ ውጤት የማምጣት እቅድ ይዞ እየሠራም ይገኛል።

የርዝመት ዝላይ አሸናፊ የማዕከሉ አትሌት መሠረት መኮንን ወደ ማሰልጠኛው ከገባች አንድ አመት ከስምንት ወር አስቆጥራለች። መጀመሪያ አሰልጣኝ እንዳልነበራቸውና እርስበርስ በመተጋገዝ ሲሠሩ እንደነበር የምታስታውሰው ወጣት አትሌት፣ አሰልጣኝ ከተቀጠረላቸው በኋላ ጥሩ ውጤት እየተመዘገበ እንደሚገኝ ታስረዳለች። ጂምናዚየም አለመኖሩ ግን የማዕከሉ አትሌቶች ፈተና መሆኑን አልሸሸገችም፡፡

የተንታ አትሌቲክስ ማሰልጠና ማዕከል ቡድን መሪ አቶ መሃመድ አለባቸው፣ ማዕከሉ ከኢትዮጵያ አትሌቲክስ ፌዴሬሽን የሚሰጡትን መመሪያና ሕጎችን መሠረት በማድረግ ሁሉም የስልጠና መርሐ ግብሮች እንደሚሰጡ ይናገራሉ። እንደ ቡድን መሪው ገለፃ፣ ማዕከሉ የአትሌቶች ምልመላና መረጣን ሲያደርግ ከፕሮጀክት የመጡትን አትሌቶች በመቀበል አጎልብቶ ወደ ቀጣይ ደረጃ እንዲሸጋገሩ ለማድረግ አልሞ ነው፡፡ በምልመላ ወቅትም አትሌቱ ለየትኛው ርቀትና ተግባር ይሆናል የሚለውን በሳይንሳዊ መንገድን ከለየ በኋላ የአራት አመት ስልጠና እንዲያገኙ ያደርጋል።

ከወሎ ዩኒቨርሲቲ ስፖርት ሳይንስ ክፍል ጋር በመሆን ለምልመላና መረጣ የተዘጋጀ ቴክኒካል ኮሚቴም በሳይንሳዊ መንገድን ምልመላውን ያደርጋል። በቀጣይ ማዕከሉን የአትሌቲክስ ክለብ ለማድረግ እንደታሰበም ቡድን መሪው ጠቁመዋል።

በዘንድሮው የውድድር ዓመት በዓለምና በአፍሪካ ደረጃ በተደረጉ ውድድሮች የማዕከሉ አትሌቶች ተሳታፊ መሆናቸው ከተመሠረተ አጭር ጊዜ ቢያስቆጥርም ተስፋ እንዲጣልበት አድርጓል፡፡ ይህንንም ለማስቀጠል ጥረት እየተደረገ ይገኛል፡፡ ያምሆኖ ማዕከሉ በሰሜኑ ጦርነት የወደሙ የመገልገያ መሣሪያዎቹን ለመተካት ተደጋጋሚ ጥረቶች ቢደረጉም አሁንም ችግሩ ሙሉ በሙሉ አልተቀረፈም፡፡ ይህንን ክፍተት ለመሸፈንም ማንኛውም አካል ድጋፍ እንዲያደርግ ቡድን መሪውና የማዕከሉ አትሌቶች ጥሪ አቅርበዋል፡፡ ዩኒቨርሲቲው በበኩሉ በቀጣይ ለስልጠና የሚስፈልጉ መሣሪያዎችን ጨምሮ የጂምናዚየምና የመም(ትራክ) ሥራን ለመከወን አቅዷል፡፡

በብርሃንና ሰላም ማተሚያ ድርጅት ታተመ